# አዲስ ልሳን

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ADDIS MEDIA NETWORK

ቅጽ 32 ቁጥር 3561 | ቅዳሜ የካቲት 14 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር








# ዘመናትን የተሻገረ ወዳጅነት

- ኢትዮጵያ ለቀጣናዊ ሰላም እና መረጋጋት ያላት አስፈላጊነት ይበልጥ እያደገ መምጣቱ ተመላክቷል



➔ 3

ፎቶ- ከገፀ ድር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና ፕሬዝዳንት ረጅብ ጣይፕ ኤርዶዋን ኢትዮጵያን እና ቱርክዬን ተጠቃሚ በሚያደርጉ ጉዳዮች ዙሪያ መክረዋል

## "የተገልጋይ እርካታን ከፍ የሚያደርጉ ስራዎች እያከናወንኩ ነው"

አዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት



➔ 14

ፎቶ- ከፋይል

የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ባለጉዳዮችን በማስተናገድ ላይ

## የምሽት ብርሃን ያረማቸው የነዋሪዎች ስጋቶች

➔ 6



ፎቶ- ከገፀ ድር

ለመዲናዋ የወንጀል መከላከል ሥራ አጋዥ የሆነው የኮሪደር ልማት ከፊል ገጽታ

## ኢትዮጵያን የመጎብኘት ጉጉት

➔ 11



ፎቶ- ከገፀ ድር

ዲዲጂ እና ጓደኞቹ የኢትዮጵያን ምግቦች በመመገብ ለዓለም አስተዋውቀዋል

# የጋራ ትብብር የሚሻው ሰላም

- ኅብረተሰቡ ሰላምን ለማስጠበቅ በተዘረጉ አደረጃጀቶች ላይ ያለው ተሳትፎ እንዲጠናከር የመገናኛ ብዙኃን ሚና ከፍተኛ መሆኑ ተጠቁሟል

**በስንታየሁ ምትኩ**

ያለንበት ዘመን መረጃ ከምንጊዜም በላይ ትልቅ አቅም የሆነበት ነው፡፡ ኅብረተሰቡ በዕለት ተለት ሕይወቱ ለሚያደርገው እንቅስቃሴ፣ ተሳትፎና ውሳኔ መረጃ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ በዚህ ረገድም መገናኛ ብዙኃን እውነተኛ፣ ወቅታዊና ትክክለኛ የመረጃ ምንጭ በመሆን፣ ኅብረተሰቡን በማስተማርና በማንቃት አይተኬ ሚና አላቸው፡፡

ተቋሙ በ2023 ዓ.ም ተመራጭ የሜትሮፖሊታን ሚዲያ የመሆን ርዕይ ሰንቆ እየተጋ ይገኛል፡፡ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት መፍትሔ የሚያመላክቱ፣ እያዝናኑ የሚያስተምሩ ይዘቶችን በተለያዩ የሚዲያ አማራጮቹ ተደራሽ እያደረገ ይገኛል፡፡

ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ- ከፋይል

የአዲስ አበባ ከተማ ሰላምና ጸጥታ አስተዳደር ቢሮ እና አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ አብሮ ለመስራት የሚያስችላቸውን የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመዋል






# ለአፍሪካ ከተሞች የለውጥ ፋና ወጊው ልማት

**በስንታየሁ ምትኩ**

የአፍሪካ ህብረት ዋና መቀመጫ የሆነችው አዲስ አበባ በአህጉሩ የነፃነትና አንድነት ታሪክ ትልቅ ስፍራ አላት። አፍሪካውያን በጋራ ጉዳያቸው ላይ ተሰባስበው የሚወያዩባትና የሚመካከሩባት መዲናቸው ናት፡፡ የአፍሪካ የፖለቲካ መዲና እየተባለችም ትጠራለች፡፡


ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ስሟንና ሚናዋን በሚመጥን ደረጃ በሁለተናዊ መልኩ ለውጥ እያሳየች ትገኛለች። የከተማዋን ገፅታ ከቀየሩ ስራዎች መካከል የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ይጠቀሳል። ልማቱ መዲናዋን ዘመናዊ፣ ውብና ለነዋሪዎችና ጎብኚዎች ተስማሚ እንድትሆን እያደረጋት ይገኛል፡፡

ከጥቂት ዓመታት በፊት የመዲናዋ ወንዝና

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

**አድራሻ** +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ



## ኢትዮጵያ ያገኘችው ዲፕሎማሲያዊ ትኩረት የቀጣናው ሚናዋን ግዝፈት የሚያሳይ ነው!

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ያላት ሚና ከታሪክ፣ ከጂኦ-ፖለቲካ እና ከሕዝብ ቁጥር ግዝፈት ጋር ተያይዞ ሁልጊዜም በወሳኝነቱ የሚጠቀስ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሀገሪቱ እያገኘችው ያለው ዓለም አቀፋዊ የዲፕሎማሲ ትኩረትም ይህንን እውነታ ዳግም ያረጋገጠ፣ የቀጣናዊ ሚናዋን ግዝፈትም በግልጽ የሚያሳይ ሆኗል።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድና አካባቢው ሰላምና ትብብር እንዲሰፍን የቆየና የጸና አቋም ያላት ሀገር ናት። በጎረቤት ሀገራት ግጭቶች ሲከሰቱ አስታራቂ በመሆን፣ የሰላም አስከባሪ ኃይሎችን በማሰማራት እና ቀጣናዊ ትስስርን በሚያጠናክሩ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ላይ ግንባር ቀደም ሆና ስትሠራ ቆይታለች። ይህ ሚናዋ ለቀጣናው መረጋጋት የጀርባ አጥንት መሆኗን ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በሚገባ ይረዳዋል።

ሀገራዊ ጥቅምን ማስጠበቅ የማንኛውም ሀገር የዲፕሎማሲ ማጠንጠኛ ነው። ኢትዮጵያም ይህንን መርህ በመከተል፣ እያደገ የመጣውን የሕዝብ ቁጥር እና ሰፊ የኢኮኖሚ ፍላጎት ከግምት ውስጥ ያስገባ የዲፕሎማሲ ሥራ እየሠራች ትገኛለች። በተለይም የባሕር በር ፍላጎቷን በጋራ ብልጽግና እና በሰላማዊ የዲፕሎማሲ መንገድ ለማሳካት የምታደርገው ጥረት፣ ሀገራዊ ጥቅሟን ከቀጣናው መረጋጋት ጋር አጣጥሞ የመጓዝ ጥበቧን ያሳያል።

የአፍሪካ ቀንድና አካባቢው የዓለምን ግዙፍ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የሚያሳልጠው የቀይ ባሕር መገኛ በመሆኑ፣ የኃያላን ሀገራት ትኩረት ማረፊያ ነው። ይህ የንግድ መስመር ሰላማዊ እና አስተማማኝ ሆኖ እንዲቀጥል ኢትዮጵያ የምታደርገው አስተዋጽኦ ለራሷ ብቻ ሳይሆን ለዓለም አቀፉ ንግድም ወሳኝ ነው። ሰላማዊ የንግድ መስመር እንዲኖር የሚሹ ሀገራት ሁሉ ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማጠናከራቸው የማይቀር ምርጫቸው ሆኗል።

ኢትዮጵያ ለቀጣናው ሰላምና ዕድገት ያላትን የገዘፈ ሚና በመረዳት፣ በርካታ ሀገራት የዲፕሎማሲ ግንኙነታቸውን እያጠናከሩ ይገኛሉ። ይህ ደግሞ ለሀገራዊ ዕድገታችን እና ለታላቅነታችን አዲስ ምዕራፍ የሚከፍት ነው።

ኢትዮጵያ መጻኢ ዕድሏን ከሚወስኑ ቁልፍ ጉዳዮች አንዱ የባሕር በር ነው። ይህን በሰላማዊና በሰጥቶ መቀበል መርህ ገቢራዊ ይሆን ዘንድም አበክራ እየሠራች ትገኛለች፡፡ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በቅርቡ በተካሄደው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 10ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ተገኝተው ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት፣ “በአፍሪካ ካለው ረጅም ኪሎ ሜትር የሚሸፍን የባሕር ጠረፍ ውስጥ ኢትዮጵያ የጠየቀችው 50 ኪሎ ሜትር ወደ ባሕር መውጫ በር እንዲሰጣት ነው። ከታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ፣ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ድርሻ በመስጠት አሊያም በኪራይ (ሊዝ)፣ በመሬት ልውውጥ አማራጮች በስምምነት የባሕር በር ማግኘት ትፈልጋለች” ማለታቸውም ይኸንኑ የሚያጠናክር ነው። አሁን ላይ ሀገሪቱ ያገኘችው ዲፕሎማሲያዊ ትኩረት የቀጣናዊ ሚናዋን ግዝፈት የሚያሳይ እና ጥያቄዎቿ ምላሽ እንዲያገኙ የበለጠ አቅም የሚፈጥር ነው!

# የእኔ እይታ

**ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።**

## ትኩረት የሚሻው የሰንደቅ ዓላማ ክብር ጉዳይ!

**በቸርነት ዋለልኝ ከአራብሳ**

ለሰንደቅ ዓላማ ያለን ክብርና አመለካከት ምን ይመስላል? እስቲ ሁላችንም ራሳችንን እንጠይቅ። ይህን ርዕሰ ጉዳይ ያነሳሁት ያለምክንያት አይደለም፤ በቅርቡ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ ስዘዋወር የታዘብኩት ጉዳይ ግርምትና ቁጭት ስለፈጠረብኝ እንጂ።

የመንግሥት ተቋም ነው መሥሪያ ቤቱ፤ መገኛው ከመንገድ ዳር በመሆኑ በቅጥር ግቢው ውስጥ የሚከናወነውን እያንዳንዱን እንቅስቃሴ መመልከት ያስችላል። በግምት አመሻሽ 12 ሰዓት ግድም ነበር፤ ሲውለበለብ የዋለ ሰንደቅ ዓላማ በሚወርድበት ሰዓት የሚገባውን ትክክለኛ ክብር የማይሰጡ የተቋሙን ባልደረቦች መመልከቴ ትዝብት አጭሮብኛል። ሰንደቅ ዓላማው ሲወርድ ገሚሱ የተቋሙ ሠራተኞች በተጠንቀቅ ቆመው ክብር ሲሰጡ፣ የተወሰኑት ግን በቅጥር ግቢው ውስጥ እንዳሻቸው ይንቀሳቀሱ ነበር። ይህ አጋጣሚ ለሰንደቅ ዓላማ ያለን ክብር የሚያስተዛዝብ መሆኑን አረጋግጦልኛል።

በዚህ ጉዳይ ላይ ሌሎች መታረም አለባቸው ብዬ የማስባቸውን ክፍተቶችም አስተውያለሁ። ለምሳሌ ዓመቱን ሙሉ ሰንደቅ ዓላማ የማይሰቀልበት የመንግሥት ተቋም በብዛት አያለሁ። አንዴ ከተሰቀለ በኋላ ዞር ብሎ የሚያየው አጥቶ፣ ለረጅም ጊዜ ሳይወርድ ተሰቅሎ የሚቀርም በየመንግሥት ተቋማቱ እንዳሉ አይቼ ታዝቤአለሁ።

ሌላው በአንዳንድ ተቋማት ያረጀና የነተበ ሰንደቅ ዓላማ ተሰቅሎ መመልከቴ ነው። ይህ ሕግና ሥርዓቱን ካለማወቅ የሚመጣ ነው ወይስ በቸልተኝነት? ሰንደቅ ዓላማ የአንድ ሀገር ሉዓላዊነትና የማንነት መገለጫ ነው። የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ጥልቅ ታሪካዊና ባህላዊ ትርጓሜዎች አሉት። ቀለማቱ የአንድነት፣ የነፃነትና የተስፋ ምልክቶቻችን ናቸው።

አዋጅ ቁጥር 654/2001 የኢፌዴሪ ሰንደቅ ዓላማን አጠቃቀም፣ ይዘት እና ክብር ለማስጠበቅ የወጣ ዝርዝር ሕግ ነው። ይህ አዋጅ ሰንደቅ ዓላማው የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ምልክት በመሆኑ፣ ማንኛውም ሰው ሲሰቀል ወይም ሲወርድ የሚገባውን ክብር የመስጠትና የማክበር ኃላፊነትና ግዴታ አለበት ይላል። በመቀጠልም ያረጀ፣ የተበላሸ፣ ቀለሙ የደበዘዘ፣ የቆሸሸ ወይም የተቀደደ ሰንደቅ ዓላማ መስቀልን በጥብቅ ይከለክላል።

የሰንደቅ ዓላማ አወጋገድንም በተመለከተ አንድ ሰንደቅ ዓላማ አገልግሎት መስጠት በማይችልበት ደረጃ በሚያረጅበት፣ በሚቀደድበት ወይም በማንኛውም መልኩ ሊያገለግል ባልቻለ ጊዜ እንደ ተራ ጨርቅ በየቦታው መጣል አይቻልም። ይልቁንም ተገቢው ክብር እና የአፈጻጸም ሥነ ሥርዓት ተከናውኖ በማቃጠል እንዲወገድ ይደረጋል።

ይህ ሆኖ ሳለ፣ “ለምንድን ነው ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣና ሲወርድ በአክብሮት ሥርዓቱን ጠብቀን የማናስፈጽመው?” የሚለው ነጥብ ጥያቄ ይፈጥርብኛል። ያረጀ ሰንደቅ ዓላማን ሥርዓቱን ጠብቆ በአግባቡ ከማስወገድ ይልቅ በቸልታ እንዲውለበለብ የሚደረገውስ ለምንድን ነው? ይህ ሁልጊዜ በሕሊናዬ የሚመላለስ ጥያቄ ነው። ብሔራዊ ክብር የሚጀምረው ከምናሳየው፣ ትንሿ ከምትመስል ግን ትልቅ ትርጉም ካላት ሥነ ሥርዓታዊ አክብሮት ነው ብዬ አምናለሁ።

በመሆኑም ሰንደቅ ዓላማን ማክበር የአንድ ወገን ወይም የጸጥታ አካላት ብቻ ግዴታ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም። ይህ ምልክት የጋራ ታሪካችን፣ የአሁኑ ማንነታችን እና የነገ ተስፋችን ማሰሪያ ነው። ተቋማት ያረጁ ሰንደቅ ዓላማዎችን በወቅቱ የመቀየር እና የማስወገድ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፤ ግለሰቦችም ባንዲራ ሲወጣና ሲወርድ የምናሳየው አክብሮት ለሀገር ያለንን ውዴታ መለኪያ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል።

ለሰንደቅ ዓላማችን የምንሰጠው ክብር የይስሙላ ሳይሆን ከውስጥ የሚመነጭ የዜግነት ግዴታችን ሊሆን ይገባል ብዬ አምናለሁ። ትውልዱም ይህንን ክብር ወርሶ እንዲያድግ ቤተሰብ፣ ትምህርት ቤቶች እና ሚዲያዎች የበኩላቸውን ሚና ሊወጡ ይገባል እላለሁ።

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች**

**ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ**

**ግንቦት 1985 ዓ.ም ተመሰረተች**

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ለይላ መሀመድ
ፋንታነሽ ተፈራ
ይግለጡ ጓዴ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ
ሄለን ጥላሁን

**ዋና አዘጋጅ**
ተካልኝ አማረ
Tekalignteke123@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር B91/17

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# ዘመናትን የተሻገረ ወዳጅነት

- **ኢትዮጵያ ለቀጣናዊ ሰላም እና መረጋጋት ያላት አስፈላጊነት ይበልጥ እያደገ መምጣቱ ተመላክቷል**

**በመለሰ ተሰጋ**

የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ታሪክ እንደ ራስ ዳሸን ከፍ ያለ ነው፤ እንደ ጣናም የሰፋ፤ እንደ ዳሎልም የጠለቀ፤ እንደ ዓባይም የገዘፈ፤ እንደ ንጋት ሐይቅም በድል የተንጣለለ ነው:: በእርግጥም ጥንታዊው የዲፕሎማሲ መዝገብ ሲገለጥ ከዓድዋ ድል ንግስቷ እና ከቀይ ባሕሯ እመቤት ኢትዮጵያ ጋር ለመወዳጀት በርካቶች አድማስ ጥሰው ባሕር አቋርጠው መጥተዋል:: በዚህ እውነት ውስጥም ቱርክዬ አለች::

የሁለቱ ሀገራት ታሪካዊ የሁለትዮሽ ግንኙነት የጀመረው በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኦቶማን ኢምፓየር የቀይ ባሕር ወደቦችን ሲቆጣጠር መሆኑን ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ቆይታ ያደረጉት የታሪክ ባለሙያው ጀማል ሸፈራው (ዶ/ር) ይናገራሉ::


እንደ ታሪክ ባለሙያው ገለፃ ዘመን ተሻጋሪው የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት በሂደት ወደ ዘላቂ እና ተግባራዊ ዲፕሎማሲያዊ ትስስር ከፍ ብሏል:: ይህንንም ተከትሎ እንደ አውሮፓዊያኑ አቆጣጠር በ1896 ሱልጣን አብዱልሀሚድ 2ኛ እና ዳግማዊ አጼ ሚኒሊክ ይፋዊ የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በመጀመራቸው ቱርክዬ በ1912 በሐረር ቆንስላ ጽህፈት ቤቷን ከፈተች:: በመቀጠልም እ.ኤ.አ በ1926 ኤምባሲዋን በአዲስ አበባ ቀለሰች:: ኢትዮጵያ ደግሞ በ1933 ኤምባሲዋን በአንካራ መክፈት ቻለች::

የ19ኛው ክፍለ ዘመን ዲፕሎማሲያዊ ልውውጦች በሀገራቱ ጠንካራ የኢኮኖሚ አጋርነት እንዲገነባ፣ ኢንቨስትመንት እና መሠረተ ልማት እንዲስፋፋ፣ ንግድ እና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንዲያድግ ማድረጉንም የታሪክ ባለሙያው ጀማል (ዶ/ር) ይናገራሉ::

ዘመናትን ያስቆጠረው የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት በታሪክ ላይ የተመሰረተ፣ በኢኮኖሚ የተጠናከረ እና በስትራቴጂካዊ ትብብር ከፍታውን አስጠብቆ የቀጠለ ነው:: ለዚህም የሰሞኑ የቱርክዬ ፕሬዝዳንት ረጅብ ጣይፕ ኤርዶዋን የኢትዮጵያ ጉብኝት እና በተለያዩ ጊዜያት በሁለቱ ሀገራት መካከል የተደረጉ የተለያዩ ስምምነቶች ማሳያ መሆናቸውን የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያው አቶ አህመድ ሰይድ ይናገራሉ::

በሀገራቱ መካከል ያለው የልማት ትብብር እና የሰብዓዊ ተሳትፎ ከፍ ያለ መሆኑን የሚገልፁት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ገነነ ካሳዬ ለአብነትም የሆስፒታል ግንባታ፣ የህክምና መሳሪያዎች ድጋፍ፣ የሙያ ስልጠና፣ ሰብዓዊ እርዳታ፣ የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞች፣ የስደተኞች ድጋፍ፣ የውሃ አቅርቦት ፕሮጀክቶች እና በተለይም በከተሞች የማዘጋጃ ቤት አቅም ግንባታ ላይ ከፍተኛ ድጋፍ እያደረገች እንደሆነም ገልፀዋል::

የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያው አቶ አህመድ ሰይድ እንደሚሉት ደግሞ ከምጣኔ ሀብት ባሻገር ሀገሪቱ በሰላምና በደህንነት ዙሪያ በአፍሪካ ቀንድ ያላት እንቅስቃሴም በቀላሉ የሚታይ አይደለም::



ፎቶ- ከገጸ ድር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና ፕሬዝዳንት ረጅብ ጣይፕ ኤርዶዋን ኢትዮጵያን እና ቱርክዬን ተጠቃሚ በሚያደርጉ ጉዳዮች ዙሪያ መክረዋል

በተለይም የአፍሪካ ቀንድ በዓለም ላይ በጣም ሚስጥራዊ ከሆኑ የባሕር መስመሮች መካከል አንዱ በቀይ ባሕር እና በኤደን ባሕረ ሰላጤ ኮሪደር አቅራቢያ ይገኛል። በመሆኑም በዚህ ክልል ውስጥ ያለው መረጋጋት በዓለም አቀፍ ንግድ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ከፍ ያለ ነው። ይህንን እውነት በውል የተረዳችው ቱርክዬ ደግሞ በቀጣናው ሁለንተናዊ አቅም ካላት ኢትዮጵያ ጋር በየጊዜው የተለያዩ ወሳኝ ስምምነቶችን እያደረገች መሆኑንም ጠቅሰዋል::

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ገነነ እንደሚሉት የትራንስፖርት ትስስር በግንኙነቱ ውስጥ ስትራቴጂካዊ ሚና ይጫወታል። ለዚህ ደግሞ ገናና ስም ያላቸው ሁለቱ አየር መንገዶች ትልቅ ድርሻ አላቸው:: በመሆኑም በአዲስ አበባ እና በኢስታንቡል መካከል የሚደረጉ በረራዎች ምስራቅ አፍሪካን በቀጥታ ከአውሮፓ እና ከእስያ ጋር በዋና ዋና የአየር መንገድ ማዕከላት ያገናኛሉ። ይህም ቱሪዝምን በማስፋፋትና ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎችን ለማጎልበት የሚኖረው ድርሻ ከፍ ያለ እንደሆነም ተናግረዋል::

የኢትዮጵያ እና ቱርክዬ ግንኙነት ወደ ሶስት ታላላቅና ተስፋ ሰጭ ደረጃዎች እየተሸጋገረ መሆኑን የሚናገሩት የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያው ይሄውም ስኬታማ የሆነ የንግድ ሽርክና (የእቃ እና የኢንቨስትመንት ልውውጥ።)፣ እያደገ ያለ የኢንዱስትሪ ሽርክና (የጋራ ምርት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር) እንዲሁም ኢትዮጵያን የበለጠ የአፍሪካ የገበያ የማምረቻ ማዕከል ሊያደርግ የሚችል የምርት ጥምረት የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት ከፍታ የሚያመላክቱ ናቸውም ብለዋል::

ባሳለፍነው ማክሰኞ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በኢትዮጵያ ይፋዊ ጉብኝት ካደረጉት የቱርክዬ ፕሬዝዳንት ረጅብ ጣይፕ ኤርዶዋን ጋር የጋራ መግለጫ መስጠታቸው አይዘነጋም። በዚሁ ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) እንዳሉት በመከባበር፣ በመደጋገፍና አብሮ በመስራት ከጥንት ጀምሮ የነበረውን የሁለቱ ሀገራት ወዳጅነት ለማጠናከር ከፕሬዝዳንቱ ጋር ከስምምነት መድረሳቸውን ገልፀዋል::

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለፃ ፕሬዝዳንት ረጅብ ጣይፕ ኤርዶዋን የቀጠናውን ሁኔታ የሚገነዘቡ በመሆናቸው በሁለትዮሽና የባለ ብዙ ወገን ጉዳዮች ላይ ያደረጉት ውይይት እጅግ ፍሬያማ ነበር:: ፕሬዝዳንቱ፣ ኢትዮጵያ በቀጣናው ተፅዕኖ ፈጣሪ መሆኗንና ሚናዋን መወጣት እንዳለባት ያምናሉ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ለዚህም ምስጋናቸውን አቅርበዋል::

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ኢትዮጵያ በአፍሪካ ፖለቲካና ዲፕሎማሲ ተፅዕኖ ያላት ሀገር መሆኗን ጠቅሰው፣ ከፍተኛ ዕድገት እያስመዘገበች የምትገኘው አፍሪካ በሚቀጥሉት ዓመታትም የሚገባትን ቦታ እንድትይዝ እየተሠራ ስለመሆኑም ጠቅሰዋል::

ፕሬዝዳንት ኤርዶዋን በበኩላቸው ኢትዮጵያ፣ በአፍሪካ የመጀመሪያው የእስልምና መዳረሻ እና የፍትሐዊው ንጉሥ ነጃሺ መገኛ መሆኗ ለሁለቱ ሀገራት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መጠናከር ትልቅ መሠረት መሆኑን ገልጸዋል። ይህ ጥንታዊ እና ታሪካዊ ወዳጅነት ዛሬም በልማት እና በዲፕሎማሲያዊ ትብብር ደምቆ መቀጠሉን አክለዋል።

የቱርክዬ የልማት ትብብር ኤጀንሲ (TIKA) ታሪካዊውን የንጉሥ ነጃሺ መስጂድ እና የንጉሡን መካነ መቃብር ዕድሳት ማጠናቀቁን ጠቅሰው፣ ይህም የሁለቱን ሀገራት እና ሕዝቦች ታሪካዊ ትስስር ይበልጥ እንደሚያጠናክረው መስክረዋል::

የቱርክዬ ማሪፍ ፋውንዴሽንም በሀገራቸው እና በኢትዮጵያ መካከል የትምህርትና የባህል ድልድይ በመሆን የሁለቱን ሀገራት ህዝቦች ይበልጥ የማቀራረብ ሥራውን አጠናክሮ እንደሚቀጥልም ፕሬዝዳንት ኤርዶዋን አረጋግጠዋል።

ፕሬዝዳንቱ አክለውም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ወደ ስልጣን ከመጡ በኋላ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ መስኮች ላስመዘገቡት ስኬት "እንኳን ደስ አለዎት" በማለት መልካም ምኞታቸውን ገልጸዋል። ፕሬዝዳንት ኤርዶዋን ረጅም የሀገረ መንግሥት ታሪክ እና የተረጋጋ አስተዳደር ያላት ኢትዮጵያ ለቀጣናዊ ሰላም እና መረጋጋት አስፈላጊነቷ ይበልጥ እያደገ መምጣቱንም መስክረዋል::

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት በኢትዮጵያ ከ260 በላይ የቱርክዬ ኩባንያዎች ከ2 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር በላይ የሚገመት የኢንቨስትመንት ተሳትፎ የሚያደርጉ ሲሆን፣ በ10 ሺዎች ለሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን የሥራ ዕድል መፍጠር ችለዋል::

ኢትዮጵያ በዋናነት ቡና እና ጥራጥሬዎችን ጨምሮ እንደ ሰሊጥና ተልባ ያሉ የቅባት እህሎችን ወደ ቱርክዬ የምትልክ ሲሆን፣ ለአብነትም በፈረንጆቹ 2024 ከ42 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላር በላይ የሚገመት ምርት ወደ ቱርክዬ ልካለች። በአንጻሩ ቱርክዬ ወደ ኢትዮጵያ ከምትልካቸው ምርቶች መካከል ለግንባታ ግብዓት የሚሆን ብረታ ብረት፣ መድኃኒትና የኢንዱስትሪ ግብዓቶች በዋናነት ይጠቀሳሉ።

የቱርክዬ ብሔራዊ ምክር ቤት መረጃ እንደሚያመለክተው ከሆነ በ2013 በሀገራቱ መካከል ያለው የንግድ ልውውጥ መጠን 421 ሚሊዮን ዶላር ነበር፤ እ.ኤ.አ በ2020 ወደ 842 ሚሊዮን ዶላር አድጓል:: የሀገራቱ መሪዎች ከሰሞኑ በአዲስ አበባ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን የንግድ ልውውጥ ቢያንስ ወደ አንድ ቢሊዮን ዶላር ለማድረስ እና ከዚያም በላይ ለማሳደግ አቅደዋል::

በነሐሴ 2021 የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በቱርክ ፕሬዝዳንት ረጅብ ጣይፕ ኤርዶዋን ግብዣ መሰረት ወደ ቱርክዬ ኦፊሴላዊ ጉብኝት አድርገዋል። በዚህ ጉብኝት ወቅት፣ ሁለቱ ሀገራት በወታደራዊ ስልጠና እና ትምህርት ትብብር፣ በጋራ ልምምዶች መሳተፍ፣ በመከላከያ ኢንዱስትሪ፣ በወታደራዊ መረጃ ልውውጥ እና በሎጂስቲክስ ድጋፍ ላይ የተደነገገ ወታደራዊ ማዕቀፍ ስምምነት መፈራረማቸው ይታወሳል::

ባሳለፍነው ማክሰኞ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከፕሬዝዳንት ረጅብ ጣይፕ ኤርዶዋን ጋር በብሔራዊ ቤተ መንግሥት በሰጡት የጋራ መግለጫ ሁለቱ ሀገራት በጋራ ለመፈፀም የተግባቡባቸውን የስምምነት አጀንዳዎች እና ነጥቦች ዘርዝረዋል።

በዚህም የዘርፍ ብዝሃነት (Diversification)፣ የንግድ ግንኙነቱ በተወሰኑ ምርቶች ላይ ብቻ ሳይወሰን የተለያዩ የቢዝነስ ዘርፎችን እንዲያካትት ስምምነት ላይ ተደርሷል። ታዋቂ የቱርክዬ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ኢንቨስት በማድረግ ለሀገር ውስጥ እና ለጠቅላላው የአፍሪካ ገበያ የሚሆኑ ምርቶችን እንዲያመርቱ እና ኤክስፖርት እንዲያደርጉ ድጋፍ ለማድረግ ተስማምተዋል።

ኢትዮጵያ ያቀደችውን የ10 ነጥብ 2 በመቶ ዕቅድ ለማሳካት የባሕር በር ወሳኝ በመሆኑ በሰላማዊ መንገድ የባሕር በር እንድታገኝ ቱርክዬ በዲፕሎማሲው መስክ የራሷን ጫና በመፍጠር የበኩሏን ሚና እንድትጫወት ከስምምነት ላይ መድረሳቸውም ተገልጿል።

በሌላ በኩልም ኢትዮጵያ እና ቱርክዬ በፀረ-ሽብር ትግሉ ዙሪያ በጋራ ለመሥራት ተስማምተዋል። የአየር ንብረት ለውጥን በተመለከተ ቱርክዬ ዘንድሮ የምታዘጋጀውን የኮፕ (COP) ስብሰባ በሚቀጥለው ዓመት ለኢትዮጵያ የምታስረክብ ሲሆን በዝግጅት ሂደት ውስጥ የልምድ ልውውጥ እና መደጋገፍ ለማድረግ ሀገራቱ ስምምነት ላይ ከደረሱባቸው ጉዳዮች መካከል ይጠቀሳሉ::

በቱርክዬ የመጀመሪያው የፕሬዝዳንት ጉብኝት ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት የተካሄደው እ.ኤ.አ መጋቢት 1967 ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ በቱርክ ካደረጉት ጉብኝት በመቀጠል በወቅቱ የቱርክ ፕሬዝዳንት የነበሩት ሴቭዴት ሱናይ እ.ኤ.አ ታህሳስ 1969 በኢትዮጵያ ያደረጉትን ጉብኝት ተከትሎ መሆኑን ዋና መቀመጫውን በአንካራ ያደረገውና በቱርክዬ፣ በአውሮፓ፣ በአፍሪካ እና በምዕራብ እና ደቡባዊ እስያ ላይ ያተኮሩ ዓለም አቀፍ ዜናዎችን እና ወቅታዊ ጉዳዮችን በመዘገብ የሚታወቀው TRT World "How Turkey built ties with the African continent over 23 years" በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ መጋቢት 2021 ይፋ ያደረገው መረጃ ያመለክታል::

## የጋራ ... ከገጽ 1 የዞረ

የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ፣ ፖለቲካና ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ማዕከል፣ የአፍሪካ መዲና እና በዓለም ሦስተኛዋ የዲፕሎማሲ ከተማ የሆነችውን አዲስ አበባ ከተማን ማዕከል አድርጎ የሚሠራ እንደመሆኑም፣ የከተማዋን ዕድገትና የነዋሪውን ፍላጎት የሚመጥን ተወዳዳሪና ተመራጭ ሚዲያ ለመሆን በለውጥ ምዕራፍ ውስጥ ከገባ ሰንበትበት ብሏል። በሚያቀርባቸው እንደ ዋርካ፣ አገልጋይ፣ በጠረጴዛ በመሳሰሉ አሳታፊ፣ ሞጋችና መረጃ ሰጪ ፕሮግራሞች የሕዝብ አገልጋይነቱ በየጊዜው እየጨመረ መጥቷል፡፡ ይህንንም የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባን ጨምሮ የከተማ አስተዳደሩ ተቋማት፣ የሕዝብ ምክር ቤት አባላት፣ የከተማዋ ነዋሪዎች እና ሌሎችም በተለያዩ ጊዜያት መስክረዋል፡፡

የትውልድ ድምፅ የሆነው አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የኅብረተሰቡን ፍላጎት ለማርካትና ይበልጥ ተልዕኮውን ለመወጣት ከተለያዩ ተቋማት ጋር አብሮ ለመሥራት ስምምነቶችን በማድረግ ላይ ነው፡፡ ከትናንት በስቲያም ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ጋር አብሮ ለመሥራት የሚያስችለውን የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ ተፈራርሟል፡፡




ፎቶ- ከፋይል
የአዲስ አበባ ከተማ ሰላምና ጸጥታ አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ ወ/ሮ ሊዲያ ግርማ እና የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ካሳሁን ጎንፋ ተቋማቱ በጋራ ለመስራት የሚያስችላቸውን የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመዋል

የስምምነት ፊርማው በተደረገበት ወቅት የአዲስ አበባ ሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሊዲያ ግርማ እንደገለጹት፣ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ብቻ ሳትሆን የአፍሪካ መዲና፣ በዓለም ሦስተኛዋ የዲፕሎማሲ ማዕከልና በርካታ ዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ የሚኖሩባት ከተማ ናት፡፡ ከዚህ አኳያ ዜጎች በሰላም ወጥተው እንዲገቡ፣ የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲካሄዱ፣ የከተማዋን ሰላም አስተማማኝ እና ዘላቂ እንዲሆን ማድረግ ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡

አስተማማኝና ዘላቂነት ያለው ሰላም ለማረጋገጥ ከፀጥታ አስከባሪዎች ባሻገር ነዋሪዎችን የሰላም ባለቤት ማድረግ እንደሚያስፈልግ የጠቆሙት ወይዘሮ ሊዲያ፣ በሰላምና ፀጥታ ሥራዎች ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና ሰላምን ለማስጠበቅ በሚፈጠሩ አደረጃጀቶች ያላቸው ተሳትፎ እንዲጠናከር በማድረግ ረገድ የመገናኛ ብዙኃን ሚና ከፍተኛ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ቢሮው ከአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ጋር ያደረገው ስምምነት ማኅበረሰቡ የወንጀል ሥጋቶችን፣ ሕገ-ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውርና መሰል ተግባራትን በመጠቆም እንዲሳተፍ እና እነዚህን ሕገ-ወጥ እንቅስቃሴዎች በመከላከል ለፀጥታ ኃይሉ አጋዥ የሚሆንበትን ሁኔታ ለመፍጠር ያስችላል፡፡ መንግሥትና ሕዝብ በጋራ ተባብረው እንዲሠሩ ለማድረግ ያግዛል፡፡ የኃይማኖት አባቶች፣ ምሁራን፣ ወጣቶች፣ ሴቶችና የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎችን በማሳተፍ በተለያዩ ጊዜያት የሚታዩ ኃይማኖትን

“አዲስ አበባ ከተማ ከዕለት ወደ ዕለት በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ ያላት ተቀባይነት እየጨመረ ይገኛል። ይህ የሆነውም ስኬታማ የልማት ተግባራት ከመከናወናቸው እኩል አስተማማኝ ሰላም ማስፈን በመቻሉ ነው”

ሽፋን ያደረጉ የአክራሪነትና ጽንፈኝነት እሳቤዎችን በመታገል ሂደት ማኅበረሰቡ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረውና የተዛቡ እሳቤዎችን ለመቀየር እንደሚያስችል ኃላፊዋ አብራርተዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ተቋሙ የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች ነዋሪዎች ተገንዝበው መብትና ግዴታቸውን እንዲወጡ ለማድረግ ከሚዲያው ጋር ተባብሮ መሥራታቸው አቅም እንደሚሆናቸው የተናገሩት ወይዘሮ ሊዲያ፣ በሁለቱ ተቋማት መካከል የተደረገው ስምምነት በመዲናዋ የተጀመሩ የልማት ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ለማድረግ፣ የቅድመ ወንጀል መከላከል ሥራዎችን ለማቀላጠፍ፣ የኅብረተሰቡን የተባባሪነት ግንዛቤ ለመጨመር፣ በከተማዋ እየተከናወነ ያለውን የሀገርን ገጽታ የቀየረ ልማት ለማስቀጠል የሚያግዝ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ካሳሁን ጎንፋ በበኩላቸው፣ አዲስ አበባ ከተማ ከዕለት ወደ ዕለት በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ ያላት ተቀባይነት እየጨመረ ይገኛል፡፡ ይህ የሆነውም ስኬታማ የልማት ተግባራት ከመከናወናቸው እኩል አስተማማኝ ሰላም ማስፈን በመቻሉ እንደሆነ አብራርተዋል። ሚዲያው ራሱን በሰው ኃይልና በቴክኖሎጂ አቅም በማሳደግ፣ በየጊዜው አዳዲስ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ፣ የማኅበረሰቡ ልሳን በመሆን፣ በቀን ሃያ አራት ሰዓት፣ በሳምንት ሰባት ቀን፣ በአምስት የሀገር ውስጥ እና በሁለት ዓለም አቀፍ ቋንቋዎች መረጃዎችን ለአድማጭ፣ ተመልካች እንዲሁም አንባቢያን እያደረሰ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

“የአዲስ አበባ ሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ የከተማዋን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ በርካታ ሥራዎችን እየሠራ ነው፡፡ እነዚህን ሥራዎች ኅብረተሰቡ እንዲያውቃቸው ማድረግ ያስፈልጋል” ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፣ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክም ወደ ማኅበረሰቡ በመውረድ፣ ችግሮችን ነቅሶ በማውጣትና ለሚመለከተው የመንግሥት አካል በማቅረብ በመንግሥትና ሕዝብ መካከል ድልድይ በመሆን እየሠራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡


ሚዲያው በተለያዩ ቋንቋዎች መረጃዎችን ተደራሽ እያደረገ እንደሆነ ያነሱት አቶ ካሳሁን፣ በቀጣይም ከከተማዋ ዕድገት ጋር አብሮ ለመራመድና የማኅበረሰቡን ፍላጎት ለማርካት በቁርጠኝነት እየሠራ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

ባለፈው መስከረም ወር የሚዲያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና የማኔጅመንት አባላት ወንጀልን አስቀድሞ የመከላከል፣ ሰላምንና የሕግ የበላይነትን የማረጋገጥ ተልዕኮን በመያዝ እየሠራ በሚገኘው የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ በመገኘት በቴክኖሎጂ አጠቃቀምና በተለያዩ ጉዳዮች ያከናወናቸውን የሪፎርም ሥራዎችን መጎብኘታቸውና ውይይት ማድረጋቸው ይታወሳል፡፡

በወቅቱም የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር ጀነራል ደመላሽ ገብረሚካኤል አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ሕዝብና መንግሥትን እንደ ድልድይ ሆኖ በማገናኘት እየሠራቸው ያሉ ሥራዎች ይበል የሚያሰኙ ናቸው ብለዋል፡፡ ወንጀልን ለመከላከል የሚደረጉ ጥረቶችና በከተማዋ ውስጥ የሚከናወኑ ሁሉን አቀፍ ልማቶች ላይ ሕዝቡ የተሟላ መረጃ እንዲኖረው ከማድረግ አንጻር የሚሠራውን ሥራ አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ተናግረዋል፡፡ የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ካሳሁን ጎንፋ በበኩላቸው፣ ሚዲያው የፌዴራል ፖሊስ ከሌሎች የፀጥታ ተቋማት ጋር በመቀናጀት፣ በቴክኖሎጂ በመታገዝ የከተማውን ሰላም እና ፀጥታን በማስከበርና የትራፊክ እንቅስቃሴን በማሳለጥ በኩል የሚሠራቸው ተግባራትን በመከታተል ለሕዝብ ተደራሽ በማድረግ እንደሚሰራ መናገራቸው ይታወሳል፡፡

በከተማ ደረጃ ከዚህ በፊት አዲስ ሚዲያ ኔትወርክ እና የከተማዋ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን፣ የቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ፣ ሥራና ክህሎት ቢሮ፣ ትምህርት ቢሮ፣ ትራንስፖርት ቢሮን ጨምሮ የተለያዩ ተቋማት ከሚዲያው ጋር ለመሥራት የሚያስችላቸውን ስምምነት መፈራረማቸው ይታወሳል፡፡ ሚዲያው በአዲስ ሚዲያ ኔትወርክ (AMN) እና ኤ ኤም ኤን ፕላስ የቴሌቪዥን ቻናሎች፣ በኤፍኤም 96.3 ሬዲዮ፣ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ፣ በዲጂታል ሚዲያ አማራጮች በከተማዋ የሚካሄዱ የልማት እንቅስቃሴዎች፣ የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ፣ የመልካም አስተዳደር እና ሌሎች ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ መረጃ ሰጪ፣ አስተማሪና አዝናኝ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ እየሠራ ይገኛል፡፡

# ለአፍሪካ ... ከገጽ 1 የዞረ



ፎቶ- ከገፀ ድር

የተለያዩ የአፍሪካ ከተሞች ከንቲባዎች እና የስራ ኃላፊዎች የአዲስ አበባን የወንዝ ዳርቻ ልማት በጎበኙበት ወቅት

የወንዝ ዳርቻዎች አይደለም ለመኖር፣ ለማየትና በአካባቢያቸው ለማለፍ የሚጠየፏቸው፣ የሚሰነፍጥ ሽታና በሽታ ምንጭ የነበሩ፣ ተፈጥሯዊ ቀለማቸውን አጥተው እንደተቃጠለ ናፍጣ የጠቆሩና የፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃና መጣያ ሆነው በከፍተኛ ደረጃ የተበከሉ ነበሩ፡፡

በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አነሳሽነት በአዲስ አበባ ከእንጦጦ ተራራዎች አንስቶ እስከ አቃቂ ወንዝ ድረስ 51 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን የወንዝ ዳርቻ ልማት እየተከናወነ ይገኛል። በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከንቲባ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ጥላሁን ወርቁ ከዚህ ቀደም ለዝግጅት ክፍላችን እንደጠቆሙት፣ የወንዝ ዳርቻ ልማቱ የአዲስ አበባን የጎርፍ ተጋላጭነትን በመቀነስ፣ የህዝብ መናፈሻ ፓርኮችን በማበራከት፣ የብስክሌትና የመሮጫ መንገዶችን በመፍጠር፣ የቱሪዝም መዳረሻ በማድረግ፣ የከተማዋን ዕይታ በመለወጥ፣ የህብረተሰቡን ደህንነት በማሻሻል፣ በልማቱ ላይም ሆነ ከልማቱ በኋላ በርካታ የሥራ ዕድል በመፍጠር ትልቅ አቅምን እየፈጠረ ነው፡፡

የወንዝ ዳርቻ ልማቱ ድልድዮች፣ ግድብ፣ አረንጓዴ ቦታዎች፣ የህፃናት መጫወቻዎች፣ የህዝብ መፀዳጃ ቤቶች፣ የመዝናኛ ማዕከላት፣ የውኃ ትራንስፖርት እና የንግድ ማዕከላት፣ የእግር ጉዞ ማድረጊያና የመሮጫ ትራኮች፣ የብስክሌት መስመሮች፣ ወንዞች እንዳይበከሉ የሚያደርጉ የፍሳሽ ማስወገጃ መሰረተ ልማቶችን አካትቶ በመሰራት ላይ ይገኛል፡፡

በአሁኑ ወቅትም የከተማዋ ወንዞች ለዓይን ማራኪ፣ ፅዱና አረንጓዴ ሆነዋል፡፡ ተፈጥሯዊ ቀለማቸውን መያዝ ጀምረዋል። ነዋሪዎች የእረፍት ጊዜያቸውን ለማሳለፍ የሚመርጧቸው ስፍራዎች መሆን ችለዋል፡፡ ወደ መዲናዋ የሚመጡ የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች፣ የከተሞች ከንቲባዎች፣ ባለሙያዎችና የተለያዩ ዜጎች የሚጎበኟቸው፣ ልምድና ተሞክሮ የሚወስዱባቸው ሆነዋል፡፡

ከሁለት ሳምንት በፊት የተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን ባደረገው ጥናት በከተሞች የፋይናንስ አስተዳደር አዲስ አበባ ከስድስት የአፍሪካ ከተሞች ቀዳሚ መሆኗን በቅርቡ ይፋ ማድረጉ ይታወሳል፡፡ በከተሞች የተሞክሮ ልውውጥ ላይ ለመሳተፍ ወደ አዲስ አበባ ከመጡት የአፍሪካ ዋና ከተሞች ከንቲባዎችና አስተዳዳሪዎች መካከል የኬንያ ዋና ከተማ ናይሮቢ ምክትል አስተዳዳሪ ጀምስ ሙችሪ አንዱ ናቸው፡፡

ሙችሪ ከሌሎች የአፍሪካ ከንቲባዎች ጋር በመሆን የአዲስ አበባን የወንዝ ዳርቻ ልማት በጎበኙበት ወቅት በሰጡት አስተያየት፤ "ያየነው ልማት ናይሮቢን ጨምሮ ሌሎች ከተሞችን ንጹህና ውብ ለማድረግ ምን መስራት እንዳለብን ጥሩ ምሳሌ የሚሆን ነው፡፡ በናይሮቢ የሚገኙ ወንዞች የተበከሉና በዙሪያቸው ቆሻሻ ስላለ ለእይታ ደስ አይሉም፡፡ የአዲስ አበባ ልማት ጥሩ እቅድና ሀብት በመመደብ ምን መስራት እንደሚቻል ጥሩ ማሳያ ነው" ሲሉ የወንዝ ዳርቻ ልማቱን አድንቀዋል፡፡ ለተገኘው ውጤትም የከተማ አስተዳደሩን እና የፌዴራል መንግስቱን አመራሮችን ያደነቁት ምክትል አስተዳዳሪው፣ ይህ ተሞክሮ ተወስዶ በናይሮቢ የወንዝ ዳርቻ ልማት እየተተገበረ እንደሆነ አንስተዋል፡፡

የኬንያው ፕሬዝዳንት ዊሊያም ሩቶ የአዲስ አበባን ተሞክሮ በመውሰድ በናይሮቢ የወንዝ ዳርቻ ልማት ያስጀመሩት ባለፈው ዓመት ነበር። ፕሮጀክቱ የከተማዋን ውበት፣ ፅዳት እና ለኑሮ ያላትን የምቹነት ደረጃ ከፍ የማድረግ፣ የትራንስፖርት መሰረተ ልማትን የማዘመን እና የነዋሪውን እንቅስቃሴ የማቀላጠፍ ተስፋ ተጥሎበታል፡፡ ለነዋሪዎቿ እና ለጎብኚዎች የምትመች የነቃች ከተማ እንድትሆን ለሚያግዘው ፕሮጀክት 50 ቢሊዮን የኬንያ ሽልንግ ተበጅቶለታል፡፡

ፕሬዝዳንት ሩቶ ፕሮጀክቱን ይፋ ባደረጉበት ወቅት፤ "በሚቀጥሉት 24 ወራት ውስጥ በናይሮቢ እጅግ ፅዱና የሚያማምሩ ወንዞችን እንመለከታለን። ወንዞችን መልሶ የማልማት ሥራው 50 ሺህ የጋራ መኖሪያ ቤቶች፣ ዘመናዊ የገበያ ማዕከላት፣ የትራንስፖርት እና መሰል አገልግሎት መስጫ መሰረተ ልማቶችን ባካተተ መልኩ የሚተገበር ነው፡፡ 60 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ዝርጋታም የፕሮጀክቱ አንድ አካል ተደርጎ ይተገበራል፡፡ ፕሮጀክቱ የጎርፍ አደጋን ለመከላከል፣ ጤናማ፣ ዘመናዊና ደረጃውን የጠበቀ የመኖሪያ ከባቢን ዕውን ለማድረግም ያግዛል" ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ለውጥ በኬንያ ብቻ ሳይሆን በደቡብ አፍሪካም በመልካም ተሞክሮነት ተነስቷል፡፡ ባለፈው ዓመት ለአፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ አዲስ አበባ በተገኙበት ወቅት ከተማዋን ተዘዋውረው

**የኢትዮጵያ የወንዝ ዳርቻ ልማት ልክ እንደ አረንጓዴ አሻራ ለመላው አፍሪካ ምልክትና ምሳሌ የሚሆን ነው**

የመጎብኘት ዕድል ያገኙት የሀገሪቱ ፕሬዝዳንት ሲሪል ራማፎሳ በአዲስ አበባ አስደናቂ ለውጥ በመደመም "ጆሀንስበርግ እንደ አዲስ አበባ እንድትሆን እንሠራለን" ማለታቸው ይታወሳል፡፡

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ባለፈው ነሐሴ ወር 2017 ዓ.ም "የመደመር መንግስት" የተሰኘውን አራተኛውን መጽሐፋቸውን በተመለከተ ከፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ጋር ባደረጉት ቆይታ፣ በአዲስ አበባ የወንዝ ዳርቻ የተሰራው ልማት ለአፍሪካ ተምሳሌት እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

"ምንም ጥርጥር የለውም፤ የኢትዮጵያ የወንዝ ዳርቻ ልማት ልክ እንደ አረንጓዴ አሻራ ለመላው አፍሪካ ምልክትና ምሳሌ የሚሆን ነው፡፡" ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገደልና የቆሻሻ መጠራቀሚያ የነበሩ የወንዝ ዳርቻዎች አሁን የተለየ ውበትና ገፅታ ይዘዋል፡፡ ለበርካታ ወገኖች የንግድና የስራ ዕድል ፈጥረዋል። የሀገርን ገፅታና መልክ መቀየራቸውንም ተናግረዋል።

በቅርቡ በተካሄደው 39ኛው የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ ላይም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ይህንን የሚያጠናክር ሀሳብ ሰጥተዋል። በአዲስ አበባ የወንዝ ዳርቻ ማልማት ስራ የተራቆቱ የወንዝ ዳርቻዎች ወደ ንፁህና እንቅስቃሴ የሞላባቸው የህዝብ መናፈሻ ቦታዎች ተቀይረዋል፡፡ የጎርፍ አደጋ ስጋትን መቀነስ፣ የሰዎችን ክብር ማስጠበቅና የማህበረሰቡን ህይወት ማጠናከር ተችሏል ነው ያሉት፡፡

ግሎባል ፒስ ባንክ በተሰኘ በሰላም ግንባታ ዙሪያ የሚሰራ መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም የሰላም ግንባታና ፕሮሞሽን ዳይሬክተር እና የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ምሁሩ አቶ ደያሞ ዳሌ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት ሀሳብ፣ ኢትዮጵያ አፍሪካዊያን ከቅኝ ግዛት ለመውጣት ባደረጉት ትግል ቅኝ ባለመገዛት ተምሳሌት ከመሆን ባሻገር በገንዘብ፣ በስልጠና፣ በሞራልና በዲፕሎማሲም አይተኬ ሚና አድርጋለች፡፡ አፍሪካውያን ነጻነታቸውን እንዲያገኙና ወደ አንድነት እንዲመጡ የቀድሞውን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (የአሁኑ የአፍሪካ ህብረት) በመመስረት ወሳኝ ሚና ተወጥታለች፡፡

ኢትዮጵያ አሁንም በታሪክ የነበራትን ሚና እያስቀጠለች እንደምትገኝ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ አቶ ደያሞ ያነሳሉ። በቅርቡም በራሷ ሀብት፣ ጉልበትና አቅም ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን በመገንባት፣ በአረንጓዴ አሻራ ዛፍ በመትከል፣ አዳዲስ በጀመረቻቸው የማዳበሪያ ፋብሪካ፣ የጋዝ፣ የአየር ማረፊያ ግንባታና ሌሎች ትላልቅ ፕሮጀክቶችን በመገንባትና በመጀመር በኢኮኖሚ ረገድም አፍሪካዊያን ከብድርና እርዳታ ተላቅቀው በራሳቸው መቆም እንዲችሉ ተምሳሌት እየሆነች መጥታለች፡፡ እነዚህ ስራዎች አፍሪካውያንን እርስ በእርስ ለማስተሳሰርና የኢኮኖሚ ውህደት ለማምጣት የሚያግዙም ናቸው፡፡

የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ እንደሚሉት፣ የአፍሪካ መዲና የሆነችው አዲስ አበባ በከተማ ልማት እያሳየች ያለው ለውጥ የአፍሪካ መዲናነቷን የሚያጎለብትና ለሌሎች የአፍሪካ ከተሞች በአርዓያነት የሚጠቀስ ነው፡፡ አዲስ አበባም ሆነ ሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞች ምስረታ ፕላንን የተከተለ አይደለም፡፡ የአፍሪካ ህብረትና የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ፣ በዓለም ሦስተኛዋ የዲፕሎማሲ ማዕከል ብትሆንም ከዘመናዊ ከተማነት አኳያ ብዙ ጉድለቶች ነበሩባት፡፡

"አሁን ላይ በኮሪደርና ወንዝ ዳርቻ ልማት ውብ፣ ፅዱና አረንጓዴ ከተማ ሆናለች" የሚሉት የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ አቶ ዳያሞ፣ ለምሳሌ የኬንያን ዋና ከተማ ናይሮቢን ብንወስድ ፅዱና ውብ የሆነ አካባቢ እንዳለ ሁሉ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ዜጎች የሚኖሩባቸው ያረጁ ሰፈሮች እንዲሁም የቆሸሹ ወንዞች ያሉባቸው አካባቢዎች አሉ፡፡ ደቡብ አፍሪካም በጣም ቆንጆ የሚባሉ ከተሞች ቢኖራትም ጥቁሮችና ደሃ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች የሚኖሩባቸው የቆሸሹ አካባቢዎች ይገኛሉ፡፡ ከዚህ አኳያ በአዲስ አበባ በወንዝ ዳርቻ የተሰራው ልማት ለብዙ ከተሞች ምሳሌ የሚሆን ነው፡፡ 39ኛውን የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ ለመሳተፍ የመጡ የአፍሪካ መሪዎች ከአዲስ አበባ ተሞክሮ ለመውሰድ መልካም አጋጣሚ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

# የምሽት ብርሃን ያረማቸው የነዋሪዎች ስጋቶች

- **የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ወንጀልን ለመከላከል አይተኬ ሚና እንዳላቸው ተመላክቷል**

**በሄለን ጥላሁን**



ፎቶ- ከገፀ ድር

ለመዲናዋ የወንጀል መከላከል ሥራ አጋዥ የሆነው የኮሪደር ልማት ከፊል ገፅታ

ወጣት ቢንያም ወልዴ ይባላል። ከምሽቱ 1፡30 ሰዓት ገደማ ከሥራ አምሽቶ በመውጣት በተለምዶ መገናኛ "ማማስ ኪችን" ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የአያት ጣፎ ታክሲ ለመያዝ ይሰለፋል። የታክሲ ሰልፉን ርዝማኔ ሲያይ ተስፋ በመቁረጥ "ቢያንስ አንድ ፌርማታ የሚያክል የእግር ጉዞ ባደርግ የአውቶቡስ ትራንስፖርት አማራጭ አገኛለሁ" በሚል በእግሩ መጓዝ ይጀምራል። ሆኖም ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላ ለማመን የሚከብድ ነገር ይገጥመዋል።

ከኋላው አንድ ወጣት 'የኔ ወንድም' ብሎ ይጠራዋል። ዞር ሲል በጀርባው የያዘው ቦርሳ ዚፕ ክፍት እንደሆነ ይነግረዋል። ሐሳቡንም ቀልቡንም ወደ ቦርሳው ባደረገበት ቅጽበት፣ ከየት መጡ ሳይባል ሁለት ጎረምሶች ጉሮሮውን አንቀው በመያዝ ያለውን ንብረት በሰላም እንዲያስረክብ ይጠይቁታል። እሱም ያለበትን ሁኔታና የጎረምሶቹን ጭካኔ በመገንዘብ የተባለውን ሁሉ እንደፈጸመ ያስታውሳል። ይህን ማድረግ ባይችል በያዙት ጩቤ ወግተው ጨለም ወዳለ ስፍራ ወስደው እንደሚጥሉት እንደነገሩትና ከማድረግም እንደማይመለሱ በተሰበረ ስሜት አጫውቶናል።

በወቅቱ ሁለት ስልኮች፣ ስማርት ሰዓት፣ ታብሌት እና ጥቃቅን ንብረቶቹን ከመውሰዳቸው ባሻገር፣ ጉሮሮውን ጠፍንገው የያዙበት ቦታ ላይ ከፍተኛ የሕመም ስሜት እንደነበረበትና በዚህ ምክንያት ለሁለት ሳምንታት ድምፅ አውጥቶ ለማውራት ይቸገር እንደነበር ያስታውሳል።

ቀደም ባሉት ጊዜያት የመንገድ ዳር መብራቶች በተለያዩ ምክንያቶች ከአገልግሎት ውጪ መሆን፣ የመብራት መጥፋት እንዲሁም ከነአካቴው ማታ ላይ ብርሃን አለመስጠት አዝማሚያዎች በስፋት በመከሰታቸው፣ ለእንደዚህ ዓይነት የወንጀል ጥቃቶች ምቹ ሁኔታ ሲፈጥሩ መቆየታቸውን የሚገልጸው ወጣት ቢንያም፤ "ይህ ሁኔታ በእኔ ብቻ የደረሰ አይደለም፤ የተለያዩ የቅርብም ሆነ የሩቅ ሰዎች መሰል አደጋ ደርሶባቸው ያውቃሉ" ብሏል። አሁን ላይ ጨለማን ተገን አድርጎ ወንጀል የሚፈጸምበት ችግር በከፍተኛ ደረጃ ተቀርፏል። ምክንያቱም በኮሪደር ልማት ሥራዎች አማካኝነት አሁን ላይ አዲስ አበባ ውስጥ በምሽት እንደልብ የመንቀሳቀስ አዝማሚያ በስፋት ይስተዋላል። ሰዎችም የእግር መንገድ ካደረጉ በኋላ ቢደክማቸው አረፍ በማለት ጥሩ ነፋሻማ አየር እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል። ከዚህ በተጨማሪ "ሌባ ከኋላዬ ያዘኝ አልያዘኝ" የሚለው ሥጋት እንዳይፈጠር በየመንገዱ የተገጠሙ የደህንነት ካሜራዎች የደህንነት ስሜት እንዲሰማቸው እንዳደረጋቸውም አክሏል።

ሌላኛዋ አስተያየት ሰጪ ወይዘሮ ባዩሽ አንዷለም ይባላሉ፤ ነዋሪነታቸው ሰሜን ሆቴል ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነው። ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት፣ ጨለማን ተገን ያደረገ ወንጀል ተፈጽሞባቸው እንደሚያውቅ ነግረውናል። እሳቸው እንዳስረዱት ሁነቱ የተከሰተው ከዛሬ አራት ዓመት በፊት ነበር። የወለደች ልጃቸውን ለማረስ ቦሌ ሩዋንዳ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ መመላለስን የዕለት ተዕለት ተግባራቸው አድርገውት ነበር። ታዲያ የተለያዩ የትራንስፖርት አማራጮችን በመጠቀም ወደ ቤታቸው ለመመለስ በሚያደርጉት ጥረት ውስጥ የእግር መንገድ ጉዞ ማድረጋቸው ግድ ይላቸው ነበር።

በዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በነበራቸው የተደጋገመ ምልልስ የደረሰባቸውን አጋጣሚ ሲያስታውሱ፡- "ለአይን ያዝ ሲያደርግ ሀገር ሰላም ብዬ ከልጄ ቤት ወደ ትራንስፖርት መያዣ ስፍራ እያቀናሁ እያለ፣ ፈርጠም ፈርጠም ያሉ ወጣቶች የዝርፊያ ጥቃት አደረሱብኝ። ድርጊቱን የፈጸሙብኝ ጉሮሮዬን በማነቅ ምንም ዓይነት ድምፅ እንዳላሰማ ካደረጉ በኋላ ነው። ቦርሳዬ ውስጥ ያለውን ገንዘብ ለትራንስፖርት እንኳን ሳያስቀሩ በማውጣት፣ ስልኬንና የወርቅ ቀለበቴን ከጣቴ ላይ በማውለቅ ዘረፋ ፈጸሙብኝ። ይህን ሲያደርጉ የተጠቀሙት ኃይልና ጉልበት ራሴን እስከመሳት አድርሶኝ ነበር። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ራሴን ሳውቅ ከአንድ ጥግ ወድቄ አገኘሁት። ሕልምም መሰለኝ። ለመጮህ ፈለግሁ፤ ነገር ግን ጉሮሮዬ ላይ ያለው የሕመም ስሜት እንዳልጮህና ድምፅ እንዳላወጣ አስቸገረኝ። ራሴን ለማረጋጋት ሞከርኩ። በደረሰብኝ ወንጀል አዝኜ፣ ለልጄም ሳልነግር ከተሳፋሪዎች የታክሲ ገንዘብ ለምኜ ወደ ቤቴ አቀናሁ" በማለት በቅጽበት ውስጥ የተፈጸመባቸውን ከባድ ወንጀል አስታውሰዋል። "አሁን ላይ በተከናወነው የኮሪደር ልማት ምሽቱን እንደ ቀን ያደመቁ መብራቶች እንዲኖሩ ተደርገዋል። ይህም ሰዎች ያለምንም ሥጋት እንዲንቀሳቀሱ ዕድል ፈጥሯል" ሲሉ ሐሳባቸውን አጋርተዋል።

ሌላኛው አስተያየት ሰጪ አቶ እንደአወቀ መስፍን በተለይ በወንዝ ዳርቻዎች አካባቢ ከዝርፊያ አንስቶ እስከ ነፍስ ማጥፋት የደረሰ ጥቃት በነዋሪዎች ላይ ይፈጸም እንደነበር አንስተዋል። እንደ ማሳያ ባነሱት ሐሳብ ላይ እንዳስረዱት፣ አንዱ ወዳጃቸው በጀርባው ያነገበውን ቦርሳ ላፕቶፕ መስሏቸው መንጭቀው አፍንጮ በር ተብሎ በሚጠራው የወንዝ ዳርቻ ዘልቀው በመግባት እንደተሰወሩባቸው አስረድተዋል። አሁን ላይ ግን ወንዞቻችን ታከመው የሌቦች መደበቂያ ከመሆን ይልቅ የመዝናኛ አማራጮች መሆን በሚችሉበት መልኩ መልማታቸው ትልቅ እፎይታን ፈጥሯል። አሁን ላይ ወንዝ ዳርቻዎች ሲደርስ የነበረው ወንጀል በመቀረፉ፣ ሰዓት ሳይመርጡ ለመንቀሳቀስ እንዳስቻሉ በመግለጽ ይህ ልማት እያበረከተ ያለውን ፋይዳ አብራርተዋል።

የዜጎችን ሰላማዊ እንቅስቃሴ ከሚያውኩ ተግባራት መካከል አንዱ ዝርፊያ፣ ነፍስ ማጥፋት እና መሰል የወንጀል ድርጊቶች ስለመሆናቸው የሚናገሩት የአዲስ አበባ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ የወንጀል መከላከል ዋና መምሪያ ኃላፊ ኮማንደር ገዛኸኝ ጌታነህ ናቸው። ወንጀል የሚፈጽሙ አካላት ይህን ድርጊት ለመፈጸም ምቹ የሆነ ጊዜና ሁኔታን ይመርጣሉ። አዲስ አበባ ከተማ ቀድሞ የነበራት ገጽታ ለጸጥታ ሥራ ምቹ የምትባል አልነበረችም። እንደ ሀገር እየተሠሩ ያሉ እንደ ኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ሥራዎች የከተማዋን ጸጥታ በማስጠበቅ ረገድ አይተኬ ሚና እያበረከቱ መሆኑን አብራርተዋል።

ከላይ የተጠቀሱት የልማት ሥራዎች ከመከናወናቸው በፊት በምሽት ጊዜ በተለይ የመንገድ መብራት በተበላሸባቸው አልያም በሌለባቸው አካባቢዎች ዝርፊያ፣ የነፍስ ማጥፋት እንዲሁም መኪኖች ሰዎችን ገጭተው የማምለጥ አዝማሚያ ይታይ ነበር። የኮሪደር ልማቱን ተከትሎ በየጎዳናው ባሉ መብራቶች ላይ የደህንነት ካሜራዎች መገጠማቸው "ለእኛም ሥራዎችን በእጅጉ አቅልሎልናል" ሲሉ ተናግረዋል።

"የደህንነት ካሜራ መረጃዎችን በመጠቀም ወንጀል የሚፈጽሙ አካላትን አድነን የምንይዝበት አግባብ አለ" የሚሉን ኮማንደር ገዛኸኝ፣ አንድ አሽከርካሪ በሰው ሕይወት ላይ አደጋ አድርሶ ከአካባቢው ቢሰወር እንኳ የመኪናው ሰሌዳ ከካሜራዎቹ እይታ አያመልጥም ብለዋል። አንዳንድ ሰፈሮች የወንጀል መንስኤ የመሆን ዕድላቸው ሰፊ ነው። በተለይ እንደ ካሳንቺስ፣ አራት ኪሎ፣ ፒያሳ የመሳሰሉት አካባቢዎች ሺሻ ቤት፣ አረቄ ቤት እንዲሁም ሴተኛ አዳሪዎች በስፋት ይገኙባቸውና ይህን ተከትሎ ለወንጀሎች መጠንሰስና መፈጸም ምንጮች ነበሩ። የእጅ ቦርሳ ስርቆት፣ የሞባይል ስልክ ንጥቂያ፣ የላፕቶፕ፣ የእጅና የአንገት ጌጥ ዝርፊያ፣ የመኪና ስፖኪዮ እና መሰል ቁሳቁሶችን የመስረቅ አዝማሚያ በስፋት ይስተዋል ነበር። ወንጀለኞች ጨለማን ተገን አድርገው ዝርፊያ ሲፈጽሙ በሚኖረው ትንቅንቅ ቀላልና ከባድ የአካል ጉዳት ይደርስ ነበር። ወንጀለኞች ሰርቀው እንደ መሸሸጊያ የሚጠቀሙባቸው አካባቢዎች የወንዝ ዳርቻዎችን እንዲሁም መንደሮችን በመሆኑ ሳቢያ ለፖሊስም ጭምር አስቸጋሪ ሁኔታ ይፈጠር እንደነበር አስረድተዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት የፍትሕ እና መልካም አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የአዲስ አበባ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያን የ2018 ዓ.ም የ6 ወር ሥራ አፈጻጸሙን በገመገመበት ወቅት፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ የወንጀል መከላከል እና መቆጣጠር ሥራው ውጤታማ እየሆነ መምጣቱን አሳውቋል። እንደ መረጃው ከሆነ የሕብረተሰቡ ሥጋት ናቸው ተብለው የተለዩ ከባድ ወንጀሎችን ለመቆጣጠር በተሠራ ሥራ፣ በ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያ 6 ወራት የተመዘገበው ውጤት ከ2017 ዓ.ም የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት ጋር ሲነጻጸር በ46 ነጥብ 3 በመቶ ወንጀልን መቀነስ ተችሏል። ለውጤቱ መሳካት አስተዋጽኦ ካደረጉ ምክንያቶች መካከል የኮሪደር ልማት ሥራው አይተኬ ሚና እንዳለው ተመላክቷል።

እንደ ኮማንደር ገዛኸኝ ገለጻ፣ ከዚህ ቀደም የወንዝ ዳርቻዎች የወንጀለኞች መሸሸጊያ እና ማምለጫ ሆነው ለበርካታ ዓመታት ቆይተዋል። አሁን ግን ወንዞችን ተገን ያደረገ የወንጀል ድርጊት ሙሉ ለሙሉ ቀርቷል። ከተማው ላይ ያሉ መብራቶች ምሽቱን ሙሉ ብሩህ ድባብን የፈጠሩ በመሆናቸው ሰላማዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ ተችሏል። ሰዎች ተቻኩለውና በሥጋት ውስጥ ሆነው የምሽት እንቅስቃሴ ከማድረግ ይልቅ የመዝናናትና ጥሩ ጊዜ የማሳለፍ ባሕል እያዳበሩ ይገኛሉ።

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ

# የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለት መከላከል ደንብ ቁጥር 180/2017

## (ክፍል 2)

ጣናበል ለማ (ዐቃቤ ህግ)

ውድ አንባቢዎቻችን፤ ባለፈው ዕትም በዋና ርዕስ ስር የአካባቢ ጥበቃ የሕግ ማዕቀፎች እንዲሁም የወንዝ ዳር የኮሪደር ልማት ለአካባቢ ጥበቃ ሕጎች ሊያበረክት የሚችላቸውን በጎ ተፅዕኖዎች እና ተያያዥ ጉዳዮችን በክፍል አንድ አስነብበናችኋል። የመጨረሻውን ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅተንላችኋል። መልካም ንባብ!

### 3. የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለት መከላከል ደንብ ቁጥር 180/2017

የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለት መከላከል ደንብ የወጣው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 84/2016 አንቀፅ 94 መሠረት አድርጎ ነው። የደንቡ ተፈጻሚነትም በአስተዳደሩ ወሰን ውስጥ በሚገኙ ወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎች ላይ እንዲሁም በወንዝና በወንዝ ዳርቻ እና በአካባቢው ደህንነት ላይ ብክለትና አሉታዊ ተፅዕኖዎችን በሚያስከትል ማንኛውም ሰው ላይ እንደሆነ በደንቡ አንቀፅ 3 ስር ሰፍሯል።

ደንቡ "የወንዝ ዳርቻ" ማለት ለወንዝ ዳርቻ መጠበቂያ ቢያንስ ከወንዙ ጠርዝ ግራና ቀኝ ዝቅተኛው 30 ሜትር ሆኖ፣ እንደ አካባቢው ሁኔታ አስተዳደሩ በሚወስነው መሠረት ስፋቱ ሊጨምር የሚችል ሲሆን፤ ለማንኛውም ዓይነት ግንባታ ወይም አገልግሎት እንዲውል የማይፈቀድ ቦታ እና በወንዙ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር ሥፍራን እንደሚያጠቃልል ይደነግጋል። በደንቡ ትርጉም ከተሰጠባቸው ቃላት መካከል "የወንዝና ወንዝ ዳርቻ ኮሪደር ልማት" የሚለው የሚገኝበት ሲሆን፤ ትርጉሙም ከወንዙ ተፋሰስ መነሻ ጀምሮ የሥነ-ምህዳር ጥበቃ፣ አረንጓዴ ልማት፣ መዝናኛ ቦታዎችን እና ተያያዥ አገልግሎቶችን ከወንዙ ኩታ-ገጠም የሆኑ አካባቢዎች ማልማት ሆኖ፣ ወሰኑና የመሬት አጠቃቀሙ በጥናት የሚወሰን መሆኑን ደንግጓል።

### 3.1. የተከለከሉ ተግባራት እና የሚያስከትሉት አስተዳደራዊ ቅጣት

በደንቡ አንቀፅ 7 መሠረት ወንዝና በወንዝ ዳርቻ ላይ የሚከተሉትን ተግባራት መፈጸም የተከለከለ ነው፡-

ከጤና ተቋማት፣ ከትምህርት ተቋማት፣ ከነዳጅ ማደያ፣ ከጋራዦች እና ከመኪና ማጠቢያዎች የሚወጡ የተለያዩ በካይ ኬሚካል ፍሳሽ ቆሻሻዎችን በወንዝና ወንዙ ዳርቻ ላይ ማከማቸት ወይም መጣል ወይም መልቀቅ፤ ይህን ተላልፎ የተገኘ ሰው 400 ሺህ ብር ይቀጣል።

ከመኖሪያ ቤት፣ ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና አምራች ድርጅቶች የሚወጡ ተረፈ ምርቶች፣ የጠርሙስ ስብርባሪ፣ አገልግሎታቸውን የጨረሱ ጣሳዎች፣ ፕላስቲክና የፕላስቲክ ከረጢቶች፣ ያገለገሉ የተሸከርካሪ ጎማዎች፣ የሞተ እንስሳት አካል፣ በድን፣ አጥንት፣ ፀጉር፣ ቆዳ፣ የግንባታና የሕንፃ ፍርስራሾች፣ ደረቅ ቆሻሻ እና ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸው በካዮች ወደ ወንዝ መድፋት ወይም መጣል የተከለከለ ሲሆን፤ ይህን ተላልፎ በተገኘ ግለሰብ ላይ 20 ሺህ ብር፣ ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ 100 ሺህ ብር ያስቀጣል።

ከመኖሪያ ቤት የሽንት ቤት ወይም ማንኛውም ያልተጣራ ፈሳሽ ቆሻሻ ወደ ወንዝ መልቀቅ ወይም መስመሩን አገናኝቶ ወንዙን መበከል ክልክል ሲሆን፤ ይህንን የተላለፈ ግለሰብ ላይ 150 ሺህ ብር፣ ድርጅት ሲሆን 300 ሺህ ብር ያስቀጣል።

ማንኛውንም ሰው ፈቃድ ሳይሰጠው ያልታከመ ፍሳሽን ወደ ወንዝ መልቀቅ የተከለከለ ሲሆን፤ ይህንን በሚተላለፉ ግለሰቦች ላይ 15 ሺህ ብር፣ እንዲሁም ድርጅቶች ላይ 40 ሺህ ብር ያስቀጣል።

ፍሳሽን ወደ ወንዝ ለመልቀቅ ፈቃድ ተሰጥቶት ቁጥጥር ሲደረግ የፍሳሽ የጥራት ደረጃዎችን ሳያሟላ እና የተከለከሉ ይዘቶችን የያዙ ፍሳሾችን መልቀቅ የተከለከለ ሲሆን፤ ይህንን ተላልፈው በሚገኙ ግለሰቦች እና ድርጅቶች ላይ እንደየ ሁኔታው ከ20 ሺህ ብር እስከ 400 ሺህ ብር የሚደርስ ቅጣት ይጣላል።

ማንኛውም በካይ ፍሳሽ ከተፈቀደው የፍሳሽ ማጠራቀሚያ ወይም የፍሳሽ መስመሩን ወደ ወንዝ ወይም ከጎርፍ መውረጃ ቦይ ጋር በማገናኘት ወደ ወንዝና ወንዝ ዳርቻ እንዲፈስ ማድረግ የተከለከለ ሲሆን፤ ይህንን ተላልፈው የሚገኙ ግለሰቦች 50 ሺህ ብር፣ ድርጅቶች ደግሞ 400 ሺህ ብር ይቀጣሉ።

ኬሚካል ነክ ፍሳሾችን ተገቢውን የማከሚያ ዘዴ ሳይጠቀሙና ባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ያለው አካል ሳያረጋግጥ ወደ ወንዝና ወንዝ ዳርቻ መድፋት ወይም መልቀቅ የተከለከለ ሲሆን፤ ይህንን ተላልፈው የሚገኙ ግለሰቦች 50 ሺህ ብር፣ ድርጅቶች ደግሞ 300 ሺህ ብር ይቀጣሉ።

ከአምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ማንኛውንም ያልታከመ ፈሳሽ ቆሻሻ ወደ ወንዝ በመልቀቅ ወይም መስመሩን በማገናኘት መበከል የተከለከለ ሲሆን፤ ይህንን ተላልፎ የተገኘ 300 ሺህ ብር ይቀጣል።

የሽንት ቤት ፍሳሽ የማስወገድ ፈቃድ ወስዶም ሆነ ሳይወስድ የሚሠራ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት በሚያስወግድበት ጊዜ ቀጥታ ወደ ወንዝ መድፋት ወይም መቀላቀል የተከለከለ ሲሆን፤ ይህንን ተላልፎ የተገኘ 1 ሚሊዮን ብር ይቀጣል።

በባህሪው አደገኛነት ያለው ደረቅም ሆነ ፈሳሽ ቆሻሻ ወደ ወንዝ መጣል ወይም እንዲጣል በማድረግ መበከል የተከለከለ ሲሆን፤ ይህንን ተላልፈው የሚገኙ ግለሰቦች



500 ሺህ ብር፣ ድርጅቶች ደግሞ 1 ሚሊዮን ብር ይቀጣሉ።

በወንዝና በወንዝ ዳርቻ ክልል ውስጥ መፀዳዳት ክልክል ሲሆን፤ ተላልፎ የተገኘ በ2 ሺህ ብር ይቀጣል።

የፍሳሽ ማጣሪያ ሳይኖረው በወንዝ ዳርቻ እና አካባቢ ላይ የተሽከርካሪ እጥበት ማከናወን የተከለከለ ሲሆን፤ ይህንን የተላለፈ በ400 ሺህ ብር ይቀጣል።

በወንዝ ዳርቻ ክልል ውስጥ እንስሳት ማሰማራት ወይም እንዲገቡ ማድረግ ወይም ከተፈቀደ መግቢያና መውጫ ውጪ ተሽከርካሪ ማሽከርከር የተከለከለ ሲሆን፤ ይህንን ተላልፎ የተገኘ በ30 ሺህ ብር ይቀጣል።

በወንዝና ወንዝ ዳርቻ ውስጥ ከተፈቀደው የመዝናኛ፣ መናፈሻና ፓርክ እና ሌሎች ለወንዝ ዳርቻው ልማት አስፈላጊ ከሆነ ግንባታ ውጪ የፕላስቲክ ቤት ወይም ማንኛውም ዓይነት ግንባታ መገንባት የተከለከለ ሲሆን፤ ይህንኑ መተላለፍ በ200 ሺህ ብር ያስቀጣል።

አስተዳደራዊ ቅጣት የተጣለበት ማንኛውም ሰው የተሰጠውን አስተዳደራዊ ቅጣት ማስታወቂያ ወረቀት በመያዝ ወዲያውኑ ጥፋቱ በተፈጸመበት አካባቢ በሚገኘው የወረዳው ደንብ ማስከበር ጽሕፈት ቤት ቀርቦ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መክፈያ ዘዴ በሦስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ቅጣቱን ገቢ ማድረግ ይኖርበታል፤ ቅጣቱ በተጠቀሰው ጊዜ ያልተከፈለ እንደሆነ የቅጣት መጠኑ እጥፍ ይሆናል (አንቀፅ 17(4) እና (7))።

ሌላው በወንጀል ሕግ እና በሌሎች ሕጎች የተመለከተው ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ እንደ አግባብነቱ ባለሥልጣኑ ወይም የከተማው አስተዳደር የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ይህንን ደንብ በተላለፈ ማንኛውም ሰው ላይ እንደ ጥፋቱ ሁኔታ ድርጊቱን የማስቆም፣ የማዘጋት፣ የማሸግ፣ ወደነበረበት ቦታ እንዲመለስ የማድረግ፣ የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም የግንባታ ፈቃድ እንዲሰረዝ የማድረግ፣ የውኃ አቅርቦት እንዲቋረጥ ስልጣን ላላቸው ተቋማት በጽሑፍ የማሳወቅ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል (አንቀፅ 17(1)(ሀ))።

በደንቡ አንቀፅ 18 መሠረት ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ክልከላዎች በመተላለፍ አስተዳደራዊ ቅጣት የተወሰነበትን ቅጣት ከፈጸመበት ቀን ጀምሮ በድጋሚ ተመሳሳይ ጥፋት የፈጸመ ማንኛውም ሰው የቅጣት መጠኑን በእጥፍ ይከፍላል። ማንኛውም ሰው የወንዝ ወይም የወንዝ ዳርቻ ብክለት አድርሷል ወይም ሊደርስ ይችላል የሚል ጥቆማ ወይም አቤቱታ ለከተማ አስተዳደሩ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በአካል፣ በጽሑፍ፣ በስልክ እንዲሁም በሌላ የኤሌክትሮኒክስ መልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴዎች ማቅረብ የሚችል መሆኑ በደንቡ አንቀፅ 15 ስር ተገልጿል።

### 4. የወንጀል ተጠያቂነት

የወንዞች ዳርቻ ልማት እና ብክለት መከላከል ደንብ ቁጥር 180/2017 በአዲስ አበባ የሚገኙ የወንዝ ዳርቻዎች ላይ ለሚከሰቱ ብክለቶች የተቀመጠውን የአስተዳደራዊ ቅጣት ሁኔታ የሚያመለክት ሲሆን፤ ነገር ግን ወንዞችን መበከል ከአስተዳደራዊ ቅጣት ባሻገር የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆኑን መገንዘብ ይገባል። በዚህ ረገድ ከሚጠቀሱ የሕግ ማዕቀፎች አንዱ የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995 ነው።

በዚህ አዋጅ አንቀፅ 16 መሠረት አንድ ሰው አዋጁን ወይም በሥሩ የሚወጡ ደንቦችን በመተላለፍ በካይን ወደ አካባቢ (የውኃ አካላትን ጨምሮ) በመልቀቅ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ፣ ከ1 ሺህ ብር በማያንስ እና ከ5 ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከ1 ዓመት በማያንስና ከ10 ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

ጥፋቱን የፈጸመው በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል (ድርጅት) ከሆነ ከ5 ሺህ ብር በማያንስና ከ25 ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ የሚቀጣ ሲሆን፤ የሥራ ኃላፊውም ከ5 ዓመት በማያንስና ከ10 ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም ከ5 ሺህ ብር በማያንስና ከ10 ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል። በሌላ በኩል የወንጀል ሕጉን አንቀፅ 517 የተመለከትን እንደሆነ፣ ማንም ሰው አስቦ ለሰው ወይም ለእንስሳ የሚያገለግለውን የመጠጥ ውኃ ለጤና ጎጂ በሆኑ ነገሮች የበከለ እንደሆነ፣ እንደ ሁኔታው እና እንደ ጉዳቱ መጠን በመቀጮ ወይም ከ1 ወር በማያንስ ቀላል እስራት፣ ወይም ወንጀሉ ከባድ በሆነ ጊዜ ከ7 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል። ወንጀሉ የተፈጸመው የውኃ ጉድጓዶችን፣ ማጠራቀሚያዎችን፣ ምንጮችን፣ የውኃ ኩሬዎችን፣ ወንዞችን ወይም ሐይቆችን አስቦ በመመረዝ እንደሆነ ቅጣቱ ከ15 ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እስራት ይሆናል። ይህም በአዋጅ ቁጥር 300/1995 አንቀፅ 16 ከተቀመጠው የቅጣት መጠን ከፍ የሚል በመሆኑ፣ ተመሳሳይ ለሆነ ድርጊት በአፈጻጸም ረገድ ጥፋተኞች ላይ ሊተገበር የሚገባው የወንጀል ሕጉ የቅጣት መጠን ይሆናል (የአዋጅ ቁጥር 300/1995 አንቀፅ 12(3))። ሌላው በወንጀል ሕጉ የተጠቀሰው ድርጊት የተፈጸመው በቸልተኛነት ከሆነ በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ እንደሚያስቀጣ ተደንግጓል።

ወንዞችን መበከል ከፍ ሲል በዝርዝር ከተቀመጡት የአስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች ባሻገር፣ የድርጊቱን ፈጻሚዎች ለሚያደርሱት ጉዳት ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ እንዲከፍሉ የሚያስችል ከውል ውጪ ኃላፊነት የሚመነጭ የፍትሐብሔር ተጠያቂነትም የሚያስከትል መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል።

አሁን ላይ በስፋት ወደ ልማት ኮሪደርነት እየተቀየሩ የሚገኙት ወንዞች ለአካባቢ ጥበቃ፣ ለማኅበረሰብ ጤንነትና ለሀገር ኢኮኖሚ ከሚያስገኙት በጎ ፋይዳ ባሻገር፣ ለከተሞች የሚሰጠው ውበትና መልካም ገፅታ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ዜጎችን የሚጠቅሙ ሥራዎች በመሆናቸው ሁሉም ዜጋ ሊንከባከባቸውና ሊጠብቃቸው ይገባል። ከዚህ ባሻገር በእነዚህ የሀገር ሀብቶች ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ግለሰቦችና ድርጅቶች በሚኖሩ ጊዜ ተገቢውን ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይገባል።



ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል
Gullele Botanic Garden

## በተፈጥሮ እቅፍ ውስጥ ከከዋክብት ጋር አዳር፦
## በጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል

**በከተማው ጫጫታ ደክሞዎታል?** ከሲሚንቶ ህንፃዎች መሀል ወጣ ብለው፣ አዲስ መንፈስ እና ልዩ ትውስታ የሚፈጥር የዱር አዳር (Camping) ልምድን በጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል ያዳብሩ ፡፡ ለነፍስዎ እረፍት፣ ለሥጋዎ ደግሞ አዲስ ጉልበት የሚሰጥ ልዩ የዱር አዳር መርሃ-ግብር ያገኛሉ፡፡

### በጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል ለምን ያድራሉ?

ማዕከላችን ለዱር አዳር ተብለው የተመረጡ፣ እጅግ ውብ እይታ ያላቸውና ሰላማዊ ቦታዎችን በማዘጋጀት የናፈቁትን የተፈጥሮ መስተንግዶ ያቀርባል።

- አስደናቂ እይታ፦ የሌሊቱን የከዋክብት ውበትና የማለዳውን የፀሐይ ብርሃን በተለየ ድባብ ለመታደም።
- ፍጹም ሰላም፦ ከከተማው ጩኸት ርቀው፣ በቅጠሎች ሽውሽውታና በአዕዋፋት ዝማሬ ለመንቃት።
- አስተማማኝ ምቾት፦ ለደህንነትዎ ቅድሚያ የሚሰጡ፣ ለካምፒንግ ምቹ እና ለዓይን ማራኪ የሆኑ ስፍራዎች።

### ለሁሉም የሚሆን ልዩ ጊዜ

ለብቻዎ ጸጥታን ለብሰው ለማንበብ፣ ከጓደኞችዎ ጋር በደመቀ ጨዋታ ለመዝናናት፣ ወይም ከቤተሰብዎ ጋር የማይረሳ ጊዜ ለማሳለፍ የእኛ "የዱር አዳር" አገልግሎት ምርጫዎ ያድርጉን።

ኑ! በተፈጥሮ እቅፍ ውስጥ አድራችሁ አዲስ ጉልበት ሰንቁ። ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል (አዲስ አበባ)
ቦታ፦ ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል (አዲስ አበባ)
**ለበለጠ መረጃ፦** (0937806711 ፣ 09 11 79 93 85 ወይም 0904616798 ይደውሉ)

## የግልጽ ጨረታ የግዥ ማስታወቂያ
### ጨረታ መለያ ቁጥር 002/2018 ዓ.ም

- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 ፋይናንስ ጽ/ቤት ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ሎት፡-1. የጽዳትዕቃዎች፣ ሎት፡-2. የደንብ ልብስ፣ ሎት፡-3. የኪራይ አገልግሎት (መኪና እና ድንኳን ኪራይ አገልግሎት) በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ በዚህ መሰረት ጨረታውን ለመሳተፍ የሚፈልጉ ሕጋዊ ተጫራቾች የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡

1. ተጫራቾች በዘርፉ የተሰማሩበት ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸውና የዘመኑን ግብር ለመከፈላቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ
2. በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በአቅራቢነት የተመዘገቡና ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ
3. የታደሰ ንግድ ፈቃድ ያለው
4. ተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል
5. ተጫራቾች ከዚህ በታች የተጠቀሰውን የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ C.P.O ማቅረብ አለባቸው፡፡

| የሎት ቁጥር | የሎት ዝርዝር | የተጠቀሰው የጨረታ ማስከበሪያ ሲፒኦ በኢትዮጵያ ብር |
|---|---|---|
| ሎት-1 | የጽዳት ዕቃዎች | 10000.00 |
| ሎት-2 | የደንብ ልብስ | 10000.00 |
| ሎት-3 | የኪራይ አገልግሎት (መኪና እና ድንኳን ኪራይ አገልግሎት) | 10000.00 |

6. የጨረታ ሰነዱን ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ በየሎቱ የማይመለስ ብር 300 / ሶስት መቶ ብር/ በመክፈል የተዘጋጀውን ሰነድ ከተቋሙ ቢሮ ቁጥር 305 እየቀረቡ መግዛት ይቻላል፡፡
7. ተጫራቾች ጨረታው ከወጣበት ቀን አንስቶ ባሉት 10 ( አስር ) ተከታታይ የስራ ቀናት ቢሮ ቁጥር 5 ድረስ በመምጣት ዋጋው የተሞላበትን የጨረታ ሰነዱን ዋናውንና ፎቶ ኮፒ ለየብቻው በማሸግ ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡
8. ጨረታው በ11ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ታሽጎ በዛው በ11ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡ የጨረታው መዝጊያና መክፈቻ ቀን የስራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተሰጠው ተመሳሳይ ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
9. ተጫራቾች ያሸነፉበትን ዋጋ የውል ማስከበሪያ 10% ማስያዝ አለባቸው፡፡
10. ተጫራቾች ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ለሚወዳደሩበት ናሙና ለሚቀርብባቸው ዕቃዎች ናሙና ማቅረብ እና በተጨማሪ የቢሮ መስተንግዶ አገልግሎት ለምትጫረቱ ነጋዴዎች ናሙና ለሚያስፈልጋቸው ዕቃዎች ናሙና ማቅረብ አለባችሁ፡፡ ናሙና የማይቀርብባቸው ቋሚ ዕቃዎች መስሪያ ቤቱ ባቀረበው ስፔስፊኬሽን መሰረት መቅረብ አለባቸው፡፡
11. የጨረታው አሸናፊ ድርጅት ያሸነፈበትን ዕቃ በራሱ ትራንስፖርት መ/ቤቱ ድረስ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
12. መ/ቤቱ ለጨረታው ከቀረበው ዕቃ እስከ 20% የመቀነስ ሆነ የመጨመር መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
13. መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ተጨማሪ ማብራሪያ ካስፈለገ በአካል በመቅረብ ከመገናኛ ወደ 24 ቀበሌ ኮከብ ህንፃ አጠገብ ወረዳ 05 አስተዳደር በመቅረብ 3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 305 ፋ/ጽ/ቤት መጠየቅ ይቻላል። ስልክ ቁጥር፡-09-05-60-96-79**

**ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 05 አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤት**

---

አመልካች በአራዳ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 01 ቀበሌ 03 በአዲሱ ወረዳ 05 የቤት ቁጥር 534 በወ/ሪት ሉሊት ገዛኸኝ ማሩ ስም የወጣው ቁጥሩ 33065 በቀን 17/11/83 ዓ.ም ወጭ የሆነና በካርታው ጀርባ ላይ በ7/7/2001 ዓ.ም ስም የዞረ ኦርጂናል ካርታ ስለጠፋባቸው በምትኩ ካርታ ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው 11/06/2018 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቋል፡፡

በመሆኑም የጠየቁትን አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሰው የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ አራዳ ክ/ከ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ እንዲያቀርቡ እያሳወቅን ካልቀረቡ ግን የጠየቁትን አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአራዳ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር የካ/ማ/13/0018719/00 ሴሪ ቁጥር 1512962 በአቶ መኮንን ለሚ ኢርጳ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የኮንደሚኒየም ቤት እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማይቀርብ ከሆነ በምትኩ መመሪያው በሚፈቅደው መሠረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በወ/ሮ ደብረወርቅ ኦላና ኤባ አድራሻው ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 08 የቤት ቁጥር 018/151 መለያ ቁጥር ል.08/6539/00 ሴሪ ቁጥር 048145 የሆነ ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ ታውጆ አገልግሎት እንዲሰጣቸው አመልክተዋል። በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሰው ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳዮቹ ስም የተመዘገበውን ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጂናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝበባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአሰለፈች ወልዴ ገብረወልድ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 02 የሚገኘው በይዞታ ካርታ ቁጥር AA000080203104 በሴሪ ቁጥሩ 050051 በስማቸው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ / ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ካርታ ቁጥር 344965 በሴሪ ቁጥር 025512 መሀመድ ሞሳ የተመዘገበ ይዞታ ማህደራቸው ከማህደር ክፍላችን መገኘት የነበረበት የጠፋባቸው ስለሆነ ማህደሩን የያዘ ግለሰብ ካለ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ እንድታሳውቁን እናሳውቃለን።

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

### ጉዳዩ፡- ማስታወቂያ እንዲወጣ ስለመጠየቅ

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ካርታ ቁጥር 344964 በሴሪ ቁጥር 025511 ሳውዳ መሀመድ አብደላ የተመዘገበ ይዞታ ማህደራቸው ከማህደር ክፍላችን መገኘት የነበረበት የጠፋባቸው ስለሆነ ማህደሩን የያዘ ግለሰብ ካለ በማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ እንድታሳውቁን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማት አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# የቅጥር ማስታወቂያ

**የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከዚህ በታች በተገለፁት ክፍት የስራ መደቦች ላይ አመልካቾችን አወዳድሮ ለመቅጠር ይፈልጋል።**

| ተ.ቁ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ | አግባብ ያለው የሥራ ልምድ | የሙያ ዓይነት | መደብ መታወቂያ ቁጥር | ብዛት | የቅጥር ሁኔታ | ደመወዝ | የሥራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **የዲጂታል ሚዲያና ህትመት ዘርፍ በድጋሚ የወጣ** | | | | | | | | | | |
| 1 | ብራንድ ቪዥዋሊስት (የግራፊክስ ባለሙያ) | XII | ኮሌጅ ዲፕሎማ፣ ቢ. ኤስ.ሲ፣ ለኤም.ኤስ.ሲ | 6/4/2 ዓመት | ኮምፒውተር ሳይንስ፣ ኮምፒውተር አፕሊኬሽን፣ ኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ፣ ኮምፒውተር ኢንጂነሪንግ፣ ኢንፎርሜሽን ሲስተም፣ ሲነማቶግራፊ ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፍ | አ/18.269 | 1 | በቋሚነት | በ ተ ቋ ሙ ስ ኬ ል መሰረት | አ ዲ ስ አበባ |
| 2 | ከፍተኛ ኤዲት ፍሎው ስትራቴጂስት (ምስልና ድምፅ ቅንብር ባለሙያ) | XII | ኮሌጅ ዲፕሎማ፣ ቢ . ኤ ስ . ሲ ፣ ለኤም.ኤስ.ሲ | 6/4/2 ዓመት | ኮምፒውተር ሳይንስ፣ ኮምፒውተር አፕሊኬሽን፣ ኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ፣ ኮምፒውተር ኢንጂነሪንግ፣ ኢንፎርሜሽን ሲስተም፣ ሲነማቶግራፊ ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፍ | አ/18.1166 | 1 | በቋሚነት | በ ተ ቋ ሙ ስ ኬ ል መሰረት | አ ዲ ስ አበባ |
| 3 | የማህበራዊ ሚዲያ አዘጋጅ | XII | ቢ..ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 7/5 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን፣በሀገር ውስጥ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ፣በውጭ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ፣በቲያትርካል አርት፣ በፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣የሚዲያ ጥናት፣ሥራ አመራር እና ቢዝነስ አስተዳደር ወይም በተዛማጅ የማህበራዊ ሳይንስ የትምህርት ዘርፍ | አ/18.262 እና አ/18.263 | 2 | በቋሚነት | በ ተ ቋ ሙ ስ ኬ ል መሰረት | አ ዲ ስ አበባ |
| 4 | የዩቲዩብ አዘጋጅ | XII | ቢ..ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 7/5 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን፣በሀገር ውስጥ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ፣በውጭ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ፣በቲያትሪካል አርት፣ በፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣የሚዲያ ጥናት፣ሥራ አመራር እና ቢዝነስ አስተዳደር ወይም በተዛማጅ የማህበራዊ ሳይንስ የትምህርት ዘርፍ | አ/18.267 | 1 | በቋሚነት | በ ተ ቋ ሙ ስ ኬ ል መሰረት | አ ዲ ስ አበባ |
| 5 | ክርኤቲቭ ሊድ አርክቴክት | XII | ቢ..ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 7/5 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ፣ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በስነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.1130 | 1 | በቋሚነት | በ ተ ቋ ሙ ስ ኬ ል መሰረት | አ ዲ ስ አበባ |
| **ለሬዲዮ ዘርፍ** | | | | | | | | | | |
| 6 | የሬድዮ ስፖርት ሪፖርተር | IX | ቢ..ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 3/1 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በስነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.218 | 1 | በቋሚነት | በ ተ ቋ ሙ ስ ኬ ል መሰረት | አ ዲ ስ አበባ |
| 7 | የሬዲዮ ዜና እና ሾዎ አቅራቢ | | ቢኤ ዲግሪ | 0ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ፣ በውጭ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ወይም በተዛማጅ የማህበራዊ ሳይንስ የትምህርት ዘርፍ | -- | 3 | በፊሊ.ራንስ | በ ተ ቋ ሙ ስ ኬ ል መሰረት | አ ዲ ስ አበባ |
| **የሀብት አስተዳደር ዘርፍ (በድጋሚ የወጣ)** | | | | | | | | | | |
| 8 | ሜካፕ አርቲስትና አልባሳት ተቆጣጣሪ | VIII | ኮሌጅ ዲፕሎማ፣ ቢ.ኤ ዲግሪ | 4/2 ዓመት | በሥነ ጥበብና ዲዛይን ወይም በተዛማጅ የትምህርት ዘርፍ | አ/18.875 | 1 | በቋሚነት | በ ተ ቋ ሙ ስ ኬ ል መሰረት | አ ዲ ስ አበባ |
| 9 | ጥበቃ | II | 12/10 ክፍል ያጠናቀቀ | 2 ዓመት የ መ ሳ ሪ ያ አ ፈ ታ ት ና አ ጠ ቃ ቀ ም ች ሎ ታ ያለው/ያላት | ቀለም | | 6 | በኮንትራት | በ ተ ቋ ሙ ስ ኬ ል መሰረት | አ ዲ ስ አበባ |

**ማሳሰቢያ:-**

1. አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10/አስር/ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የትምህርት ማስረጃችሁን ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ በመያዝ በተቋሙ የሰው ኃብት ሥራ አመራር እና ልማት ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 05 ድረስ በመምጣት እንድትመዘገቡ እናሳስባለን፡፡
2. ከግል ድርጅቶች የሚቀርብ የስራ ልምድ ማስረጃ የስራ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ማስረጃ መምጣት ይኖርበታል፡፡
3. የስራ ልምድ የሚጠይቀው ከወጣው ክፍት መደብ ጋር ቀጥተኛ መሆን አለበት፡፡
4. በቴክኒክና ሙያ/ሌቭል የሚወዳደሩ የብቃት ማረጋገጫ/COC ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. የምዝገባው ቀን ከየካቲት 16 ቀን 2018 ዓ.ም እስከ የካቲት 27 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ ነው፡፡
6. የፈተና ቀን በውስጥ ማስታወቂያ ይገለፃል፡፡
7. ለበለጠ መረጃ አድራሻ አምስት /5/ ኪሎ ቅድስተ ማርያም ፊት ለፊት ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጐን ስልክ 0111551848

## አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ

# ኪነ ጥበባዊ ድግሶች

**በጊዜው አማረ**

በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች እና አዳዲስ ጥበባዊ ሥራዎች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል፡፡ ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም የተለያዩ ጥበባዊ መሰናዶዎች ይደረጋሉ፡፡ ከተሰናዱ ዋና ዋና ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች መካከል የሐሳብ እና ንባብ ውይይት፣ የሥዕል አውደ ርዕይ፣ የመጽሐፍት ምረቃ፣ የቴአትር መርሃ ግብር እና ሌሎች መሰናዶዎች ይገኙበታል፡፡ ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

## መጽሐፍት

“እንዲህም ተኑሯል” መጽሐፍ በዛሬው ዕለት ይመረቃል፡፡ ከ21 በላይ መጻሕፍትን ለንባብ ያበቃው ጋዜጠኛና ደራሲ አበራ ለማን የሕይወት ታሪክ የያዘው ይህ መጽሐፍ ዛሬ በብሔራዊ ቤተ መጻሕፍትና ቤተ መዛግብት የምረቃ መርሃ ግብሩ ይከናወናል፡፡ መጽሐፉ የደራሲውን የሕይወት ውጣ ውረድ፣ በኢትዮጵያ ሬዲዮና ፕሬስ መምሪያዎች የነበረውን ቆይታ እንዲሁም የሥነ-ጽሑፍ ጉዞውን በሰፊው ይዳስሳል።

በሌላ መረጃ “ABINA” የተሰኘ የአፋርኛ ሰዋሰው መጽሐፍ ለንባብ በቅቷል። የአፋርኛ ቋንቋ ሰዋሰው ክፍሎችን በተገቢው ሁኔታ እንዳካተተ የተነገረለት ይህ መጽሐፍ በአሊ አብዱልቃድር መዘጋጀቱ ተሰምቷል፡፡ አዘጋጁ ካሁን ቀደም የአፋርኛ ቋንቋ ድምጾችን፣ ምዕላዶችን እና የቋንቋን ጠባያት የሚተነትኑ መጽሐፍትን በማሳተም ለአንባብያን አድርሷል፡፡

## መታሰቢያና የኪነ ጥበብ ውይይት


የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ሥነ ጥበባት ማዕከል፣ የሎሬት ጸጋዬ ገብረመድኅንን 20ኛ ዓመት የዕረፍት መታሰቢያ ዝግጅት ዛሬ ያካሄዳል፡፡

በዝግጅቱ ላይ የባህልና ስፖርት ሚኒስትር ዴኤታ ነብዩ ባዬ የሎሬት ጸጋዬ ቴአትሮች ላይ ዳሰሳ ያቀርባሉ፡፡ ወንድወሰን አዳነ (የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሥነ ጽሑፍ መምህርና ረዳት ፕሮፌሰር) ግጥሞቹን ይተነትናል፡፡ የሥነ ጽሑፍ ሐያሲው ቴዎድሮስ አጥላው በጸጋዬ ሕይወት ዙሪያ የተጻፈውን “ምጥቀት በቅኔ አክናፍ” የተሰኘው መጽሐፍ ላይ ዳሰሳ ያቀርባል ተብሏል፡፡

መርሃ ግብሩ የሚካሄደው የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ቅጥር ግቢ (ጳውሎስ ሆስፒታል አካባቢ) ንግድ ባንክ ጉለሌ ቅርንጫፍ አለፍ እንዳሉ ሲሆን ሰዓቱ 8፡00 ሰዓት ነው፡፡

## የንባብና የሐሳብ ውይይት

በዛሬው ዕለት “ንባብ እና ዲጂታል ኤጅ” በሚል ሐሳብ ውይይት ይደረጋል። ውይይቱ የሚደረገው ዛሬ ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ጀምሮ ሲሆን፤ የውይይት መነሻ ሐሳብ የሚያቀርበው ደራሲ ቡርሃን አዲስ (መሐመድ አሊ ቡርሃን) ነው፡፡ ውይይቱ የሚደረገው ደግሞ 4 ኪሎ ኢክላስ ሕንፃ ዋልያ መጻሕፍት አዳራሽ ነው፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

በከተማችን ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

## የሥዕል አውደ ርዕይ

7 ሰዓሊያን የተሳተፉበት “ዓድዋ” የተሰኘ የቡድን የሥዕል አውደ ርዕይ በእይታ ላይ ይገኛል፡፡ አውደ ርዕዩን ያዘጋጁት አኑማ ኃይሉ፣ የሱቃል ተስፋዬ፣ ዮርዳኖስ ውቤ፣ እዮብ እሸቱ፣ ሱራፌል ከተማ፣ ዮዲት ወልደማርያም እና ዘካሪያስ ከተማ ናቸው፡፡ ፈንድቃ የባህል ማዕከል እና ሀያት ረጀንሲ ሆቴል በመተባበር ያዘጋጁት ይህ መርሃ ግብር እስከ የካቲት 30 ቀን 2018 ዓ.ም በእይታ ላይ ይቆያል፡፡

## የቡና ፌስቲቫል

በዛሬው የኢትዮጵያ የቡና ባህል ቀን ፌስቲቫል በዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ይካሄዳል፡፡ ኢትዮጵያ የቡና መገኛ ብቻ ሳትሆን፣ ለዓለም ልዩ የሆነ የቡና ሥነ-ሥርዓት ባህል ያበረከተች ሀገር ናት። ይህንን የቆየ ማኅበራዊ መስተጋብር ለማክበርና ይበልጥ ለማስተዋወቅ የተዘጋጀው ፌስቲቫል ዛሬ ለ2ኛ ጊዜ ይካሄዳል፡፡ ዋና ዓላማውም ከመዝናናት ባለፈ የሀገራችንን የቡና ሥነ-ሥርዓት ባህል ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ፣ ለዓለም ለማስተዋወቅና በዩኔስኮ (UNESCO) የማይዳሰስ ቅርስ ሆኖ እንዲመዘገብ ግፊት ለማድረግ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

## የቴአትር መርሃ ግብር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ። ቅዳሜ ከ11፡30 ሰዓት ጀምሮ “12ቱ እንግዶች” ቴአትር ይታያል፡፡ እሁድ በ7፡30 ሰዓት “ንጉሥ አርማህ” ቴአትር፣ እንዲሁም “እምዬ ብረቷ” የተሰኘው ቴአትር በ11፡30 ሰዓት ላይ ይታያሉ፡፡ በብሔራዊ ቴአትር በሌሎች ቀናት ደግሞ ሐሙስ 11፡30 ሰዓት “ሽምጋይ” እንዲሁም አርብ 11፡30 ሰዓት “ዴጊያ” ቴአትር ለእይታ ይበቃሉ፡፡

# የቁጥር ጨዋታ


## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ከታች በኩል በስተግራ የሚገኘው (6×2)+9=21 ይሆናል፡ ፡ከታች በኩል በስተቀኝ የሚገኘው ደግሞ (3×7)+1=22 ነው፡፡ በዚህ ስሌት መሰረት (5 × 8) + 3=43 ይሆናል፡፡ ስለዚህ ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛ ቁጥር **43** ነው፡፡




## የዛሬው የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# ኢትዮጵያን የመጎብኘት ጉጉት

**በጊዜው አማረ**

ኢትዮጵያ የረጅም ዘመን ታሪክ፣ የራሷ ፊደልና ባህል ያላት ሀገር እንደመሆኗ መጠን የኪነ ጥበብ ታሪኳም ከማንነቷና ከጥንታዊነቷ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው። ከዋሻ ስዕል እስከ አብያተ ክርስቲያናት የግድግዳ ድንቅ ስራዎች፣ ከባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች እስከ ዘመናዊው ሲኒማ ድረስ የኢትዮጵያ ኪነ ጥበብ የሕዝቧን እምነት፣ ጀግንነትና ማኅበራዊ ሕይወት እየዘከረ እና እያወሳ ዛሬም ድረስ ቀጥሏል። ይህች ጥንታዊት ሀገር ከድንጋይ ላይ ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት እስከ ብራና መጻሕፍት፣ ከቅዱስ ያሬድ ዜማ እስከ ዘመናዊው የኢትዮ-ጃዝ (Ethio-Jazz) ድረስ የዘለቀ ጥልቅ የጥበብ አሻራ አላት። ይህ ጥበብ የሀገሪቱ መልክ፣ ማንነትና ነጻነት መገለጫም ነው። በዚህም ለመላው የጥቁር ሕዝቦች ኩራት መሆን ችላለች።



ፎቶ- ከገፀ ድር

ዲዲጂ እና ጓደኞቹ የኢትዮጵያን ምግቦች በመመገብ ለዓለም አስተዋውቀዋል

ኢትዮጵያ ለጥቁር ሕዝቦች ያላት ትርጉም ከድንበር የዘለለ ነው። በቅኝ ግዛት ዘመን የአፍሪካ ሀገራት በቅኝ ግዛት ቀንበር ስር ሲወድቁ፣ ኢትዮጵያ በነጻነቷ ጸንታ መቆም መቻሏ ለጥቁሮች ሁሉ የኩራትና የተስፋ ብርሃን ሆኖ አገልግሏል። ይህ እውነት ታዋቂው የዲጂታል ዓለም ተጽዕኖ ፈጣሪ አይሾው ስፒድ ኢትዮጵያን በጎበኘ ወቅት በገሃድ ታይቷል።

በእርግጥም በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተከታዮች ያሉት ወጣቱ አሜሪካዊ የዲጂታል ይዘት ፈጣሪ ዳረን ዋትኪንስ (በቅጽል ስሙ አይሾው ስፒድ - IShowSpeed) ወደ ኢትዮጵያ ያደረገው ጉብኝት ታሪካዊ ነበር ማለት ይቻላል። ይህ ጉብኝት ከተለመደው የቱሪስት ጉብኝት ባለፈ፣ የኢትዮጵያን ባህል፣ ታሪክና ዘመናዊ ገጽታ ለዓለም ጥቁር ሕዝቦችና ለጥበብ ሰዎች አዲስ መነቃቃትን ፈጥሯል።

የስፒድን ጉብኝት ተከትሎ በርካታ ተዋንያን፣ ታዋቂ ሙዚቀኞችና የዲጂታል ዓለም ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ኢትዮጵያን ለመጎብኘት ያላቸውን ጉጉት እየገለጹ ይገኛሉ። በተለይ በአሜሪካና በአውሮፓ የሚኖሩ ጥቁር አሜሪካውያን ኢትዮጵያን የታሪካቸው ምንጭ አድርገው ማየታቸው ለየት ያለ ስሜት ፈጥሮባቸዋል። ከእነዚህ ሰዎች ውስጥ አንዱ ታዋቂው አሜሪካዊ የራፕ ሙዚቃ ባለሙያ ዲዲጂ (DDG) ነው።

## ዲዲጂ (DDG) ማን ነው?

ሙሉ ስሙ ዳሪል ድዌይን ግራንቤሪ ጁኒየር ነው። ዓለም የሚያውቀው ግን ዲዲጂ (DDG) በሚለው የመድረክ ስሙ ነው። ይህ ሰው ታዋቂ አሜሪካዊ ራፐር፣ የዘፈን ግጥም ጸሐፊ እና የዲጂታል ሚዲያ ተጽዕኖ ፈጣሪ ነው።

የዘር ሀረጉ ከአፍሪካዊቷ ሀገር ናይጀሪያ የሚመዘዝ ሲሆን፣ የተወለደው በፈረንጆቹ ጥቅምት 10 ቀን 1997 በፖንቲያክ፣ ሚቺጋን ነው። ትምህርቱን በፖንቲያክ አካዳሚ ተከታትሏል። ዳሪል ገና በልጅነቱ በትምህርቱ ጎበዝ የነበረ ሲሆን፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ከክፍሉ አንደኛ በመሆን አጠናቅቋል።

ከዚያም ወደ ሴንትራል ሚቺጋን ዩኒቨርሲቲ አምርቶ የነበረ ቢሆንም፣ ወዲያው ወደ ሙዚቃና ዲጂታል ሚዲያ ፊቱን አዞረ። ይህ ውሳኔ ዛሬ ለደረሰበት ስኬት የመሠረት ድንጋይ መሆኑን ይናገራል። የDDG ጉዞ የጀመረው እ.ኤ.አ. በ2014 ቪዲዮዎችን በዩቲዩብ ላይ በመልቀቅ ነበር። መጀመሪያ ላይ ቀልዶችን፣ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎችን እና ፈተናዎችን በማቅረብ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተከታዮችን አፈራ። ሆኖም ግን የልጅነት ሕልሙ ሙዚቃ ነበር።

እ.ኤ.አ. በ2018 በለቀቀው "Givenchy" የተሰኘ ነጠላ ዜማ በዩቲዩብ ከፍተኛ እይታን በማግኘቱ በሙዚቃው ዓለም ትኩረት እንዲስብ አደረገው። በዚህም ከታዋቂው "Epic Records" የሙዚቃ ኩባንያ ጋር ውል ተፈራረመ። በዚህ ሳይገደብ የራሱን የሙዚቃ ተቋም በማቋቋም ወጣት ተሰጥኦዎችን ማበረታታት ጀመረ።

በአሁኑ ዘመን የኪነ-ጥበብ ዓለም በዲጂታል ሚዲያና በባህላዊው የሙዚቃ ኢንዱስትሪ መካከል ያለው መስመር እየቀጠነ መጥቷል። የዚህ ለውጥ ዋነኛ ማሳያ ደግሞ ዳሪል ድዌይን ግራንቤሪ ጁኒየር ወይም በቅጽል ስሙ DDG ነው ይላሉ በርካቶች። ምክንያቱ ደግሞ ከማኅበራዊ ሚዲያ ተጽዕኖ ፈጣሪነት ተነስቶ የቢልቦርድ ሰንጠረዦችን እስከመምራት የዘለቀው ጉዞው ለብዙ ወጣቶች አርአያ በመሆኑ ነው።

በሙዚቃ ስራውም፡-
ወጣት ነኝ አቅም ያለኝ
ሀብታም እና ጥቁር ነኝ
የስኬት መንገዴን መቀጠል አለብኝ
እናም በፍጹም
ወደ ኋላ አልመለስም... ይላል በጥቁርነቱ የሚኮራውና ለበርካቶች ድምጽ መሆን የቻለው ይኸው ወጣት።

> **የዲዲጂ መምጣት በተለይ ለወጣቱ ትውልድ እና ለሙዚቃው ኢንዱስትሪ ትልቅ አጋጣሚ ነው። አርቲስቱ ከሙዚቃ ስራው ባለፈ በዩቲዩብ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተከታዮች ያሉት በመሆኑ፣ የእሱ ጉብኝት ሌላ ተጨማሪ የዓለም አቀፍ ሚዲያ ትኩረትን ይስባል። ይህም ለኢትዮጵያ ቱሪዝምና አዲስ ገጽታ ሌላ መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል**

ዳሪል ድዌይን ግራንቤሪ (DDG) ከአንድ ተራ ቪዲዮ ቀራጭነት ተነስቶ ዓለም አቀፍ ዝናን ያተረፈ የሙዚቃ ኮከብ ለመሆን የበቃው በጠንካራ ስራውና በፈጠራ ብቃቱ ነው። ወጣቱ ራፐር ለዲጂታል ዘመን ወጣቶች "ሕልምን እውን ለማድረግ ገደብ የለም" የሚል ሕያው ምስክር ነው። ዲዲጂ ለኢትዮጵያና አፍሪካ ልዩ ፍቅር ያለው ወጣት አርቲስት ነው። የናይጀሪያው "ዘ ኔሽን" ጋዜጣ ባሳለፍነው የፈረንጆቹ 2025 እንደዘገበው፣ የራፕ ሙዚቃ ባለሙያው አሜሪካን በመተው ኑሮውን አፍሪካ ለማድረግ ዕቅድ አለው።

## የዲዲጂ ኢትዮጵያን የመጎብኘት ዕቅድ

ታዋቂው አሜሪካዊ ዩቲዩበር እና የቀጥታ ስርጭት ባለሙያ ዳረን ዋትኪንስ ጁኒየር ወይም በቅጽል ስሙ አይሾው ስፒድ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት፣ በሀገሪቱ የቱሪዝም እና የገጽታ ግንባታ ታሪክ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ ከፍቷል። ይህ ጉብኝት ኢትዮጵያን ለዓለም ከማስተዋወቅ ባለፈ፣ እንደ ዲዲጂ (DDG) ያሉ ሌሎች ታዋቂ አሜሪካውያን አርቲስቶች ዓይናቸውን ወደ ኢትዮጵያ እንዲያዞሩ አድርጓል።

የአይሾው ስፒድ ቪዲዮዎች ዓለምን ባጥለቀለቁ ማግስት፣ ሌላኛው ዝነኛ አሜሪካዊ ራፐር እና የዩቲዩብ ኮከብ ዳሪል ድዌይን ግራንቤሪ (DDG) ትኩረቱን ወደ ኢትዮጵያ አድርጓል። ዲዲጂ በማኅበራዊ ሚዲያ ገጾቹ ላይ ባሰፈረው መልዕክት፣ የስፒድን ቆይታና የኢትዮጵያውያንን እንግዳ ተቀባይነት ካየ በኋላ ሀገሪቱን ለመጎብኘት ከፍተኛ ጉጉት እንዳደረበት ገልጿል።

ዲዲጂ በቅርቡ ወደ ኢትዮጵያ እንደሚመጣ የገለጸ ሲሆን፣ ይህም በኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍ ላይ "የታዋቂ ሰዎች ተከታታይ ጉብኝትን" እየተፈጠረ መሆኑን ያሳያል። የዲዲጂ መምጣት በተለይ ለወጣቱ ትውልድ እና ለሙዚቃው ኢንዱስትሪ ትልቅ አጋጣሚ ነው። አርቲስቱ ከሙዚቃ ስራው ባለፈ በዩቲዩብ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተከታዮች ያሉት በመሆኑ፣ የእሱ ጉብኝት ሌላ ተጨማሪ የዓለም አቀፍ ሚዲያ ትኩረትን ይስባል። ይህም ለኢትዮጵያ ቱሪዝምና አዲስ ገጽታ ሌላ መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል።

በዓለም አቀፍ የሙዚቃ ኢንዱስትሪ ውስጥ ስመ ጥር የሆነው አሜሪካዊው ራፐር፣ ዩቲዩበር እና ስራ ፈጣሪ ዳሪል ድዌይን ግራንቤሪ (DDG)፣ ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት ያለውን ጽኑ ፍላጎት በይፋ የማኅበራዊ ትስስር ገጹ መግለጹ በመላው ዓለም በሚኖሩ ጥቁሮችና ትውልደ አፍሪካውያን እንዲሁም ኢትዮጵያውያን ዘንድ ትልቅ መነቃቃትን ፈጥሯል። ዲዲጂን ከሌሎች አርቲስቶች ለየት የሚያደርገው፣ ስለ ኢትዮጵያ ያለው ፍቅርና የመጎብኘት ፍላጎት ዛሬ የተጀመረ ሳይሆን፣ ከዚህ ቀደምም በባህሏና በእስክስታዋ እንደሚማረክ በተደጋጋሚ ሲገልጽ የነበረ ሰው መሆኑ ነው።

የዲዲጂ (DDG) የኢትዮጵያ ፍቅር በ"እስክስታ" ተጀምሮ ዛሬ ላይ በታላቅ ጉጉትና በይፋዊ የጉብኝት ተስፋና ፍላጎት ጫፍ ላይ ደርሷል። አይሾው ስፒድ የከፈተው በር፣ ለዲዲጂ እና ለሌሎች ዓለም አቀፍ ከዋክብት ኢትዮጵያን እንደ አዲስ እንዲመለከቷት አድርጓቸዋል። ምድረ ቀደምቷ ኢትዮጵያም እንደ ዲዲጂ ያሉ የጥበብ ሰዎችን በክብር ለመቀበልና የባህልና የዘመናዊነት ጥምረትዋን ለዓለም ለማሳየት ዝግጁ የሆኑ በርካታ መዳረሻዎችን አዘጋጅታለች። በርካታ ተከታዮቹና ሌሎች ዓለም አቀፍ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ጉዞውን እንደሚደግፉና ምድረ ቀደምት ወደ ሆነችው ኢትዮጵያ የሚያደርገው ጉዞ ስኬታማ እንዲሆንለት እያበረታቱት ይገኛሉ።

በአጠቃላይ በርካታ ታዋቂ የኪነ ጥበብ ሰዎች ኢትዮጵያን ለመጎብኘት ጉጉት እንዳላቸው እየገለጹ ነው። ምክንያቱም ኢትዮጵያ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ያላት የተፈጥሮ ስጦታ እና ሰው ሠራሽ ሀብት ማለቂያ የለውም። በተጨማሪም በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ የተገነቡት ዘመናዊ ፓርኮች፣ የዓድዋ ድል መታሰቢያ እና የቱሪዝም መሠረተ ልማቶች ሀገሪቱን ከታሪካዊነቷ ባለፈ ለዘመናዊ ጎብኚዎች ምቹ አድርገዋታል። ጥንታዊ ታሪክ ከዘመናዊ ሥልጣኔ ጋር የተዋሃደባት ሀገር በመሆኗ፣ ኢትዮጵያ የብዙ ጎብኚዎች ቀዳሚ ፍላጎት ሆና ስሟ እንዲነሳ ምክንያት ሆኗል።

ከዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ

# ኮሌጁ ከየት ወዴት?

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**

የአንድ ሀገር የጤና ዘርፍ ጥንካሬ የሚለካው ባለው የሕክምና ቁሳቁስ ብቻ ሳይሆን፣ ዘርፉን በሚመራው የሰው ኃይል እውቀትና በምርምር ውጤቶች ነው። በዚህ ረገድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የጤና አገልግሎትን ለማዘመን፣ የሕክምና ጥራትን ለማረጋገጥ እና አዳዲስ የፈውስ መንገዶችን ለመቀመር እንደ ዋነኛ ሞተር ያገለግላሉ። ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የንድፈ-ሐሳብ መገኛ ብቻ ሳይሆኑ፣ የኅብረተሰቡን የጤና ችግሮች የሚፈቱ ተግባራዊ ጥናቶች የሚከናወኑባቸው የለውጥ ማዕከላትም ናቸው።

እነዚህ ተቋማት ብቁና በሥነ-ምግባር የታነጹ የሕክምና ባለሙያዎችን በማፍራት ረገድ የማይተካ ሚና አላቸው። ዘመኑ ከደረሰበት የቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር የሚራመድ የጤና ባለሙያ በማፍራት፣ የሕክምና አገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋና ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋሉ። ይህም በጤና ተቋማት ውስጥ የሚስተዋለውን የአገልግሎት መዘግየት ከመቅረፍ ባለፈ፣ በታካሚዎችና በባለሙያዎች መካከል ያለውን ግንኙነት በሳይንሳዊ መንገድ እንዲቃኝ ያስችላል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ በዚህ ረገድ በምሳሌነት የሚጠቀሰው ጆንስ ሆፕኪንስ ዩኒቨርሲቲ (Johns Hopkins University) ነው። ይህ ተቋም በተለይም በሕክምና ምርምር እና በትምህርት ጥራት የዓለምን ቀዳሚነት ስፍራ የያዘው፣ በክሊኒካዊ ልምምድ እና በንድፈ-ሐሳብ መካከል ያለውን ልዩነት በማጥበቡ እንደሆነ ይነገርለታል። ተቋሙ አዳዲስ የሕክምና ግኝቶችን ለዓለም በማስተዋወቅና የሕዝብ ጤና አጠባበቅ ስልቶችን በመቀመር ረገድ ወደር የለውም። ይህም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሰው ልጅን ሕይወት ለመታደግ ያላቸውን አቅም በተግባር ያሳያል።

በትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚፈጠሩ የፈጠራ ውጤቶች ወደ ሕክምና ማዕከላት ሲወርዱ፣ ዜጎች ጥራቱን የጠበቀ ፈጣን የሕክምና አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ። ስለሆነም ለእነዚህ ተቋማት የሚደረገው ድጋፍና የሚመደበው የምርምር በጀት ለጤናው ዘርፍ መዳበር እንደ ትልቅ ኢንቨስትመንት ሊወሰድ ይገባል።

በሀገራችንም መሰል ተቋማት እየተስፋፉ ይገኛሉ። የዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አንዱ ነው። ኮሌጁ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር የሚገኝ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ሲሆን፣ የመጀመሪያው የጤና ረዳት ማሰልጠኛ ተቋም በመሆን በ1941 ዓ.ም እንደተቋቋመ መረጃዎች ያመላክታሉ።

ከዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ያገኘናቸው ጽሑፋዊ መረጃዎች እንደሚያመላክቱት፣ በጤናው ዘርፍ የነበረውን ከፍተኛ የባለሙያዎች


ፎቶ ከፋይል
የዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ቺፍ ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተር አቶ አለሙ ዳንኤል

እጥረት ለመቅረፍ ኮሌጁ በዘርፉ የሠለጠኑ ብቁ ባለሙያዎችን እንዲያፈራ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሻሻለው ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 ዓ.ም መሠረት የዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ሆኖ በደንብ ቁጥር 3/2000 ዓ.ም ተቋቁሟል።

ኮሌጁ ወቅታዊና ጥራቱን የጠበቀ ቴክኖሎጂን ያማከለ የጤና ትምህርትና አገልግሎት፣ ችግር ፈቺ ምርምር እንዲሁም የማኅበረሰብ አገልግሎት በመስጠት ለሀገራዊ ብልጽግና ጉዞ የራሱን አሻራ ለማሳረፍ ተቋማዊ የአደረጃጀት ለውጥ በማድረግ ተልዕኮውን በመወጣት ላይ ይገኛል።

የዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ቺፍ ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተር አቶ አለሙ ዳንኤል ኮሌጁ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ሥር እንደሚገኝ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ከሌሎች ተቋማት ጋር ሊናበብ እና ሊተገበር የሚችል ሥርዓተ ትምህርት በመጠቀም የሕብረተሰቡን የጤና ችግሮች ለመፍታት ብቁ የጤና ባለሙያዎችን በማፍራት ረገድ የበኩሉን ኃላፊነት እየተወጣ እንደሆነ ነው ያስረዱት።

የዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ እና የኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ በአንድ ከተማ አስተዳደር ሥር ያሉ መሆናቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት መመስረቱን ያወሱት አቶ አለሙ፣ ተመሳሳይ የሆነ የሥልጠና ሂደትን የሚከተሉ በመሆኑ ቢዋሃዱ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖራቸው በመታመኑ ከዩኒቨርሲቲው ጋር ነሐሴ 8 ቀን 2010 ዓ.ም በመዋሃድ ቆይቷል ብለዋል።

ከሐምሌ 2014 ዓ.ም ጀምሮ የዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ወደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ተመልሶ በመልሶ ማቋቋሚያ አዋጅ ደንብ ቁጥር 153/2015 የዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የሚል ስያሜ አግኝቶ አዲስ መዋቅራዊ አደረጃጀት ኖሮት ሥራውን እየሠራ ይገኛል።

በተቋሙ ስትራቴጂክ ሰነድ ላይ እንደተመላከተውም የኮሌጁ ራዕይ "ኮሌጁ በ2026 ዓመተ ምህረት በጤና ትምህርት እንዲሁም ችግር ፈቺ ጥናትና የምርምር ሥራዎችን አጠናክሮ በመቀጠል ሆስፒታል ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ሆኖ ማየት" የሚል ነው።

ጥራታቸውን የጠበቁ የጤና ትምህርት ዘርፎችን በማስተማር፤ በእውቀት፣ በክህሎት እና በአመለካከት ብቁ እና ተወዳዳሪ የጤና ባለሙያዎችን በማፍራት፣ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን በማካሄድ፤ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በማላመድ፣ በማስረፅ እና የማኅበረሰብ አገልግሎት በመስጠት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን ብሎም የሀገሪቱን የጤና ዕድገት ማፋጠን የሚል ነው።

እነዚህን ርዕዮችና ግቦች አስቀምጦ ወደ ትግበራ የገባው የዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በከተማ ደረጃ ብቃት ያላቸውን የጤና ባለሙያዎች ከማውጣት ባሻገር በየዓመቱ በአሥር ሺህ ለሚቆጠሩ የከተማዋ ነዋሪዎች የውስጥ ደዌ ሕክምናና አገልግሎት በመስጠት ላይ አተኩሮ እየሠራ እንደሆነም ዋና ሥራ አስፈጻሚው ያስረዳሉ።

በእርግጥም በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ያለውን የመማር ማስተማር ሥራ በተሳካ ሁኔታ ለማስቀጠል፣ የትምህርትና ሥልጠና፤ የጥናትና ምርምር፣ ማኅበራዊ አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግ፣ የተገልጋይ ፍላጎት የሚያረካ፣ ጊዜንና ወጪን ቆጣቢ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

ለዚህም ተቋማት ለተገልጋዮችና ለባለድርሻ አካላት የሚሰጧቸውን አገልግሎቶች የአገልጋይነት መንፈስ በመላበስ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል የለውጥ መሣሪያዎችን በመተግበር አደረጃጀታቸውንና አሠራራቸውን መለወጥ እና ማዘመን እንዳለባቸው ይታመናል።

የዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተቋማዊ የአደረጃጀት ለውጥ በማድረግ ተልዕኮውን በመወጣት የሀገሪቱን የዕድገት ጉዞ ከዳር ለማድረስ የሚያስችል ሥልጠና እየሰጠ ሲሆን፣ 60 በመቶ የመማር ማስተማር፣ 25 በመቶ ጥናትና ምርምር እንዲሁም 15 በመቶ የማኅበረሰብ አቀፍ አገልግሎቶችን ከማስፈጸም አኳያ ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን በትኩረት እየሠራ እንደሆነም ነው የተቋሙ ዋና ሥራ አስፈጻሚው አቶ አለሙ የሚጠቁሙት።

ኮሌጁ በ2017 ዓመተ ምህረት በአዲስ መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት ክሊኒካል ነርስና ሚድዋይፈሪን (የማዋለድ አገልግሎት) ጨምሮ 3 የትምህርት ክፍሎችን በአዲስ መልክ በማቋቋም በአሁኑ ወቅት 17 የትምህርት ክፍሎች ያሉት ሲሆን፤ በእነዚህ ትምህርት ክፍሎች ውስጥ 16 የቅድመ-ምረቃ እና 6 የድህረ-ምረቃ ፕሮግራሞች ይገኛሉ። በተጨማሪም በአካዳሚክ ዘርፍ 5 ዳይሬክተሮች፣ አንድ የተማሪዎች ዲን እና 6 የአስተዳደር ዳይሬክቶሬቶችም በሥሩ አሉት።

እንደ ዋና ሥራ አስፈጻሚው አቶ አለሙ ገለጻ የትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂና አዋጅ 954/2016 የዜጎች ብቃትና ተነሳሽነት ተጣጥሞ የመኖርን ችሎታ ለማሠልጠን ታስቦ የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ መሥራት ቢቻል ለማኅበረሰባችን ድህነት ቅነሳ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ዝቅተኛ እና መካከለኛ ደረጃ ባለሙያዎችን ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማቅረብ በተቀመጠው እንዲሁም በቅርቡ በሀገራችን በጸደቀው ፍኖተ ካርታ መሠረት በከፍተኛ ትምህርት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በተለዩ የትኩረት አቅጣጫዎች በተደራሽነት፣ እኩልነት፣ ከብዝሃነት ጋር አንድነት፣ ጥራት፣ ተገቢነት፣ ቅልጥፍና እና የገንዘብ ድጋፍን ጨምሮ የተሻሻለ ሥራ እንዲሠራ አስፈልጓል።

በዚህም የከፍተኛ የትምህርት ፖሊሲውና ሥርዓተ ትምህርቱ የአካባቢዎችን ሁለንተናዊ ዕድገት በሁሉም ዜጎች ለማስፈን፣ በራስ መተማመን እና ብቁ ዜጎችን ለማፍራት፣ ወሳኝ አሳቢዎች እንዲሆኑ፣ የዓለም ገበያ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ብቃት ያላቸው ባለሙያዎች ለመፍጠር፣ ሥራ ፈጣሪዎች እና ፈጠራን የሚያበረታቱ፣ ጠንካራ የሥነ ምግባር እና የሞራል እሴቶችን የሚያዳብሩ፣ ለፍትሕ የሚቆሙ፣ ሰላም እና በልዩነት ውስጥ አንድነት የሚያመጡ ዜጎችን ለመቅረጽ በተቀመጠው መሠረት የዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የተለያዩ የትምህርት ፕሮግራሞችን በመክፈት ጥራቱን የጠበቀ ትምህርትና ሥልጠና በመስጠት ላይ ይገኛል።

# ልጆች፤ ስለ የልጆች ዓለም ፓርክ ምን ያህል ታውቃላችሁ?

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ልጆች፤ አዲስ አበባ በኮሪደር እና በወንዝ ዳርቻ ልማት በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል፤ በመሠራት ላይም ይገኛሉ። ከእነዚህ ሥራዎች መካከል የመዝናኛ ስፍራዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ልጆች፤ ልማቱ እንደሌሎቹ የኅብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ እናንተንም ተጠቃሚ እያደረገ መሆኑን እናንተ በአንደበታችሁ የመሰከራችሁት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ እናንተ እንድትዝናኑ፣ አእምሮአችሁ ዘና እንዲል ዕድል ፈጥሮላችኋል፡፡ የከተማ አስተዳደሩ ለእናንተ ለልጆች ትኩረት መስጠቱን አጠናክሮ በመቀጠል አሁን ላይ "የልጆች ዓለም" በሚል መዝናኛ ቦታ እየሠራላችሁ ነው፡፡

ልጆች፤ የልጆች ዓለም ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣ በውስጡ ምን ምን መዝናኛዎች እንዳሉትና ምን ዓይነት ጠቀሜታ እንደሚያስገኝ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ኃላፊ ጠይቀናል፡፡ እሳቸውም ስማቸውንና ኃላፊነታቸውን በማስተዋወቅ ስለ ጉዳዩ ማብራሪያ ይሰጧችኋል፡፡

"ሰላም ልጆች እንዴት ናችሁ፤ ፀሐይ ጌታሁን እባላለሁ፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ውበት እና አረንጓዴ ልማት ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ እና የልጆች ዓለም ፓርክ ግንባታ አስተባባሪ ነኝ፡፡

ልጆች፤ የልጆች ዓለም ማለት እናንተ የምትደሰቱበት፣ የምትዝናኑበት እንዲሁም የምትማሩበት፣ የፈጠራ ሥራዎችን የምታዳብሩበት ቦታ ነው። ይህ ማለት ስብዕናችሁ ወይም ሥነ ምግባራችሁ የሚገነባበት ማለት ነው፡፡"



ፎቶ ከፋይል

ለልጆች ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ያለው የልጆች ዓለም ፓርክ ከፊል ገጽታ

እየተገነባላችሁ ያለው የልጆች ዓለም ፓርክ የሚገኘው ካዛንችስ ነው። ፓርኩ በጣም ሰፊ እና በከተማችንም የመጀመሪያው ነው፡፡ በጣም የሚያምር ሆኖ በውስጡ የተለያዩ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረጊያ ሰፋፊና ጠመዝማዛ የመሮጫ መንገዶች፣ መረብ ኳስ፣ ቅርጫት ኳስ፣ እጅ ኳስ እና የብስክሌት መንጃዎችን ይዟል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በባቡርና በትንንሽ መኪናዎች መንሸራሸሪያ ቦታ፣ በዛፍ መልክ የተሠሩ የተለያዩ ውበት ያላቸው መብራቶች፣ የንባብ ባህላችሁን የምታዳብሩበት ቤተ መጻሕፍት፣ የፈጠራና የኪነ ጥበብ ሥራዎች፣ ለሕፃናት ተስማሚ የሆኑ ምግቦችና መጠጦችን የያዘ የካፌ አገልግሎት፣ የተለያዩ የእፅዋት ዝርያዎችና የመሬት ገጽታዎች (መልከዓ ምድር)፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚታወቁ አገራት የሚታዩ የመጫወቻ ዓይነቶችን የያዘም ነው፡፡ ኢትዮጵያዊ እሴትን የጠበቀ ማለትም ባህላዊ ቤቶች፣ የቡና ሥርዓት፣ ሳይንሳዊ ምርምር የምታደርጉበት የፈጠራ ማዕከልም አሉት፡፡

የልጆች ዓለም ፓርክ የሚሰጠው አገልግሎት በቴክኖሎጂ በተደገፈና ዘመናዊ እንዲሆን ተደርጎ ነው እየተሠራ ያለው፡፡

ፓርኩ ተመርቆ መጥታችሁ ስትዝናኑ የተለያዩ ጥቅሞችን ታገኛላችሁ። ከእነዚህም ውስጥ የመጀመሪያው የአገራችሁን ባህል ታውቃላችሁ፤ ባህሏን ስታውቁ አገራችሁን የበለጠ እንድትወዱ ያደርጋችኋል፡፡ አዳዲስ ነገሮችን በመመራመርና በመሞከር የፈጠራ ችሎታችሁን ታዳብራላችሁ። አእምሮአችሁ ይነቃቃል፤ አካላዊ እንቅስቃሴን ስለምታደርጉም ለጤናችሁ ዘርፈ ብዙ ጥቅም እንድታገኙ ትሆናላችሁ።

ልጆች፤ አዲስ አበባ ከተማ ለእናንተ ምቹ ሆና እየተሠራች ነው፡፡ የተለያዩ መጫወቻ ቦታዎች ተሠርተውላችኋል። ዕድለኞች ናችሁ፡፡ የልጆች ዓለም ፓርክ ግንባታ ሲጠናቀቅ መጥታችሁ እንድትዝናኑ ጋብዣችኋለሁ፡፡ የዚያን ጊዜ እንግዶቻችን እናንተ ናችሁ፡፡ መልካም የትምህርት ጊዜ ይሁንላችሁ፡፡

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ሲወስዱበት የሚሰፋ**

**መልስ፦** መ. ጉድጓድ

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ጉድ መጣ ጉድ መጣ ከመሬት ውስጥ ልቃቂት ወጣ**

ሀ. ቀይ ሽንኩርት
ለ. ልቃቂት
ሐ. ነጭ ሽንኩርት

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ።**

**ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ መሶብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል የመንግስት አገልግሎት ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ**

# “የተገልጋይ እርካታን ከፍ የሚያደርጉ ሥራዎች እያከናወንኩ ነው”

**አዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት**

- **ተቋሙ የተገልጋይ እርካታን 94 ነጥብ 2 ከመቶ ማድረሱን ገልጿል**

**በደረጀ ታደሰ**

ወጣት መርየም አሚን ትባላለች፡፡ ወደ አዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት የመጣችው ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሆን፣ ምክንያቷ ደግሞ የፋይዳ መታወቂያ ለማውጣት የሚያስችላትን አሻራ ለመስጠት ነው፡፡ ጉዳይዋን ፈጽማ ስትወጣ አግኝተናት ስለ አገልግሎት አሰጣጡ ጠየቅናት፡፡ እሷም ሐሳቧን የገለጸችው፤ “በጣም አሪፍ ነው። ፈጣን ነው፡፡ ሳልጉላላ ነው አገልግሎቱን ያገኘሁት፡፡ ከመግቢያው ጀምሮ በትሕትና ተቀብለው፣ የትና እንዴት መሄድ እንዳለብኝ አግዘውኛል፡፡ ስመጣ የነበረኝን ግምት ፍጹም የቀየረ ሁኔታ ነው ያገኘሁት፡፡ ወረፋ እና ሰልፍ እንደሚኖር ጠብቄ ነበር፡፡ ነገር ግን ቦታው ደርሼ የተመለከትኩት ፈጣን፣ ቀልጣፋና ደስ የሚል አገልግሎት የሚሰጥበት መሆኑን ነው” በማለት ነው፡፡

አያይዛም፤ እንዲህ ዓይነቱ ልምድ በሁሉም የመንግሥት ተቋማት መስፋፋት እንደሚገባው አስተያየቷን አጋርታለች፡፡ በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ያሉ ተቋማት በአዲስ መሶብ ደረጃ ላይ ቢደርሱ የሕብረተሰቡ እንግልት ይቀንሳል፣ ጊዜና ገንዘብ ይቆጠባል፣ የሕዝብ ምሬት ይቀንሳልም ብላለች፡፡

በአሁኑ ወቅት በአራዳ ክፍለ ከተማ በሚገኘው አዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል መንግሥት አገልግሎት ዋና መሥሪያ ቤት እና በቦሌ ቅርንጫፍ አማካኝነት በየዕለቱ ከ9 መቶ እስከ 1ሺህ ተገልጋዮች በመገልገል ላይ ናቸው፡፡ እንደ ወጣት መርየም ሁሉ ሌሎችም ተገልጋዮች ከተቋሙ በሚያገኙት አገልግሎት ደስተኞች ናቸው፡፡ በአገልግሎት አሰጣጡ የሚደነቁ፣ የተሰማቸውን ስሜት በጽሑፍ እና በቃል የሚገልጹ፣ በአጋጣሚዎች ሁሉ ለሌሎች ምስክርነት የሚሰጡ ብዙዎች ናቸው፡፡ በዚህ መልኩ ከተገልጋይ የሚሰጥ አዎንታዊ አስተያየት እና ግብረ መልስ፣ ተቋሙን ለተሻለ ስኬት የሚያተጋ ኃይል ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡

የአዲስ መሶብ አገልግሎት አሰጣጥ በተገልጋዮች ዘንድ የመወደዱ እውነት በጥናት የተረጋገጠ ነው፡፡ እንደ ጥናቱ መረጃ፣ የተቋሙ ተገልጋዮች እርካታ ከ94 ነጥብ 2 ከመቶ በላይ ደርሷል። የተቋሙ ውጤታማነት በከተማ አስተዳደሩ ተመስክሮለታል፤ ዕውቅናም ተሰጥቶታል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ፣ የ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት አፈጻጸምን ለአዲስ አበባ ምክር ቤት ባቀረቡበት ወቅት በአገልግሎት አሰጣጥ መዘመንና መሻሻል ላይ “የአዲስ መሶብ አፈጻጸም አበረታች ስለመሆኑ” ያነሱትን ሐሳብ ማስታወስ ይገባል፡፡

ከንቲባ አዳነች በሪፖርታቸው፤ “የከተማችንን ነዋሪዎች እንግልት ለመቀነስና ቃላችንን አክብረን ለማገልገል፣ አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል፣ የተቋም ግንባታን ቁልፍ ተግባራችን አድርገን በማቀድ በርካታ ሥራዎችን አከናውነናል። የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሳደግ፣ የሰው ኃይል ብቃትና ሥነ ምግባር ማሻሻል፣ ግልጽ እና ቀልጣፋ አሠራርን መተግበር ዋና ዋና የትኩረት ማዕከል በማድረግ ተሠርቷል፡፡ በዚህም እንደ ከተማ አስተዳደር 23 አዳዲስ አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ የተደገፉ እንዲሆኑ ተደርጓል። በአጠቃላይ በቴክኖሎጂ ታግዘው የሚሰጡ አገልግሎቶች ብዛት ከ370 በላይ ደርሷል፡፡ በተለይም ሁለት አዳዲስ ‘የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት’ መስጫዎች፣ ደረጃቸውን ጠብቀው ወደ አገልግሎት መግባታቸው አገልግሎቶችን በተቀናጀ መልኩ ለመስጠት አስችለዋል፡፡ ይህም የተገልጋዩን ሕብረተሰብ እንግልት፣ ጊዜንና ወጪን በመቀነስ፣ ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጥ አግዘዋል፡፡ የአዲስ መሶብ የተገልጋይን እርካታ 94 ነጥብ 2 ከመቶ ማድረስ ተችሏል” በማለት አብራርተዋል፡፡



ፎቶ- ከፋይል

የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ባለጉዳዮችን በማስተናገድ ላይ

አቶ ደረጀ አየለ፣ የተቋሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተር እና የዲጂታላይዜሽንና የአንድ ማዕከል ልማት ዘርፍ ኃላፊ ናቸው፡፡ በዋናው መሥሪያ ቤት እና በቦሌ ቅርንጫፍ በሚሰጠው አገልግሎት የተገልጋይ እርካታ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ፣ ይህንን የእርካታ ደረጃ ለማወቅ ስለሚከተሉት አሠራር፣ ጅምሩን ለማስቀጠል እና ለማስፋት በቀጣይ ስለተያዘው ዕቅድ እንዲሁም ተያያዥ ጉዳዮች ለዝግጅት ክፍላችን ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

እንደ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ በማዕከሉ የሚሰጥ ማንኛውም አገልግሎት ከብልሹ አሠራር የጸዳ፣ ተገልጋይን ያከበረ፣ የሥራ ሥነ ምግባርን የተከተለ፣ ጊዜንና ገንዘብን ያላባከነ፣ በዋናነትም የተገልጋይን እርካታን ከፍ ያደረገ እንዲሆን እየተሠራ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሠረት በዋናው መሥሪያ ቤት እና ቦሌ ቅርንጫፍ (ይህ መረጃ እስከ ተጠናቀረበት የካቲት 12 ቀን 2018 ዓ.ም. ድረስ ከ90 ሺህ በላይ) ተገልጋዮች የተለያዩ አገልግሎቶችን አግኝተዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ስላገኙት አገልግሎት በቴክኖሎጂ በታገዘ ዘመናዊ የአሠራር ሥርዓት በግብረ መልስ ሰጥተዋል፡፡ አስተያየታቸውም ተተንትኖ፣ ለተቋሙ ዕድገት በግብዓትነት ጥቅም ላይ ውሏል።

በተቋሙ አገልግሎቱን ለማዘመን፣ ለማሻሻል፣ ለማቀላጠፍ፣ ጊዜና ወጪን ለመቆጠብ፣ ከሁሉም በላይ የተገልጋይን እርካታ ከፍ ለማድረግ እንዲያስችሉ ቁጥራቸው ዘጠኝ የሚደርሱ (በዋናነት የኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት) የለሙ ዲጂታል የሥራ ማቀላጠፊያዎች (Systems)ለአገልግሎት በቅተዋል፡፡ ከእነዚህ ዲጂታል የሥራ ማቀላጠፊያዎች መካከል፡- የተገልጋይ እርካታ ግብረ መልስ የሚሰበሰብበት አንዱ ነው፡፡

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ እንዳስረዱት፤ የተገልጋይ እርካታ ግብረ መልስ የሚሰበሰብበት ሥርዓት ተገልጋዩ አገልግሎቱን አግኝቶ እንደጨረሰ፣ በአገልግሎቱ ምን ያህል እንደረካ ክትትል የሚደረግበት ዘመናዊ አሠራር ሲሆን፣ ማንኛውም ተገልጋይ የተሰማውን ስሜት በነጻነት የሚገልጽበት ነው፡፡ አገልግሎት አግኝቶ የጨረሰ ተገልጋይ፣ ለአስተያየት መሰብሰቢያ የተዘጋጁ መጠይቆችን ከታብሌት ላይ በማንበብና በመሙላት ይሰጣል፡፡ የአስተያየት መሰብሰብ ሥራው የተሳካ እንዲሆን በሁሉም የሕንፃው ወለል ላይ የተመደቡ በጎ ፈቃደኛ ባለሙያዎች ለተገልጋዮች ሲስተሙን በማሳወቅ እና እንዲጠቀሙ ይደግፋሉ፡፡

አቶ ደረጀ አክለው እንደጠቆሙት፤ በእያንዳንዱ ተገልጋይ የተሰጠው አስተያየት ተተንትኖ መረጃው በማዕከል ደረጃ ላሉ አመራሮች ይደርሳል፡፡ መረጃው ምን ያህል ተገልጋይ አስተያየት እንደሰጠ፣ አስተያየቱ ምን እንደሆነ፣ የእርካታ መጠኑ (ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ) ምን ደረጃ ላይ እንደተቀመጠ... የሚገለፅ ነው፡፡ በተገኘው የመረጃ ትንተና ውጤት ላይ በየዕለቱ የስትራቴጂክ ማኔጅመንት ክፍሉ ውይይትና ግምገማ ያካሂዳል፡፡ በተመሳሳይ የሳምንቱ፣ የወሩ፣ የሩብ ዓመቱ፣ የስድስት ወሩ እና የዓመቱ የተገልጋዮች እርካታ ውጤት የሚተነተን፣ ውይይትና ግምገማ የሚደረግበት ይሆናል፡፡ ከዚህ በመነሳት ለክፍተቶች ፈጣንና ተገቢ መፍትሔ ይሰጣል፡፡ ለቀጣይ ውጤታማነት አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችንም ይወስዳል፡፡

በቴክኖሎጂ ከታገዘው የተገልጋይ እርካታ ግብረ መልስ የሚሰበሰብበት የአሠራር ሥርዓት በተጨማሪ፤ የተቋሙ አመራሮች የተገልጋዮች እርካታን የተመለከተ አስተያየት እንዲሰጡ ቃለ መጠይቅ እንደሚያደርጓቸው የሚገልጹት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፣ የተቋሙን አበረታች ልምድም ጠቅሰዋል፡፡ የተቋሙ አመራሮች ባነሷቸው ጥያቄዎች ላይ ተገልጋዮች የሰጧቸው የቃል አስተያየቶች ጭብጥ፤ “በከተማ አስተዳደራችን የመንግሥት አገልግሎት ይህን ያህል ጥራት፣ በዚህን ያህል ፍጥነት፣ እጅግ በሚደነቅ የሠራተኛ የአገልጋይነት ስሜት፣ በተመቻቸ የሥራ አካባቢ ላይ መሠራቱ የሚበረታታ እና ሊሰፋ የሚገባው ነው” የሚል መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተመለከተ ራሱን የቻለ ስታንዳርድ ተዘጋጅቷል፡፡ የሠራተኛው የሥራ ዲሲፕሊን ምን መሆን እንዳለበት ግልጽ የሥነ ምግባር መመሪያ አለ፡፡ በተጨማሪ፤ በሥራ ላይ የዋሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እና ሲስተሞች ከሰው እጅ ንክኪ ነጻ መሆናቸው ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ ፈጣን፣ ከአድልዎ ነጻ፣ ተገልጋይን ያከበረ... አገልግሎት እንዲሰጥ ከፍተኛ ድርሻ እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡ የእነዚህ ድምር ውጤትም በተቋሙ የተገልጋይ እርካታ ከፍተኛ እንዲሆን አግዞታል። ይህ ውጤት የሚያበረታታ ቢሆንም፤ ተኩራርቶ ለመቀመጥ ወይም ያለውን ለማስቀጠል የሚያበቃ አለመሆኑን ከንቲባ ወይዘሮ አዳነችን ጨምሮ በየደረጃው ያሉ የከተማ አስተዳደሩ አመራሮች እና ሠራተኞች የሚጋሩት ሐቅ ነው፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ አቶ ደረጀ በመልዕክታቸው፤ “በተቋሙ እየታየ ያለው የተገልጋይ እርካታ የሚያበረታታ ቢሆንም፤ እንደ አመራር እና እንደ አገልጋይ ሠራተኛ የሚያኮራ አይደለም። ይህንን ጅምር የበለጠ ለማጠናከር እና ለማስቀጠል ጥረት ማድረግ ይገባል፡፡ በቀጣይ የሚከፈቱ ቅርንጫፎች መሰል የተገልጋይን እርካታ በከፍተኛ ደረጃ የሚያረጋግጡ እንዲሆኑ ሁሉን አቀፍ ተግባር ማከናወን ይገባል፡፡ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ በሥራ ሥነ ምግባር በመመራት፣ ተገልጋይን በማክበር ‘ተገልጋይን ያከበረ እና እርካታውን ከፍ ያደረገ አገልግሎት’ መስጠትን መገለጫው የሆነ የመንግሥት ተቋም በስፋት መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ይህ ከአዲስ መሶብ አልፎ በከተማዋ ባሉ ሁሉም የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት መፈጸም አለበት” ብለዋል፡፡

በተመሳሳይ ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ የከተማ አስተዳደሩን የ2018 በጀት ዓመት የቀጣይ ስድስት ወራት ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች መካከል፤ የተጀመረውን የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎትን የበለጠ ማስፋትና ተደራሽነቱን ማሳደግ፣ በተቋማት መካከል ያለውን የአፈጻጸም ልዩነት ማቀራረብ፣ ለሕዝብ አገልግሎት የለሙ ቦታዎችን ለታለመላቸው ዓላማ ብቻ እንዲውሉ ማስቻል፣ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በቁርጠኝነት ለመፍታትና የነዋሪዎችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እንደሚገኙበት ያመላከቱበትን ጉዳይ ማንሳት፣ በመንግሥት አገልግሎት የተገልጋይን እርካታ ከፍ ለማድረግ እንደ ከተማ አስተዳደር የተደረሰበትን ቁርጠኛ አቋም ለመረዳት ያስችላል፡፡

ኢኮኖሚ

**ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ**

# የከተማ ግብርና ያቀለለው የኑሮ አቀበት

- **በአዲስ አበባ ከተማ 423 ሺህ 113 ነዋሪዎች በእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፍ በመሰማራት ተጠቃሚ መሆናቸው ተገልጿል**

**በይግለጡ ጓዴ**

በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 የሚገኘው የወይዘሮ ገላኔ ተሊላ መኖሪያ ግቢ፣ ዛሬ የተስፋ እና የሥራ ክብር መገለጫ ሆኗል። የ11 ልጆች እናት የሆኑት ወይዘሮ ገላኔ፣ ባለቤታቸውን በሞት ካጡ በኋላ የቤተሰቡ ሙሉ የኃላፊነት ሸክም በትከሻቸው ላይ ለመሸከም ተገደው ነበር። ይሁን እንጂ እኚህ ብርቱ እናት ተስፋ ከመቁረጥ ይልቅ፣ የከተማ ግብርናን እንደ መውጫ መንገድ በመጠቀም የኑሮን አቀበት በልጆቻቸው እገዛ መግፋት ጀምረዋል።

ወይዘሮ ገላኔ አሁን ላይ በከተማ ግብርና ዘርፍ በተለይም በሌማት ትሩፋት መርሃ ግብር አማካኝነት በእንስሳት ሀብት፣ በዶሮ እርባታና በወተት ልማት ተጠቃሚ መሆን ችለዋል። የ58 ዓመቷ እናት እንደሚናገሩት፣ የከተማ ግብርናው የምግብ ዋስትናቸውን ከማረጋገጥ ባለፈ ሕይወታቸውን አሻሽሎላቸዋል፤ ቤተሰባቸውን በኩራት እንዲያስተዳድሩም ያስቻላቸው የገቢ ምንጭ ሆኖላቸዋል።

የወይዘሮ ገላኔ ሥራ ለብዙዎች አርአያ የሚሆን ነው። በአሁኑ ወቅት 300 እንቁላል ጣይ ዶሮዎች፣ ስምንት የወተት ላሞች እና ሦስት ጥጆች ያሏቸው ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪም በበግና በሬ ማድለብ ሥራ ላይ በስፋት ተሰማርተዋል። ይህ ጥረት ደግሞ ለ11 ልጆቻቸው ብቻ ሳይሆን ለስድስት ቋሚ ሠራተኞች የሥራ ዕድል የፈጠረ ሲሆን፣ አጠቃላይ የሥራ ካፒታላቸውም 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር ደርሷል።

የወይዘሮ ገላኔ ልጅ የሆነው ወጣት ተሊላ መርጋ፣ የእናቱ ስኬት ቀጥተኛ ተጠቃሚና የሥራው አጋር ነው። ወጣቱ ተሊላ ከዚህ ቀደም የነበረውን የቅጥር ሥራ ትቶ እናቱን በማገዝ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ ግብርናው ከገንዘብ ባለፈ እንስሳትንና አትክልትን በመንከባከብ የሕሊና ዕረፍት እንደሰጠው ይገልጻል። ሌሎች ወጣቶችም ሥራ ሳይንቁ ወደ ከተማ ግብርና በመግባት የራሳቸውን ሀብት እንዲያፈሩ ይመክራል።

በተመሳሳይ በዚሁ ግቢ ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩት አቶ ታደሰ አቫቱ፣ የከተማ ግብርናው ለዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ረገድ ያለውን ሚና ይመሰክራሉ። በእንስሳት እንክብካቤ ሥራቸው በሚያገኙት ገቢ ቤተሰባቸውን እያስተዳደሩ እንደሚገኙና ሥራው በሕይወታቸው ላይ ትልቅ ለውጥ እንዳመጣላቸው ይገልጻሉ። ይህም የከተማ ግብርና የኑሮ ውድነትን በማረጋጋት ረገድ ያለውን ጉልህ ድርሻ በግልጽ ያሳያል።

ወይዘሮ ገላኔ ተሊላ ለስኬታቸው የከተማ ግብርና ባለሙያዎች የሚያደርጉላቸው ሙያዊ ምክርና የግብዓት ድጋፍ ከፍተኛ መሆኑን አይዘነጉም። ዛሬ ላይ የራሳቸውን ሕይወት ከመቀየር ባለፈ፣ ለሌሎች የአካባቢው ነዋሪዎች የሥራ ተሞክሯቸውን እያካፈሉ ይገኛሉ። የከተማ ግብርና በትክክል ከተሠራበት የገንዘብ ምንጭና የደስታ መገኛ መሆኑን በተግባር እያስመሰከሩ ነው።




ፎቶ ከፋይል

ወይዘሮ ገላኔ ተሊላ በመኖሪያ ግቢአቸው ከሚያከናውኗቸው የከተማ ግብርና ሥራዎች መካከል ከፊሎቹ

የከተማ ግብርና እና የእንስሳት ሀብት ልማት በከተሞች ውስጥ ያለውን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ፣ የሥራ ዕድል ለመፍጠር እና የአካባቢ ጥበቃን ለማሻሻል ትልቅ ፋይዳ አለው። ይህ ዘርፍ በተለይ ውስን ቦታን በመጠቀም ከፍተኛ ውጤት የሚያስገኝ የኢኮኖሚ ዘርፍ እየሆነ መጥቷል። የከተማ ነዋሪዎች ወተት፣ እንቁላል እና ሥጋ በቀላሉ እና በቅርብ ርቀት እንዲያገኙ ያስችላል። በተለይ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች በፕሮቲን እና ቫይታሚን የበለፀጉ ምግቦችን በዝቅተኛ ዋጋ እንዲያገኙ ይረዳል።

በከተማ ደረጃ በዋነኝነት የሚከናወኑት ትናንሽ እንስሳትን በማርባት ላይ ሲሆን፣ ጥቅሞቹም በትንሽ ቦታ ብዙ እንቁላልና ሥጋ ማምረት ማስቻሉ ነው። ለቤተሰብና ለጎረቤት የሚሆን ንጹሕ ወተት በማቅረብ ረገድ የከተማ ግብርና ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አለው።

በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሀብታሙ ክብሬ፣ በከተማ ግብርና ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ገበያ የማረጋጋት ሥራ ላይ ትኩረት በማድረግ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል። አቅርቦትን በመጨመር ነዋሪዎች በተመጣጣኝ ዋጋ የግብርና ምርት እንዲያገኙ ለማስቻል፣ በራሳቸው ቦታ እና ግቢ ውስጥ በእንስሳት እርባታ፣ በዶሮ፣ በወተት ላም፣ በንብ ማነብ እና በማድለብ ላይ በክላስተር ተሳትፎ እያደረጉ መሆኑንም ተናግረዋል።

በሌማት ትሩፋት መርሐ ግብር በወረዳው 4 ሺህ 300 ነዋሪዎች በዶሮ እርባታ ሥራ ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን

> **በከተማዋ በእንቁላል ጣይ ዶሮ ልማት 414 ሺህ 892፣ በወተት ላም 5 ሺህ 246 ነዋሪዎች ተሰማርተው ተጠቃሚ ሆነዋል**

ጠቁመው፣ በወተት ላም ደግሞ 372 እማወራዎች እና አባወራዎች ወደ ሥራ መግባታቸውን ገልጸዋል።

በወረዳው በዚህ ዓመት ወደ 14 ሺህ ዶሮዎች በማስገባትና ስርጭት በማድረግ ነዋሪዎች በጓሯቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረጋቸውን ተናግረዋል። ሰፊ ቦታ ለሌላቸው ደግሞ የዶሮ ኬጅ (Cage) በማስገባት ተጠቃሚ እያደረጉ መሆኑንም ይገልጻሉ።

አቶ ሀብታሙ በማብራሪያቸው፣ ለተጠቃሚዎች የሙያ፣ የእንስሳት ሕክምና፣ የብድር፣ የዶሮ ጫጩት፣ የመኖ እና የኬጅ ግብዓት ድጋፍ እየተደረገ መሆኑን አውስተው፣ በቤተሰብ ደረጃ ለተደራጁ የከተማዋ ነዋሪዎች ጭምር ድጋፉ እንደሚደረግ አስታውቀዋል። ለአንድ ቤተሰብ ከ100 በላይ እንቁላል ጣይ ዶሮዎችን በመስጠት ሥራ እንዲጀምሩ መደረጉንም ተናግረዋል። ሰፊ ቦታ ያላቸው ደግሞ በወተት ላም ሥራ ላይ ትኩረት አድርገው እንዲሠሩ በማድረግ ውጤታማ የሆኑ ነዋሪዎች መኖራቸውን ገልጸዋል።

የኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ ደመቁ ንጉሡ፣ በክፍለ ከተማው በከተማ ግብርና ዘርፍ ሰፋፊ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ ብለዋል። በተለይ በሌማት ትሩፋት መርሐ ግብር "ምግቤን ከጓሮዬ" በሚል መሪ ቃል በርካታ ቁጥር ያላቸው የከተማዋ ነዋሪዎች ወደ ዘርፉ መቀላቀላቸውን ገልጸዋል።

በመርሐ ግብሩ አማካኝነት በቤተሰብ ፍጆታና በገበያ ላይ የግብርና ምርቶችን ማምረትና ከማቅረብ አንጻር የተሻለ ሥራ መሠራቱን ጠቁመዋል። በተለይ የወተት ከብት እርባታ፣ ማድለብ፣ ንብ ማነብ እና በዶሮ እርባታው ዘርፍ ከቤተሰብ ተጠቃሚነት ባለፈ ሰፋፊ ክላስተር የመፍጠር ሥራ መሠራቱን ገልጸዋል።

በተመሳሳይ በየካ ክፍለ ከተማ የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ መሰረት መካሻ፣ በክፍለ ከተማው በሚገኙ 12 ወረዳዎች በእንስሳት ሀብት ልማት፣ በዶሮ እርባታ፣ በወተት ላሞች ማርባት፣ በንብ፣ በአሳ እና በከብት ማድለብ ሥራዎች ይሠራሉ ብለዋል። በእንስሳት ሀብት እና በእጽዋት ልማት 89 ሺህ 911 ነባር ተጠቃሚዎችን ማስቀጠል መቻሉን ተናግረዋል።

በእንስሳት ሀብት ብቻ 35 ሺህ 332 ነባር ተጠቃሚዎችን ማስቀጠል መቻሉን የጠቆሙት ወይዘሮ መሰረት፣ በግብዓት አቅርቦት፣ በመኖ አቅርቦት ትስስር፣ በብድር፣ በእንስሳት ጤና ሕክምና፣ በመሥሪያ ሼድ እና በቴክኒካል ድጋፍ እገዛ እየተደረገ መሆኑን ይገልጻሉ።

በክፍለ ከተማው በእንስሳት ዘርፍ ነዋሪዎች ወተት እና እንቁላል ምርት በቅርብ እና በቅናሽ ዋጋ እንዲያገኙ ማስቻላቸውን ወይዘሮ መሰረት ገልጸው፣ ለቀጣይም ዘርፉ ውጤታማ እንዲሆን የሚደረገው የግብዓት እና የሙያ ድጋፍ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አስረድተዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የእንስሳት ሀብት ዳይሬክተር ዶክተር ደጀኔ ጌታቸው፣ በከተማ ግብርና በእንስሳት ሀብት ልማት ሰፊ ሥራ እየተሠራ መሆኑን በመጠቆም፣ በከተማዋ 423 ሺህ 113 ተጠቃሚዎች መኖራቸውን ገልጸዋል።

በከተማዋ እንቁላል ጣይ ዶሮ 414 ሺህ 892፣ በሥጋ ዶሮ 1 ሺህ 174፣ በወተት ሀብት 5 ሺህ 246፣ በንብ እርባታ በማኅበር እና በግለሰብ 1 ሺህ 801 ነዋሪዎች መሰማራታቸውን ጠቁመዋል። በክላስተር ደረጃ፣ በቤተሰብ ፓኬጅና በአርሶ አደሮች በራሳቸው ይዞታ የእንስሳት ሀብት ልማት ሥራን ተግባራዊ እያደረጉ ይገኛሉ።

በሌማት ትሩፋት የእንስሳት ተዋጽኦ ምርቶች የቅንጦት ምግቦች ሳይሆኑ ከሌማት የማይለዩ፣ በዕለታዊ ምግቦች ማባያነት የማይታጡ ግብዓቶች ማድረግ እንደሚቻል እሙን ነው። የሌማት ትሩፋት መርሐ ግብር የእንስሳት ተዋጽኦ ምርት እምርታን ማረጋገጥ እና ከእምርታው ፍሬም የመቋደስ ግብ በመሰነቅ እየተተገበረ ያለ መርሐ ግብር ነው። በዚህም ውጤት መታየቱ በተግባር የታየ ሃቅ መሆኑ ይታወቃል።

በከተማዋ በከተማ ግብርና በሌማት ትሩፋት እየተሠሩ ያሉ የተቀናጀ የከተማ ግብርና ሥራዎች በእንስሳት ሀብት እና በሌሎችም ዘርፎች ውጤታማ መሆን ችለዋል። አዲስ አበባ ላይ “የከተማ ግብርና ሥራ አይቻልም” የሚለው አመለካከት መቀየሩን እና የነዋሪዎች የይቻላል አስተሳሰብ በተግባር የተረጋገጠበት ጉዳይ ሆኗል።

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የአዲስ አበባን የብክለት አጋላጮች ለመከላከል ምን እየተሰራ ነው?

**በለይላ መሀመድ**

### የአካባቢ ብክለት መንስኤዎችና ተጽዕኖው

አዲስ አበባ ለኑሮ ተስማሚና ምቹ የአየር ንብረት አላት፡፡ ይሁን እንጂ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከሕዝብ ቁጥሯ መጨመርና ከግንባታዎች መስፋፋት ጋር በተያያዘ የአካባቢ ብክለት አንዱ ፈተና ሆኖ እንደቆየ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሙክታር ሰይድ እንደሚገልጹት በከተማዋ የአካባቢ ብክለት መንስኤዎች በርካታ ናቸው፡፡ በዋናነት ከሚጠቀሱት መካከል ተገቢ ያልሆነ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት አንዱ ነው፡፡ የምግብ ትርፍራፊ፣ የፕላስቲክ ውጤቶች፣ የኢንዱስትሪ ተረፈ ምርቶች፣ ብረታ ብረቶች፣ የብርጭቆ ስብርባሪዎች የመሳሰሉት ለዚህ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ የአካባቢ ብክለት እያስከተለ ያለው የፕላስቲክ ከረጢት ወይም ፌስታል ነው፡፡

ፌስታል ከተማዋ ቆሸሻ እንድትታይ በማድረግ ውበቷን ያሳጣታል። የፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮችን በመዘጋት የአስፋልት መንገዶች በጎርፍ እንዲጎዱና ለአላስፈላጊ ብልሽት እንዲዳረጉ ያደርጋል። ይህ ደግሞ ጉዳቱ የአካባቢ ብቻም ሳይሆን ኢኮኖሚያዊ መሆኑንም ያመላክታል። ምክንያቱም የፕላስቲክ ከረጢት ለመበስበስ አንድ ሺህ ዓመት ያህል ጊዜ ይወስድበታል። በውስጡ ቆሻሻ እንደያዘ በሚወገድበት ወቅት እንስሳት ስለሚመገቡት በቀላሉ ሊገድላቸው ይችላል። ይህም የእንስሳቱ ባለቤቶች በኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ እንደሚያደርጋቸው አቶ ሙክታር ያስረዳሉ።

ለአዲስ አበባ አካባቢ ብክለት ሁለተኛው መንስኤ ወንዝና የወንዝ ዳርቻዎች በአግባቡ አለመያዛቸው ነው። እንደ ከተማዋ መሪ ፕላን በመሀል ከተማ ክልል የሚገኙት ወንዞች በግራና በቀኝ አቅጣጫ 15 ሜትር፣ በከተማዋ ዳርቻ ወይም ማስፋፊያ ቦታዎች በግራና በቀኝ እስከ 100 ሜትር ለወንዝ ዳርቻ መጠበቂያነት እንዲውል ያዛል። ይሁን እንጂ እነዚህ የወንዝ ዳርቻዎች በአብዛኛው በከተማው ውስጥ በመኖሪያ ቤቶች፣ ፋብሪካዎችና አገልግሎት መስጫዎች ሙሉ በሙሉ የተያዙ ነበሩ።ይህም የወንዝ ዳርቻዎችን አረንጓዴነት በማጥፋት በወንዞቹ ተፈጥሯዊ ሥርዓተ ምህዳር መኖር የነበረባቸው እንስሳት፣ ዕፅዋትና ሌሎች የብዝሃ ሕይወት አካላት ከአካባቢው እንዲጠፉ፣ ከተማዋም ውበትና ጽዳቷን እንድታጣ አድርጎ ቆይቷል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር
የአካባቢ ብክለትን ለመከላከል ከተሰሩ ሥራዎች መካከል የወንዝ ዳርቻ ልማት ይጠቀሳል

ሦስተኛው የአካባቢ ብክለት መንስኤ በከተማ አስተዳደር ውስጥ ለሚከናወኑ የመንገድና የሕንፃ ግንባታ የሚያገለግሉ የኮንስትራክሽን ማዕድናት በከተማው የተለያዩ ቦታዎች በሰፊው ተመርተው ለግንባታ ፍላጎት እየዋሉ መሆናቸው ነው። እነዚህ የኮንስትራክሽን ማዕድናት ማምረቻ ቦታዎች ቀደም ሲል ያለ ጥናት ይከናወኑ ስለነበር በሥርዓተ ምህዳሩ ላይ ሰፋ ያለ ጉዳት ሲያደርሱ ቆይተዋል።

ከጋራዥና የመኪና እጥበት፣ ከኢንዱስትሪዎች፣ ከመኖሪያ መጸዳጃ ቤቶች የሚወጣው ቆሻሻ ለአካባቢ መበከል ሌላው መንስኤ ነው። በከተማዋ የተቋቋሙት ጋራዦች በወንዝ ዳርቻዎች አካባቢ የሚገኙ በመሆናቸው ምክንያት ዘይትና ግሪስ ተጠራርጎ ወደ ወንዝ ከመግባቱም በተጨማሪ የመኪና እጥበት ወንዝ ዳርቻዎች ላይ ስለሚከናወን ለወንዞች መበከል ምክንያት ሆኖ ቆይቷል። በከተማዋ አንዳንድ መኖሪያ ቤቶች መጸዳጃ ቤቶቻቸውን ከወንዝ ጋር አገናኝተው ሲያስወግዱ ቆይተዋል። ኢንዱስትሪዎች የወንዝ አካላትን መሠረት አድርገው የተቋቋሙ ሲሆን 45 በመቶ የሚሆኑት ከትንሹ አቃቂ ወንዝ ከ50 ሜትር ባነሰ ርቀት ላይ ይገኛሉ። ይህም ወንዞች እንዲበከሉ ከማድረጉም በተጨማሪ የወንዝ ዳርቻዎች ሣር ቅጠል የማይበቅልባቸውና ለሰዎች መናፈሻነት ከማገልገል ውጭ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

### የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

ዳይሬክተሩ አቶ ሙክታር እንደሚገልጹት፤ አካባቢ ላይ የብክለት ምንጭ የሆኑትን ችግሮች ለማስወገድ በርካታ የመፍትሄ እርምጃዎች እየተወሰዱ

> “የወንዝ ዳርቻዎች አረንጓዴና ጽዱ እንዲሆኑ እየተሰራ ነው። ከመጸዳጃነት፣ ከደረቅ ቆሻሻ መጣያነት፣ ከፋብሪካ ቆሻሻ ማስወገጃነት፣ ከጋራዥና ከመኪና ማጠቢያነት እንዲሁም ሕገ-ወጥ የግንባታ ኳሪ ማውጫነት ነጻ እንዲሆኑ እየተደረገ ነው”

ይገኛሉ። አንደኛ የወንዝ ዳርቻዎቹን አረንጓዴና ጽዱ እንዲሆኑ እየተሰራ ነው። ከመጸዳጃነት፣ ከደረቅ ቆሻሻ መጣያነት፣ ከፋብሪካ ቆሻሻ ማስወገጃነት፣ ከጋራዥና ከመኪና ማጠቢያነት እንዲሁም ሕገ-ወጥ የግንባታ ኳሪ መውጫነት ነጻ እንዲሆን እየተደረገ ነው። ኳሪ ሲባል የማዕድን ሚኒስቴር ወይም የሚመለከተው አካል ሳያውቀው ድንጋይ ወይም አሸዋ ማውጣት፤ የአካባቢ ጥበቃ ጥናት ሳይደረግና ተጽዕኖው ሳይታወቅ ቁፋሮ ማካሄድ እና የተፈቀደለትን የቦታ ስፋት ወይም የጥልቀት መጠን አልፎ መቆፈርን ይመለከታል።

በተፋሰስና አረንጓዴ ቦታዎች ላይ ፕላኑን ያልጠበቀ የይዞታ አሰጣጥና ሕገ-ወጥ ግንባታዎችን ለማስቀረት ከደንብ ማስከበር ባለሥልጣንና የከተማዋ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ ጋር በመሆን እየተሰራ ነው። አስገዳጅ ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር በአረንጓዴ ቦታዎች ላይ ለገረጋንቲና ነጭ ድንጋይ ማውጫ መሬት እንዳይሰጥ፤ አስገዳጅ ሆኖ ከተሰጠም ከምርት በኋላ መልሶ በማልማት አረንጓዴና ጽዱ እንዲሆን እንደሚሰራ ነው አቶ ሙክታር ያስረዱት።

የከተማው የላይኛው ተፋሰስ የመተንፈሻ ሳንባ ቢባልም በአካባቢው ውበትም ሆነ ሥርዓተ ምህዳሩ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ባለው የባሕር ዛፍ ዝርያ ተሸፍኖ ቆይቷል፡፡ ይህን ቀስ በቀስ ለሥርዓተ ምህዳሩና ኢኮ-ቱሪዝም እንዲሁም ለከተማዋ ውበት አስተዋጽኦ ባላቸው አገር በቀል ዛፎች በመተካት እየተሰራ ይገኛል፡፡ ከኢንዱስትሪዎች የሚመነጨውንና አካባቢ ላይ የሚያደርሰውን ብክለት ለመፍታት ከኢንዱስትሪ ባለቤቶች ጋር ውይይት አድርጎ በመፍትሄዎቹ ላይ መግባባት በመፍጠር ለውጥ የሚመጣበትን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ ባለሥልጣኑ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል። በ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወር የአካባቢ ብክለት በሚያደርሱ ተቋማት ላይ በተደረገ ክትትል 1 ሺህ 604 ላይ እርምጃ ለመውሰድ ታቅዶ በ1 ሺህ 575ቱ ላይ የተወሰደ ሲሆን ይህም አፈጻጸሙ 98 ነጥብ 2 በመቶ ነው። ከዚህ አንጻር ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው 71 አምራች ተቋማት ሲሆኑ 1 ሺህ 468 አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ናቸው። እሽጋ የተደረገባቸው 26 አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሲሆኑ 10ሩ ደግሞ አምራች ተቋማት ናቸው። እነዚህ የተወሰዱ እርምጃዎች በሁሉም ክፍለ ከተሞች ከአየር፣ ከድምፅ እና ከሽታ ጋር የተያያዙ እንደሆኑ የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተሩ አቶ ሙክታር ገልጸዋል።

ከሆስፒታሎች፣ ፋብሪካዎችና ከመሳሰሉ ተቋማት ተገቢ ባልሆነ አያያዝና ቦታዎች እየተወገዱ ያሉትን መርዛማ ወይም አደገኛ ቆሻሻዎች መጠንና የአወጋገድ ዘዴ እንዲሁም የማስወገጃ ቦታዎችን በጥልቀት በማስጠናት ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ እንዲወገዱ እየተሰራ ነው። በ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወርም የኬሚካል እና አደገኛ ቆሻሻ የሚያመነጩ 225 አምራች ተቋማትን ለመከታተልና ለመቆጣጠር ታቅዶ 221 የሚሆኑት ላይ መፈጸም ተችሏል።

ፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻዎች ከምንጩ በዓይነት በዓይነታቸው ተለይተው ለኃይል ምንጭነትና ለተፈጥሮ ማዳበሪያነት እንዲሁም በመልሶ መጠቀም ምርት እንዲሰጡ ወይም ለተገቢው አገልግሎት እንዲውሉ በማድረግ ብክለትን ለመቀነስ ጥረት እየተደረገ እንደሆነ አቶ ሙክታር ያብራራሉ።

በተቋማት ከአሰራር ቅንጅት መጓደል የተነሳ የሚመነጩትን የአካባቢ የብክለት ችግሮች በአካባቢ ላይ ተጽዕኖ በማድረስ የሕብረተሰብ ጤናና የልማቱን ቀጣይነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡ የአገልግሎትና የልማት ሥራዎች ከመተግበራቸው በፊት መናበብና መረዳዳት እንዲኖር በተቋማቱ መካከል ጥብቅ ቅንጅታዊ አሰራር በመዘርጋት እየተሰራ ይገኛል፡፡

የአካባቢ ጥበቃ ሥራ በአንድ ጀምበር ለውጥ የማይመጣበት እንደመሆኑ መጠን የማያቋርጥ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ ማድረግን ይጠይቃል፡፡ ተፋሰስ ባለባቸው አካባቢዎች፣ የማምረቻና የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ዙሪያ የተጠናከረ ክትትልና ቁጥጥር በማካሄድ እየተሰራ እንደሚገኝም ነው ዳይሬክተሩ አቶ ሙክታር የገለጹት፡፡

# ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ

## የጨረታ ማስታወቂያ ል/ክ/ከ/ወ/10/ፋ/ጽ/ቤት

## የግዥ መለያ ቁጥር 02/2018

በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ፋ/ጽ/ቤት ለወረዳው ጽ/ቤቶች ለ2018 በጀት ዓመት በሎት የተጠቀሱትን እቃዎች በግልጽ ጨረታ ህጋዊ አቅራቢዎችን አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ አቅራቢዎች መሳተፍ ይችላሉ።

| የሎት ቁጥር | የሎት ምድብ | የጨረታ ማስከበሪያ CPO |
|---|---|---|
| ሎት.1 | የመኪና ጎማ የሚኒባስ እና የመኪና ጎማ BYD ከነ ቸርኬ ግዥ እና የሞተር ሳይክል ጎማ ግዥ | 25,000.00 |
| ሎት.2 | የፈርኒቸር እቃ ግዥ | 25,000.00 |
| ሎት.3 | የደንብ ልብስ ግዥ | 5,000.00 |
| ሎት.4 | ሞንታርቦ ከነአፓሊፋየር እቃ ግዥ | 20,000.00 |
| ሎት.5 | ዋየርለስ ማይክ ግዥ | 10,000.00 |

**በዚሁም መሰረት:-**

1. ተጫራቾች ህጋዊ የ2018 የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸው እና የዘመኑን ግብር የከፈሉበትን ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
2. ተጫራቾች VAT ተመዝጋቢ የሆኑና የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ እና በመንግስት ግ/ን/ኤጀንሲ ድህረ ገፅ ላይ በአቅራቢዎች ምዝገባ ዝርዝር የተመዘገቡ ህጋዊ የVAT ተመዝጋቢ የሆኑና የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፡፡
3. ጥቃቅንና አነስተኛ ተጫራቾች ካደራጃቸው ባለሥልጣን በአምራችነት የተደራጁበትን ድብዳቤ በማምጣት የጨረታ ሰነድ በነፃ በመውሰድ 3 ፐርሰንት ቅናሽ የሚደረግላቸው እራሳቸው ላመረቱት እቃና ቫሊው አድ ላደረጉት እቃ ብቻ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተ ረጋገጠ ሲፒኦ ብቻ/cpo/ ከጨረታ ሰነዶች ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. ተጫራቾች ጨረታው በአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ አዲስ ልሳን ጋዜጣ ላይ ከወጣበት ዕለት አንስቶ በተከታታይ 10 የስራ ቀናት ውስጥ የማይመለስ ብር 200.00 /ሁለት መቶ ብር ብቻ/ በመክፈል በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ፋ/ጽ/ቤት የግዥ ቡድን መሪ ቢሮ በመምጣት የጨረታ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
6. ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዳቸውን በታሸገ ኤንቨሎፕ ማስታወቂያው ከወጣበት ዕለት አንስቶ በተከታታይ 10 የስራ ቀናት በወረዳ 10 ፋ/ጽ/ቤት የመንግስት ግዥ ቢሮ ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
7. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ11ኛው ቀን 2፡30 ሰዓት ታሽጎ በዕለቱ ከቀኑ 3፡00 ሰዓት በወረዳው10 ፋ/ጽ/ቤት በመንግስት ግዥ ቢሮ ይከፈታል፡፡ የመክፈቻ ቀኑ ቅዳሜና እሁድ ወይም የበዓል ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ታሽጎ ይከፈታል፡፡
8. ተጫራቾች የጨረታ ሳጥን ከመከፈቱ በፊት ለተወዳደሩበት ሎት የተሟላ የፍላጎት መግለጫ እና ሳንፕል ማዘጋጀትና ማቅረብ ይጠበቅባችዋል፡፡
9. ተጫራቾች የሚወዳደሩበትን ለእያንዳንዱ ቫት ጋር ያለውን ዋጋ ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡
10. የዘገየ ጨረታና በጨረታ መክፈቻ ላይ ያልተነበበ ጨረታ ተቀባይነት የለውም፡፡
11. አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉባቸውን እቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት ግዥ ፈፃሚው መስሪያ ቤት ድረስ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
12. ለጨረታ ከቀረቡት እቃዎች ዝርዝር ውስጥ ጽ/ቤቱ እስከ 20 ፐርሰንት ጨምሮ ወይም ቀንሶ የመግዛት መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡
13. መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨማሪ ማብራሪያና ጥያቄ፡-** ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 10 ፋ/ጽ/ቤት የመንግስት ግዥ ቢሮ ቁጥር 003 በስልክ ቁጥር 0115574351/ 0115574176 በመደወል ወይም ቅ/ልደታ ቤተ ክርስቲያን ጀርባ አዲስ አበባ ፎምና ፕላስቲክ ፋብሪካ አጠገብ ያለው ቢሮ በአካል በመቅረብ መጠየቅ ይቻላል፡፡

**በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10**
**ፋይናንስ ጽ/ቤት**

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የ2018 በጀት ዓመት የተለያዩ የቢሮ ዕቃዎችን የመኪና ሰርቪስ በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል።

| የሎት ቁጥር | የግዥ ዓይነት ዝርዝር/ሎት | የጨረታ ማስከበሪያ መያዣ/CPO |
|---|---|---|
| 1 | አላቂ የፅህፈት ዕቃዎች | 10,000 |
| 2 | አላቂ የፅዳት ዕቃዎች | 5,000 |
| 3 | የደንብ አልባሳት | 2,000 |
| 4 | የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች | 20,000 |
| 5 | ቋሚ የቢሮ ዕቃዎች | 20,000 |

**ማሳሰቢያ፡-**

- ተጫራቾች በዘርፉ የተመዘገቡበትን የታደሰ የንግድ ስራ ፈቃድ፣ ተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የግብር ከፋይ ምዝገባ ሰርተፍኬት እና የንግድ ስም ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ምዝገባ ምስክር ወረቀት ያላቸው የዘመኑን ግብር የከፈሉበትን ማስረጃዎች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል።
- ከብር 100,000.00 /አንድ መቶ ሺ/ በላይ ለማቅረብ የሚወዳደሩ ተጫራቾች የቫት/VAT/ ተመዝጋቢ ሰርተፍኬት ማቅረብ አለባቸው።
- ተጫራቾች የሚያቀርቧቸው ሰነዶች ሁሉ ተነባቢ መሆን ይኖርባቸዋል።
- የጨረታ ማስከበሪያ በሲፒኦ /CPO/ ወይም የባንክ ጋራንቲ፣ በጥሬ ገንዘብ የተከፈለበት ደረሰኝ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
- ጥቃቅንና አነስተኛ በራሳችሁ ምርት ብቻ ነው መወዳደር የምትችሉት።
- ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከሚዘጋበት ቀንና ሰዓት ድረስ የጨረታ ሰነድ መግዣ ለሎት የግዥ ዓይነት የተቀመጠውን የማይመለስ 300.00ብር /ሦስት መቶ ብር ብቻ/ መስሪያ ቤታችን ለፋይናንስ ዳይሬክቶሬት በመክፈል ሰነዱን ከፋይናንስ ዳይሬክቶሬት አራተኛ ፎቅ መውሰድ ይቻላል።
- ፋይናንሻልና ቴክኒካል ሰነዶችን ኦርጅናል እና ኮፒ በተለያየ ኤንቨሎፖች /ፖስታዎች/ በማሸግ ኦርጅናል እና ኮፒ የሚል ምልክት /ጽሑፍ/ በማድረግ በተለያየ የጨረታ ሳጥን ውስጥ ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት ማስገባት ይኖርባችኋል።
- የጨረታ ማስከበሪያ ሲፒኦ የባንክ ጋራንቲ ወይም ጥሬ ገንዘብ የተከፈለበት ደረሰኝ ኮፒ፣ እንዲሁም ለጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅት ከተቋማቸው አካል የተሰጠ የዋስትና ደብዳቤ ኦርጅናል በታሸገ ፖስታ ውስጥ መካተት አለበት። በኦርጅናል እና በቅጅው መካከል ያለመጣጣም ቢከሰት ኦርጅናሉ፤ የበላይነት ይኖረዋል።
- በመጫረቻ ሰነዱ የቀረበው ዋጋ ጨረታው ከተከፈተበት ዕለት ጀምሮ ከ60 ቀናት በላይ የሚወስድ ከሆነ መስሪያ ቤቱ እንደ አስፈላጊነቱ ግምገማው እስኪጠናቀቅ ድረስ ተጫራቾች ያቀረቡትን የመጫረቻ ዋጋ እንዲያራዝም የመጠየቅ መብት ያለው ሆኖ ለማራዘም ፈቃደኛ ያልሆነ ድርጅት ከጨረታው ይሰረዛል።
- ከተገለፀው ቀንና ሰዓት በኋላ የሚቀርብ የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት አይኖረውም።
- ጨረታው በተጠቀሰው የመክፍቻ ቀን ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በግልፅ የሚከፈት ይሆናል።
- ማንኛውም ተጫራች በሌላ ተጫራች ዋጋ ላይ ተመርኩዞ መጫረት አይችልም።
- ጨረታው በጋዜጣ ላይ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 /አስር/ የስራ ቀናት ክፍት ሆኖ ከቆየ በኋላ በ11ኛው ቀን ከጧቱ 4:30 ሰዓት ተዘግቶ ከጧቱ 5:00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል።
- የጨረታው መዝጊያ እና መክፈቻ ቀን በበዓል ወይም ቅዳሜ እና እሁድ ላይ ከዋለ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ይከፈታል።
- የተጫራቾች ተሟልቶ አለመገኘት የጨረታውን አከፋፈት ሥነ ሥርዓት አያስተጓጉለውም።
- ተጫራቾች የሚሰጡት ዋጋ ላይ ቫትን ያላካተተ ተጫራች የሰጠው ዋጋ ቫትን እንዳካተተ ተቆጥሮ ይወሰዳል።
- መስሪያ ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብት አለው። ተጫራቾች የጨረታ ውጤት ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ በ7 የቅሬታ መስሚያ ቀናት ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ።
- እንዲሁም ከ7 የቅሬታው መስሚያ ቀናት በኋላ ባለው 5 የስራ ቀናት ውል መውሰድ ይችላሉ።
- ተጫራቾች ሰነድ ለመግዛት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አካውንት ቁጥር 1000288861815 ላይ በማስገባት የባንክ ደረሰኝ ማምጣት አለባቸው በጥሬ ገንዘብ መክፈል አይቻልም፡፡

**ማስታወሻ፡-**

1. ይህ የጨረታ ማስታወቂያ የጨረታ ሰነዱ አንድ አካል ተደርጎ ይቆጠራል።
2. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱ ላይ የሰፈሩትን ዝርዝር መረጃዎች በጨረታ መመሪያው ላይ ሰንጠረዥ የተዘረዘሩትን ግዴታዎች በትኩረት ማንበብ ይኖርባቸዋል።

**አድራሻ፡-** 22 ለም ሆቴል ዝቅ ብሎ ኤልሳ ቆሎ አጠገብ

**ለተጨማሪ ማብራሪያ** በስልክ ቁጥር 0111812 0087 መደወል ይችላሉ፡፡

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድና**
**ቁጥጥር ባለሥልጣን ቁ.2**

## በልደታ ክ/ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የልደታ ሰላም የመ/ደ/ት/ቤት
## ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ
## ግዥ መለያ ቁጥር 002/2018

1. ሎት 1 የደንብ ልብስ
2. ሎት 2 አላቂ የቢሮ እቃዎች
3. ሎት 3 አላቂ የህክምና እቃዎች
4. ሎት 4 አላቂ የትምህርት እቃዎች
5. ሎት 5 ለሌሎች አላቂ እቃዎች አቅርቦት
6. ሎት 6 ልዩ ልዩ መሣሪያዎች
7. ሎት 7 ለህንፃና ለቁሳቁስ ለተገጣጣሚ መግዣ
8. ሎት 8 ለፐላን ማሽነሪ እና ማሽን መግዣ

**መስሪያ ቤቱ ባወጣው ግልፅ ጨረታ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች መወዳደር ይችላሉ፡፡**

- በጨረታው ለመወዳደር ፍላጎት ላላቸው ተጫራቾች የታደሰ ንግድ ፈቃድ ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉ፣ በመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ድህረ ገፅ በአቅራቢዎች ዝርዝር የተመዘገቡ፣ የቲንና የቫት ተመዝጋቢ የሆኑና የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፡፡
- የጨረታ አሸናፊዎች የጨረታ ዋስትና 10% ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
- ተጫራቾች በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ዕለት አንስቶ በተከታታይ 10 የስራ ቀናተ የማይመለስ 200 ብር (ሁለት መቶ ብር) በልደታ ሠላም የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት በመገኘት ህንፃ 2 ቢሮ ቁጥር 2 በመምጣት የጨረታ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ
- ተጫራቾች የመጫረቻ ሠነዶቻቸውን በታሸገ ኢንቨሎፐ ማስታወቂያው ከወጣበት ዕለት ጀምሮ በተከታታይ 10 የስራ ቀናት በልደታ ሠላም የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ህንፃ 2 ቢሮ ቁጥር 2 በተዘጋጀው የጨረታ ሣጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
- ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ10ኛው ቀን ከቀኑ 10፡00 ሰዓት ላይ ታሽጎ በዛኑ ቀን ከቀኑ 10፡30 ሰዓት ላይ በልደታ ሠላም የመ/ደ/ት/ቤት ህንፃ 2 ቢሮ ቁጥር 2 ይከፈታል፡፡
- የመከፈቻው ቀን ቅዳሜና እሁድ ወይም የበዓል ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሣሣይ ሠዓት ታሽጎ ይከፈታል፡፡
- ተጫራቾች የጨረታ ሣጥኑ ከመከፈቱ በፊት ለተወዳደሩባቸው ለሎት 1፣ ለሎት 2፣ ለሎት 3፣ ለሎት 4፣ ለሎት 5፣ ለሎት 6፣ ለሎት 7 እና ለሎት 8 ናሙና ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- በጨረታው መከፈቻ ቀን ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ባይገኙም ት/ቤቱ ጨረታውን የመክፈት መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
- ተጫራቾች የሚወዳደሩባቸውን ዕቃዎች በእያንዳንዱ ከቫት ጋር ያለውን ዋጋ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡
- በጨረታ መከፈቻ ላይ ያልተነበበ ጨረታ ተቀባይነት የለውም፡፡
- አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉባቸውን እቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት ግዢ ፈፃሚው መስሪያ ቤት ድረስ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
- ት/ቤቱ እቃዎችን 20% የመቀነስ ወይም የመጨመር መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
- ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ 5000 (አምስት ሺህ ብር) በባንክ የተረጋገጠ ቼክ ወይም CPO ከሰነዶቻቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡

**አድራሻ፡- አዲሱ ደሴ ሆቴል በተሠራው መንገድ ወረድ ብሎ ልደታ ፀበል መብራቱን ተሻግሮ የሚገኝ**

**ስልክ ቁጥር፡- 0113-69-04-39/ 0113-69-22-57**

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በልደታ ክ/ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የልደታ ሰላም አንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት

---

አቶ ይበልጣል ተፈራ ይመር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 13 ካርታ ቁጥር ቦሌ13/62/9/1/252239/00 ሴሪ ቁጥር 0183620 ተመዝግባ የነበረው ኦርጂናል /ዋናው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በተለያየ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባለው 30 ቀናት ውስጥ በቦሌ ለክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ካልቀረበ በምትኩ ሌላ አዲስ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማና እስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በዕንቁነሽ መንግስት ግዛው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከ/ወረዳ 1 የሚገኘው ካርታ ቁጥር 01/56/27753/802037/01 ሴሪ ቁጥር 0246375 በጽ/ቤታችን በስማቸው የተመዘገበ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት /ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝታችሁ /ይዚዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ወ/ሮ/ወ/ት ዘውዴ ነጋሽ በየካ ክ/ከተማ በቀድሞ ወረዳ --- ቀበሌ ----ወይም አዲሱ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር 274 የካርታ ቁጥር የካ/240043/13 ሴሪ ቁጥር 0681997 ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለው የሚል ካለ እስከ 20 ቀን ድረስ አዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን በምትኩ ሌላ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው በአቶ ራጃ ያሲን አብዱራህማን ስም በልደታ ክ/ከተማ የቀድሞ ወረዳ 23 የቀድሞ ቀበሌ 13 የቤት ቁጥር 2037 በቀን 21/11/2008 ዓ.ም የካርታ ቁጥር 05/200/5083/57826/01 ሴሪ ቁጥር 0629436 የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ ታውጆ አገልግሎት እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳዮቹ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጂናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ/ወ/ሮ/ወሪት ቢሻው ወንድሙ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 የይዞታ ልዩ መለያ ኮድ AA000100700808 በሴሪ ቁጥር R 064256 የሆነው ይዞታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ /ሰርተፊኬት/ ስለጠፋባው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለው/ የሚል ሰው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረበ በምትኩ ሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ/ሰርተፍኬት/ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## ክፍት የስራ መደብ ማስታወቂያ

| ተ/ቁ | የስራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | ደመወዝ | ጥቅማ ጥቅም | ተፈላጊ ችሎታ | | ተፈላጊ የሰው ኃይል ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | የትምህርት ዝግጅት | የስራ ልምድ | |
| 1 | የትራንስፖርት ስምሪት ሠራተኛ III | VIII | 11,500.00 | የቤት ድጎማ አበል ብር1,250.00 | በማኔጅመንት፣ በሰፕላይስ ማኔጅመንት፣ በማቴሪያል ማኔጅመንት፣ በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን፣ በአውቶ መካኒክስ የትምህርት መስክ ዲፕሎማ፣ 10+3፣ በደረጃ III፣ IV፣ V የብቃት ማረጋገጫ ያለው/ላት | 4 ዓመት አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ያለዉ/ያላት እና መንጃ ፍቃድ ያለው/ያላት | 1 |
| 2 | የቢሮ አገልግሎት ኃላፊ I | IV | 7,159.00 | የቤት ድጎማ አበል ብር 1,250.00 | በደን ልማት፣ እጽዋት ሳይንስና ተመሳሳይ ዲፕሎማ፣ 10+3፣ በደረጃ III፣ IV፣ V ያለው/ላት | 6 ዓመት አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ያለው/ያላት | 1 |
| 3 | ሁለገብ የጥገና ሠራተኛ IV | IX | 12,566.00 | የቤት ድጎማ አበል ብር 1,250.00 | በእንጨትስራ፣ በኮንስትራክሽን፣ በብረታ ብረት፣ በመካኒክነትና በተመሳሳይ የትምህርት መስክ ቴክኒክና ሙያ ዲፕሎማ፣ 10+3፣ ደረጃ III፣ IV፣ V ያለው/ላት | 6 ዓመት አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ያለው/ያላት | 1 |
| 4 | የኤሌክትሪክ ቴክኒሺያን ሠራተኛ IV | VIII | 11,500.00 | የቤት ድጎማ አበል ብር 1,250.00 | በኤሌክትሪክሲቲና በተመሳሳይ የትምህርት መስክ ዲፕሎማ ወይም 10+3 ወይም ደረጃ III፣ IV፣ V ያለው/ላት | 6ዓመት አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ያለው/ያላት | 1 |
| 5 | የቧንቧ ሠራተኛ III | VIII | 11,500.00 | የቤት ድጎማ አበል ብር 1,250.00 | በቧንቧ፣በመካኒካልና በተመሳሳይ የትምህርት መስክ የቴክኒክና ሙያ ዲፕሎማ ወይም 10+3 ወይም ደረጃ III፣ IV፣ V ያለው/ያላት | 4 ዓመት አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ያለው/ያላት | 1 |
| 6 | የውሃና ፍሳሽ መስመር ዝርጋታና ጥገና ሠራተኛ III | VIII | 11,500.00 | የቤት ድጎማ አበል ብር 1,250.00 | በቧንቧ፣ በመካኒካልና በተመሳሳይ የትምህርት መስክ የቴክኒክና ሙያ ዲፕሎማ ወይም 10+3 ወይም በደረጃ III፣ IV፣ V ያለው/ያላት | 4 ዓመት አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ያለው/ያላት | 1 |
| 7 | የጀነሬተር ኦፕሬተር I | VI | 8,029.00 | የቤት ድጎማ አበል ብር 1,250.00 | በኤሌክትሪክሲቲና በተመሳሳይ የትምህርት መስክ ዲፕሎማ ወይም 10+3 ወይም ደረጃ III፣ IV፣ V ያለው/ላት | 4 ዓመት አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ያለው/ያላት | 1 |
| 8 | አትክልተኛ | III | 6,750.00 | የቤት ድጎማ አበል ብር 1,500.00 | 10ኛ ክፍል ያጠናቀቀ | 2 ዓመት አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ያለው/ያላት | 1 |
| 9 | የሕፃናት ድጋፍና እንክብካቤ ሠራተኛ | VII | 8,478.00 | የቤት ድጎማ አበል ብር 1,250.00 | 10ኛ/12ኛ ክፍል ያጠናቀቀችና በህጻናት እንክብካቤ ስልጠና የወሰደችና ሰርተፊኬት ያለው/ላት | 2 ዓመት በህጻናት እንክብካቤ ያገለገለ/ች | 1 |

**ማሳሰቢያ፡-**

- የምዝገባ ቀን እና ቦታ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት አራት ኪሎ ዳብር ህንፃ የሰው ሀብት አስተዳደርና ልማት ዳይሬክቶሬት 2ኛ ወለል ቢሮ ቁጥር 207 ፡፡
- አመልካቾች የትምህርት ማስረጃችሁን፣ የስራ ልምድ እና የታደሰ የመንጃ ፈቃዳችሁን ዋናውን እና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ በመያዝ መመዝገብ ትችላላችሁ፡፡
- ከግል ተቋማት የሚቀርቡ የስራ ልምድ ማስረጃዎች የስራ ግብር የተከፈለባቸው መሆን አለባቸው።
- ለፈተና ለሚመለመሉ አመልካቾች ፈተና የሚሰጥበትን ቀን እና ቦታ በውስጥ ማስታወቂያ እና በስልክ የምንገልጽ ይሆናል፡፡

**አድራሻ፡-** አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 አራት ኪሎ ወደ ፒያሳ በሚወስደው መንገድ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት አለፍ ብሎ በሚገኘው ዳብር ሕንፃ።

**ስልክ ቁጥር፡-** 011 6 67 32 65/ 011 6 67 34 73

**የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ**

---

**ቁጥር፡- 821/5**

## ክፍት የስራ ማስታወቂያ

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 የብስራት ቅድመ አንደኛ፤ አንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከዚህ በታች በተዘረዘረው ክፍት የስራ መደብ ላይ ሠራተኞችን አወዳድሮ መቅጠር ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም መስፈርቱን የምታሟሉ አመልካቾች መወዳደር የምትችሉ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

| ተ.ቁ | የስራ መደቡ መጠሪያ | ተፈላጊ ችሎታ | የስራ ልምድ | ደመወዝ | ብዛት | ደረጃ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ ሠራተኛ (ሞግዚት) | 10ኛ /12ኛ/ ክፍል ያጠናቀቀ/ች/፤ በህጻናት አያያዝ እና እንክብካቤ /ሞግዚትነት/ ስልጠና ሰርተፊኬት ያላት | 0 ዓመት | 8478.00 | 2 | VII (7) | በቋሚነት |
| 2 | የፅዳት ሠራተኛ | 12ኛ ክፍል ያጠናቀቀና 2 ዓመት የስራ ልምድ ያለው /ያላት ወይም 10ኛ ክፍል ያጠናቀቀና 2 ዓመት የስራ ልምድ ያለው/ ያላት ወይም 9ኛ ክፍል ያጠናቀቀና 3 ዓመት የስራ ልምድ ያለው /ያላት ወይም 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀና 4 ዓመት የስራ ልምድ ያለው /ያላት | | 6750.00 | 1 | III | ኮንትራት |

---

በሉላይና ዘውድነህ በካርታ ቁጥር ቦሌ10/123/2/5/86865/00 የተሰጠበት ቀን 19/10/2011 ዓ.ም የቦታው ስፋት 150 ካ.ሜ የሆነው ካርታ መጥፋቱ ተገልጾ ለፖሊስ እንዲፃፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ወረዳ 09 የሆነው መኖሪያ ቤት በሉላይና ዘውድነህ በካርታ ቁጥር ቦሌ10/123/2/5/86865/00 የተሰጠበት ቀን 19/10/2011 ዓ.ም የቦታው ስፋት 150 ካ.ሜ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ኦርጅናል የጠፋ ስለሆነ ይዞታውን (ቤቱን) በዕዳ ይገፎዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ካርታውን የምናዘጋጅ መሆኑን እየገለፅን የማስታወቂያ ወጪ በባለጉዳዩ የሚሸፈን መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር**
**ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 07 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000090709401 በአቶ ኑርአዲስ አብደላ መሀመድ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) የጠፋባቸው መሆኑን በቀን 27/04/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይገፎዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ90 (ዘጠና) ቀናት ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# ከፍልሚያ ሜዳው ባሻገር

**በሳህሉ ብርሃኑ**

በእግር ኳስ ዓለም ውስጥ መደበኛ ጨዋታዎች አሉ፤ ደግሞ ደም የሚያሞቁና ታሪክን በሁለት ጎራ ከፍለው የሚያፋልሙ የ‘ደርቢ’ ጨዋታዎች አሉ። ለብዙዎች እግር ኳስ መዝናኛ ሊሆን ይችላል፤ የ‘ደርቢ’ ፍልሚያዎች ግን ትርጉማቸው ብዙ ነው። የ‘ደርቢ’ ጨዋታዎች በሚካሄዱበት ዕለት ውጥረቱ ከሜዳ ይሻገራል፤ ጎረቤት ከጎረቤቱ ይኳረፋል፤ አባትና ልጅ ለ90 ደቂቃ እግር ኳሳዊ ባላንጣ ይሆናሉ።

‘ደርቢ’ ማለት የአንድ ከተማ ደጋፊዎች በሁለት ተለይተው “ይህች ከተማ የኔ ናት” የሚሉበት የክብር መድረክ ነው። ተጫዋቾች ያልፋሉ፤ አሰልጣኞች ይቀየራሉ፤ ስታዲየሞች እንኳ ሊፈርሱ ይችላሉ። ነገር ግን የአንድ ‘ደርቢ’ ድል የሚሰጠው ኩራትና ሽንፈቱ የሚያስከትለው የቅስም ስብራት ለትውልድ የሚሻገር ጠባሳ ጥሎ ያልፋል።

በዚህ አምድ ኳስ ከክብነቷ ወጥታ የሰው ልጅ ስሜት መተንፈሻ ወደምትሆንባቸው፣ ዓለምን ወደሚያስደንቁ ታላላቅ የ‘ደርቢ’ ፍልሚያዎች እንጓዛለን። መነሻችንንም ቱርኪዬን በማድረግ የ‘ደርቢ’ ፍልሚያዎችና ደጋፊዎች ስላላቸው ቁርኝት እንቃኛለን፡፡

ለመሆኑ አንድን ጨዋታ ‘ደርቢ’ የሚያሰኘው ምንድነው? ቅርበት ወይስ ጥላቻ? ለዚህ መሰረታዊ ጥያቄ ምላሽ እናገኝ ዘንድ መነሻችንን ኢስታንቡልን እናድርግ፡፡ በእግር ኳስ ውስጥ ስታዲየሞች የጨዋታ ሜዳ ብቻ አይደሉም፤ በተለይ በቱርክዬ ምድር ስታዲየም ማለት የክብር መለኪያ፣ አስደማሚ የድጋፍ ድባብና ተጋጣሚ ቡድኖችን ቅስማቸውን የሚሰብር ስፍራ ነው። የቱርክዬ ደጋፊዎች ለእግር ኳስ ያላቸው ፍቅር ከመደበኛው ስፖርታዊ ድጋፍ አልፎ ወደ ከባድ ሱስ ተቀይሯል።

ታላላቆቹ ሦስት ክለቦች ማለትም ጋላታሳራይ፣ ፌነርባቼ እና ቤሽክታሽ ደርቢ የሆኑበት ምክንያት ከኳስ ጨዋታ ባለፈ ማህበራዊ መደብ፣ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ እና ታሪካዊ ማንነት ላይ የተመሰረተ ስለመሆኑ የዘ ጋርዲያን ዘገባ ያትታል።

የኢስታንቡል ከተማ በቦስፎረስ ባህር ሰርጥ ለሁለት ስትከፈል አንደኛው ወገን አውሮፓ፣ ሌላኛው ደግሞ እስያ ነው። ጋላታሳራይ በአውሮፓው ክፍል የተመሰረተ ሲሆን፣ ፌነርባቼ ደግሞ በእስያ ክፍል ይገኛል። ይህ በመሆኑም በመካከላቸው የሚደረገው ጨዋታ ‘የአህጉራት ደርቢ’ የሚል ስያሜ እንዲያገኝ አስችሎታል። ደጋፊው ጨዋታውን የሚያየው እንደ አንድ ከተማ ቡድኖች ሳይሆን፣ እንደ ሁለት የተለያዩ ዓለማት ፍልሚያ አድርጎ ነው።

በሌላም በኩል ክለቦቹ ሲመሰረቱ የነበራቸው የደጋፊ መሰረት የተለያየ መደብ የነበረው ሲሆን፣ የጋላታሳራይ እግር ኳስ ክለብ የተመሰረተው በጋላታሳራይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሲሆን፣ በወቅቱ የነበሩት ደጋፊዎች የተማሩ፣ የምዕራባውያን አስተሳሰብ ያላቸውና የሀብታሙ መደብ




ፎቶ- ከገፀ ድር

‘የአህጉራት ደርቢ’ የሚል ስያሜ የተሰጠው የቱርክዬው ደማቁ የጋላታሳራይ እና የፌነርባቼ ክለቦች ደርቢ ጨዋታ

አባላት ነበሩ። የፌነርባቼ እግር ኳስ ክለብ እንደዚሁ የተመሰረተው በሰራተኛውና በነጋዴው ማህበረሰብ በመሆኑና ‘የህዝብ ቡድን’ ተብሎ ስለሚታመን፣ ከማንኛውም የፖለቲካ ወይም የኢኮኖሚ ተጽዕኖ ነፃ የሆነ የብዙሃኑ ድምጽ ተደርጎ ይወሰዳል።

ወደ ኢስታንቡል የሚጓዙ የአውሮፓ ታላላቅ ክለቦች ተጫዋቾች ታዲያ ገና አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርሱ የሚቀበላቸው መፈክር “እንኳን ወደ ሲኦል በደህና መጡ” (Welcome to Hell) የሚል ነው። ይህ ማስፈራሪያ ብቻ አይደለም፤ በስታዲየም ውስጥ የሚለኮሱት በመቶዎች የሚቆጠሩ የጭስ ችቦዎች ስታዲየሙን ቀይ እሳት ያስመስሉታል። የቱርክ ደጋፊዎች በጩኸት ከፍተኛውን የ‘ዴሲቤል’ (Decibel) መጠን በመመዝገብ የዓለም ድንቃ ድንቅ መዝገብ ወይም ‘ጊነስ ሪከርድ’ን ደጋግመው ሰብረዋል። ድምፁ በጣም ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ ተጫዋቾች በሜዳ ላይ ጎን ለጎን ቆመው መነጋገር አይችሉም እስከመባል ተደርሷል።

ቢቢሲ የኢስታንቡል ‘ደርቢ’ን “በዓለም ላይ ካሉ እጅግ አስፈሪ እና ስሜታዊ እግር ኳስ ፍልሚያዎች አንዱ” ሲል ዘግቦታል። በተለይ በደጋፊዎች የሚፈጠረውን የድምፅ መጠን እና ስታዲየሞች ውስጥ የሚታየውን የእሳት ጭስ “ከእግር ኳስ ጨዋታ በላይ የሆነ ትርኢት” በማለት ይገልጸዋል።

የቱርክዬ እግር ኳስ ማማ ላይ ያሉት ጋላታሳራይ እና ፌነርባቼ ሲሆኑ፣ ይህ ጨዋታ ሲደርስ መላው ቱርክ ለሁለት ትከፈላለች። በ‘ደርቢ’ው ቀን በኢስታንቡል ጎዳናዎች ላይ እንቅስቃሴ ይቆማል። ደጋፊዎች ቡድናቸው ከተሸነፈ እስከ ቀጣዩ ጨዋታ ድረስ አንገታቸውን ደፍተው ነው የሚኖሩት። ድሉ ግን የሳምንታት ብሔራዊ በዓል ያህል ይከበራል።

እግር ኳስ 90 ደቂቃ ብቻ አይደለም፤ የቤሽክታሽ ደጋፊ ልጁ ሲወለድ

> **“የደርቢ ጨዋታዎች እና ሌሎች የዓለም ታላላቅ የከተማ ፍልሚያዎች ከ90 ደቂቃ ጨዋታ በላይ ናቸው፤ እነዚህ ጨዋታዎች የሰው ልጅ ለማንነቱ፣ ለክብሩና ለሚወደው ስብስብ ያለው ታማኝነት የሚገለጥባቸው መድረኮች ናቸው”**

መጀመሪያ የሚያደርገው የቡድኑን ማሊያ ማልበስ ነው። በቅርቡ እውቁ አሰልጣኝ ጆሴ ሞሪንሆ ወደ ፌነርባቼ ሲመጡ የተደረገላቸው አቀባበል የቱርክዬ ደጋፊዎች ምን ያህል ለስፖርቱ ፍቅር እንዳላቸው ያሳይ ነበር። በሺዎች የሚቆጠሩ ደጋፊዎች ስታዲየም ተገኝተው ለአሰልጣኙ የሰጡት አቀባበል ለብዙ ሀገራት ለዋንጫ ድል የሚሰጥ ዓይነት ነበር። ለዚህም ነው ብዙ ኮከብ ተጫዋቾች በደመወዝ ማነስ እንኳ ሳይገደቡ ያንን ‘የእብደት’ ድባብ ለመቅመስ ወደ ቱርክዬ የሚያመሩት።

የስፖርት ተንታኞችና የስነ-ልቦና ባለሙያዎች እንደሚሉት፣ የቱርክዬ ‘ደርቢ’ዎች ወይም ሌሎች ዓለም አቀፍ የ‘ደርቢ’ ፍልሚያዎች ከስፖርታዊ ውድድር ባለፈ ጥልቅ ማህበራዊ ትርጉም አላቸው። በቱርክ ስፖርት ስነ-ልቦና ላይ ጥናት ያደረጉት የስነ-ልቦና ባለሙያው ሜህመት ኦዝካን (ዶ/ር)፣ “ለብዙ የቱርክዬ ደጋፊዎች ክለባቸው ማለት ቤተሰባቸው ነው። በኑሮ ውስጥ የሚገጥሟቸውን ውጥረቶችና ኢኮኖሚያዊ ጫናዎች የሚረሱት በስታዲየም ውስጥ በሚያወጡት ጩኸት ነው። እዚያ ውስጥ ‘እኔ’ የለም፤ ‘እኛ’ ብቻ ነው ያለው። ያ ደግሞ ለሰው ልጅ ትልቅ የደህንነትና የማንነት ስሜት ይሰጠዋል” ይላሉ፡፡

የቀድሞው የጋላታሳራይ ተጫዋችና የአሁኑ የስፖርት ተንታኝ ሀካን ኡንሳል ስለ ‘ደርቢ’ዎቹ ግለት ሲያስረዳ፣ በቱርክዬ ‘ደርቢ’ መሸነፍ ማለት ለሚቀጥሉት ወራት አንገት ደፍቶ መሄድ ማለት ነው። ደጋፊው ተጫዋቾቹ እንዲያሸንፉ የሚፈልገው ስለ ዋንጫው ብቻ ሳይሆን፣ በከተማዋ ላይ ስላለው ‘የበላይነት ኩራት’ ጭምር ስለመሆኑ ያስረዳሉ፡፡ አክለውም፣ በሜዳ ላይ ያለው ጫና ተጫዋቾችን ወይ ጀግና ያደርጋቸዋል፣ ወይም ሙሉ በሙሉ ያጠፋቸዋል ብለዋል፡፡

ከቱርኪዬ ባሻገር፣ በአርጀንቲና የሚካሄደው የቦካ ጁኒየርስ እና የሪቨር ፕሌት ‘ሱፐር ክላሲኮ’ የዓለም እግር ኳስን ትኩረት የሚስብ እጅግ ግዙፍ ‘ደርቢ’ ነው። በቦነስ አይረስ ከተማ የሚገኘው የቦካ ጁኒየርስ ስታዲየም ‘ላ ቦምቦኔራ’ ደጋፊዎቹ በጋራ ሲዘልሉ የመሬት መንቀጥቀጥ ያህል እንደሚርገበገብ ይነገራል። እዚህ ደርቢ ላይ ኳስ ጨዋታ ብቻ ሳትሆን የክብርና የማንነት መገለጫ ነች፤ ደጋፊዎቹ በሚፈጥሩት ባለቀለም ወረቀቶችና የጭስ ድባብ ሜዳው ለተመልካችም ሆነ ለተቃራኒ ቡድን ተጫዋቾች እጅግ አስፈሪና አስደሳች ድባብን ይፈጥራል።

‘ኦልድ ፈርም’ በሚል መጠሪያ የሚታወቀው የስኮትላንዱ የሴልቲክ እና ሬንጀርስ ፍልሚያ ታሪካዊ ‘ደርቢ’ በታሪክ፣ በኃይማኖትና በፖለቲካዊ ልዩነቶች የታጀበ በመሆኑ በዓለም ላይ ካሉ እጅግ ጠንካራ ‘ደርቢ’ዎች መካከል አንዱ ነው። በግላስኮ ከተማ የሚካሄደው ይህ ፍልሚያ ደጋፊዎቹ ለ90 ደቂቃ ሳይታክቱ በሚያሰሟቸው መዝሙሮችና ጩኸቶች ይታወቃል። በተመሳሳይ የጀርመኑ ቦሩሲያ ዶርትሙንድ ደጋፊዎች የሚፈጥሩት ‘ቢጫው ግንብ’ (The Yellow Wall) በሺዎች የሚቆጠሩ ደጋፊዎች በአንድ ላይ ቆመው የሚፈጥሩት አስገራሚ ትርኢት፣ እግር ኳስ ከስፖርታዊ ውድድር ባለፈ እንዴት ያለ ጥልቅ ስሜትና ጥበባዊ ድባብ ሊኖረው እንደሚችል ለዓለም የሚያሳይ አብነት ነው።

ባለሙያዎች እንደሚስማሙበትና ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃንም ደጋግመው እንደዘገቡት፣ የቱርክዬ ‘ደርቢ’ዎችም ሆኑ የዓለም ታላላቅ የከተማ ፍልሚያዎች ከ90 ደቂቃ ጨዋታ በላይ ናቸው። እነዚህ ጨዋታዎች የሰው ልጅ ለማንነቱ፣ ለክብሩና ለሚወደው ስብስብ ያለው ታማኝነት የሚገለጥባቸው መድረኮች ናቸው። በኢስታንቡል ድምፅ የሚያደነቁረው ጩኸት፣ በቦነስ አይረስ የሚርገበገበው ስታዲየም፣ ወይም በግላስኮ የሚሰማው ጥልቅ መዝሙር ሁሉ የሚያረጋግጡት እውነት አለ። በአንድ በኩል እግር ኳስ ውበት የሚኖረው በሜዳው ላይ በሚታየው ጥበብ ብቻ ሳይሆን፣ በተመልካቹ ደም ውስጥ በሚፈሰው ስሜት ጭምር ነው። በሌላም በኩል ‘ደርቢ’ዎች የሚነግሩን ትልቁ ቁም ነገር እግር ኳስ ቋንቋ፣ ኃይማኖትና ድንበር ሳይገድበው ሰዎችን በአንድ ስሜት የማስተሳሰር ትልቅ ኃይል እንዳለው ነው።